

የሁለት አባቶች - አንድ ብሶት

ገጽ 16



የዓድዋ ድልን እንዲዘክር ተደርጎ እየተገነባ ያለው ፕሮጀክት

ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 175 የካቲት 25 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ለ20 ወራት የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመቋረጡ መቸገራውን የሐራ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ

## - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በበኩሉ በቅርቡ አገልግሎቱን አስጀምራለሁ ብሏል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ለአንድ ዓመት ከስምንት ወራት የተቋረጠው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለበርካታ ችግር እንደዳረጋቸው በሰሜን ወሎ ዞን የሐራ ከተማ ነዋሪዎች ተናገሩ። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በበኩሉ ለህዝብ መገልገያ ተቋማት ቅድሚያ በመስጠት አገልግሎቱን ለማስጀመር እየሰራ መሆኑን አስታውቋል።

የሐራ ከተማ ነዋሪ አቶ መላኩ ምስጋናው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ለአንድ ዓመት ከስምንት ወራት የተቋረጠው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለበርካታ ችግር ዳርጓቸዋል።

ኤሌክትሪክ በመቋረጡ ምክንያት ከፍተኛ ለሆነ የውሀ ችግር ተዳርገናል። ያልተጣራ አንድ ጀሪካን ውሀ ከ35 እስከ 40 ብር እየገዛን ነው የምንጠቀመው። ይህም ከገንዘብ ኪሳራ ባለፈ ለጤናችን ጠንቅ ሆኖናል ብለዋል።

ከውሃ በተጨማሪም ወፍጮ ቤት የምናገኘው ረጅም ኪሎ ሜትር ተጉዘን ነው። የስልክ ኔትወርክ አገልግሎትም በሚፈለገው ልክ እያገኘን አይደለም። በዚህ የተነሳም

ለ20 ወራት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








አቶ ጌታቸው ቢያዝን

## በአማራ ክልል ከ10 ሚሊዮን በላይ መጽሐፍት ቢታተሙም የተሰራጨው 2 ነጥብ 7 ሚሊዮኑ ብቻ ነው

ገጽ 4

## እስራኤል በጤናው ዘርፍ ለኢትዮጵያ ሙያዊ ድጋፍ እንደምታደርግ ተገለጸ



ፎቶ፡- አሸናፊ ጉደታ

አምባሳደር አለልኝ አድማሱ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ ፡- የእስራኤል የጤና ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ልምድ በማካፈል፣ የእውቀት ሽግግር በማድረግና የኢትዮጵያ ባለሙያዎች በእስራኤል እንዲማሩ በማድረግ የጤና ዘርፍ እንዲዘምን እየሠራች መሆኑን በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አለልኝ አድማሱ አስታወቁ።

እስራኤል በጤናው ዘርፍ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## " አፍሪካውያንን ከፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ጎን ለማሰለፍ ኢትዮጵያኒዝምን ማጠናከር ያስፈልጋል"

- ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ
የታሪክ ተመራማሪ


**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካውያንን ኢትዮጵያ ከያዘችው የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ጎን ለማሰለፍ ቅድሚያ ኢትዮጵያኒዝምን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተመራማሪና መምህሩ ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ ገለጹ።

ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በዓድዋ ድል ያስመዘገበችው ድል ነጮች ስለ ጥቁሮች የነበራቸውን የተዛባ አስተሳሰብ

" አፍሪካውያንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ሳፋሪኮም የዲጂታል አሠራሮችን ለማሳደግ ስምምነት ተፈራረሙ

**ማርቆስ በላይ**

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ የዲጂታል አሠራሮችን ለማሳደግ እና በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ስትራቴጂካዊ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ።

በባንኩ ዋናው መሥሪያ ቤት የተደረገውን ስምምነት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ እና የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አነዋር ሶሳ ተፈራርመዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በስምምነቱ ወቅት እንደገለጹት፤ ስምምነቱ የንግድ ባንክን ሞባይል ባንኪንግ መተግበሪያ በመጠቀም የሳፋሪኮም አየር ሰዓትና የተለያዩ ጥቅሎችን መግዛት የሚያስችል ነው።


ፎቶ - ሀዱሽ አብርሃ

ሳፋሪኮም ከመደበኛ የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ መሸጫዎች በተጨማሪ ደንበኞች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሞባይል ባንኪንግ መተግበሪያን በመጠቀም ያለምንም የአገልግሎት ክፍያ የአየር ሰዓት ለመግዛትና የኢንተርኔት ክፍያ ለመፈጸም የባንኩን የፋይናንስ አማራጮች መጠቀም እንደሚችሉ አስረድተዋል።

ሳፋሪኮም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የውጪ ቴሌኮም ኩባንያ በመሆኑ የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ታሪካዊ ያደርገዋል ያሉት አቶ አቤ፣ በዚህም ከሳፋሪኮም ቴሌኮሙኒኬሽን ኢትዮጵያ ጋር የተደረገው ስምምነት ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት አለው ብለዋል።

እንደ አቶ አቤ ገለጻ፤ ባንኩ የደንበኞችን ፍላጎት ለማሳደግ የተለያዩ ዘመናዊ አሠራሮችን ተግባራዊ እያደረገ ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከባንክ ኢንዱስትሪው ድጋፍን የሚጠይቅ በመሆኑ እንደ ንግድ ባንክ ካሉ ዋና የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢ ተቋማት ጋር በትብብር የመሥራት ልምድን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለፉት 80 ዓመታት የኢትዮጵያ የፋይናንስ ኢንዱስትሪን በማጠናከር ረገድ ሚናው የጎላ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ባንኩ የሞባይል ባንኪንግ፣የኤቲኤም አገልግሎት የመሳሰሉ የራሱ ዲጂታል መድረኮች እንዳሉት በመግለጽ የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ይበልጥ ለማዘመን እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዚህም ስምምነቱ ባንኩ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በዘመናዊ አሠራር ለመደገፍ የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፤ አካታች የፋይናንስ አገልግሎትን ለማቅረብና አሠራሩን የበለጠ ቀልጣፋና ፈጠራ የታከለበት ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አነዋር ሶሳ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ የዲጂታል አገልግሎት እየተስፋፋ መምጣቱ የሚበረታታ ነው። በዚህም ከባንኩ ጋር በትብብር መሥራት ለደንበኞች ተገቢውን የዲጂታል አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ የተገልጋዮችን ፍላጎትን ለማሟላት ያስችላል ብለዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ዓለም በልዩ ልዩ የቴክኖሎጂ ሥራዎች አንድ እየሆነች በመጣችበት በዚህ ጊዜ የተለያዩ የዲጂታል አማራጮችን በመጠቀም አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው። በዚህም ሳፋሪኮም ከባንኩ ጋር ያደረገው ስምምነት ዲጂታላይዜሽን አሠራር አገልግሎቶችን ተደራሽና ቀልጣፋ ለማድረግ ይረዳል።



# ለበጎ ሰው ሽልማት ከ100 በላይ ዕጩዎች ተጠቆሙ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ለበጎ ሰው ሽልማት በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ከመቶ በላይ ዕጩዎች ተጠቁመዋል ሲል የበጎ ሰው ሽልማት ቦርድ አስታወቀ።

የበጎ ሰው ሽልማት ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ነጻነት ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የበጎ ሰው ሽልማት ዕጩዎችን መቀበል ከጀመረበት የካቲት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ከመቶ በላይ ሰዎች በዕጩነት ተጠቁመዋል።

ያም ሆኖ ግን ጠቋሚዎች የመረጡትን ሰው መረጃ ያለማሟላት እና ሰሞኑን ሃገሪቱ ላይ ያጋጠመው የኢንተርኔት መቆራረጥ ችግር የዕጩዎች ቁጥር ከአምናው ጋር ሲነፃፀር አናሳ እንዲሆን አድርጐታል ብለዋል።

በየዓመቱ የሚገጥመን ችግር ሰዎች ዕጩዎችን ሲጠቁሙ የሰዎቹን ሙሉ መረጃ ያለመግለጽ ነው ያሉት የቦርድ ሰብሳቢው፤ ይህ ደግሞ ለሃገር ብዙ የሠሩ ሰዎች በቂ መረጃ ባለመገኘቱ ማጣሪያውን ሳያልፉ እንዲቀሩ ያደርጋል ብለዋል። ስለዚህ ጠቋሚዎች በተዘጋጀው መጠቆሚያ ቅጽ መሠረት የዕጩዎችን ሙሉ ስም እና አድራሻ እንዲሁም ሙሉ የሕይወት ታሪካቸውን መግለጽ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በዕጩነት የሚቀርቡ ሰዎችን ዕድል ከማስፋት አንጻር የዘንድሮ የበጎ ሰው ሽልማት ዘርፉን በይዘት አስፍቶ ቀርቧል ያሉት አቶ ነፃነት፤ ከዚህ በፊት በሳይንስ ዘርፍ፣ በኪነጥበብ ዘርፍ፣ በንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፍ እንዲሁም በሚዲያ እና ጋዜጠኝነት ዘርፍ ላይ ሲሸልም መቆየቱ ይታወሳል ብለዋል። በዚህ ዓመት ባሉት ዘርፎች ላይ የቴክኖሎጂ፣ የስዕል፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የዲጂታል ሚዲያ ዘርፍ ዕጩዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል ብለዋል።

የበጎ ሰው ሽልማት በሚካሄድበት ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከየካቲት አንድ ጀምሮ ዕጩዎችን መቀበል መጀመሩን አስታውሰው፤ ሽልማቱም ከየትኛውም የሀገራችን አካባቢዎች፣ የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዘር ልዩነት ሳይኖር ለሀገር መልካም ሥራ የሠሩ ሰዎች ዕውቅና የሚያገኙበት ነው ብለዋል።

ጥቆማው ሙሉ በሙሉ የሚመጣው ከሕዝብ ሲሆን በጎ ሰዎችን በመሸለም እና እውቅና በመስጠት ሌሎች በጎ ሰዎችን እናፍራ በሚል መርሕ የሚካሄድ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በየዓመቱ ከ800 በላይ ዕጩዎችን የሚቀበለው የበጎ ሰው ሽልማት በዚህ ዓመትም ነሐሴ ወር ማብቂያ ላይ የሚደረግ ይሆናል። ከዚያ በፊትም ቦርዱ የዕጩዎቹን ተገቢነት ማረጋገጥ እና የሕይወት ታሪካቸውን የማጣራት ሥራ የሚሠራ ሲሆን የመጨረሻዎቹ ዕጩዎች በቦርዱ ከታዩ በኋላ ለየዘርፉ በሙያቸው ብቁ የሆኑ አምስት አምስት ዳኛዎችን በመመደብ እንዲዳኙ ይደረጋል ።

የበጎ ሰው ሽልማት ለአስራ አንድ ዓመት ያለማቋረጥ ሲሸልም እና እውቅና ሲሰጥ የቆየ ድርጅት ነው ያሉት አቶ ነፃነት፤ በዚህ ዓመት የሚደረገው የበጎ ሰው ሽልማትም ድርጅቱ ተጠናክሮ መቀጠሉን ማሳያ መሆኑን ጠቁመው፤ በሃገር ደረጃ የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት በተገኙበት እውቅና የሚሰጥበት መርሐ ግብር መሆኑን እንደማሳያ አንስተዋል።

# ክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ቱሪስቶችን አስተናግዷል

*መዓዛ ማሞ*

አዲስ አበባ፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ባለፉት ስድስት ወራት 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶችን ማስተናገዱ ተገለጸ።

የክልሉ ባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይለማርያም ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት 1 ሚሊዮን 490 ሺ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች ክልሉን ጎብኝተዋል።

ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ወቅት የነበረው የአገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥር 1 ነጥብ 1 ሚሊዮን እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው፤ የቁጥሩ መጨመር በክልሉ የሚገኙ የቱሪዝም መስሕቦችን በሚገባ በማስተዋወቅ የተገኘ ውጤት መሆኑን ጠቁመዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በኮቪድ -19 ምክንያት እና በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ከነበረው የጸጥታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የውጪ ሀገር ጎብኚዎች ቁጥር ዝቅተኛ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ኃይለማርያም፤ በዚህ ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ወደ ክልሉ የመጡ የውጪ አገር ጎብኚዎች ቁጥር ላይ መጠነኛ መሻሻል መኖሩን እንደሚያሳይ ተናግረዋል።

በዚህም መሠረት ባለፉት ስድስት ወራት 4100 የውጪ አገር ጎብኚዎች ክልሉን እንደጎበኙ ጠቁመው፤ይህ ቁጥር ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ600 ብልጫ ቢኖረውም በስድስት ወሩ ከታቀደው አንጻር አነስተኛ ነው ብለዋል። ቁጥሩ እንዲጨምር ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነም ተናግረዋል።



እንደ አቶ ኃይለማርያም ገለጻ፤ የብሔር ብሔረሰቦች ባሕሎች ይበልጥ ጎልተው እንዲወጡ ባለፉት ስድስት ወራት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። በክልሉ ልዩ የሆኑ ባሕሎችን እና ቅርሶችን በመለየት እና በመመዝገብ የዓለም ቅርስ ለማድረግም የተለያዩ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። የጌዴኦ አግሮ ፎረስተሪ ጥናት ተጠናቆ ለዩኔስኮ ተልኳል።

የወላይታ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ "ጊፋታ" እንዲሁም የደራሼ ብሔረሰብ ባሕላዊ ሙዚቃ "ፊላ" እና የጋሞ ባሕላዊ የሽምግልና ሥነ-ሥርዓት "ድቡሻ"ን በማስጠናት በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ የማድረግ ሥራዎች እንደተጀመሩም ኃላፊው ጠቁመዋል።

ከሁሉም የሚዲያ ተቋማት የተውጣጡ የጋዜጠኞች ቡድን በክልሉ የሚገኙ የመስሕብ ቦታዎችን እንዲጎበኙ በማድረግ ተመልሰው ክልሉን በሚዲያ እንዲያስተዋውቁ የማድረግ ሥራም እንደተሠራ ተናግረዋል።

አቶ ኃይለማርያም እንደሚሉት ቢሮው ቱሪስቶች በክልሉ ያሉ መዳረሻ ቦታዎችን የሚመለከት መረጃ የሚያገኙበትን መተግበሪያ የማዘጋጀት ሥራም ተከናውኗል።

በክልሉ አሌ ልዩ ወረዳ እና ኮንሶ ዞን እንዲሁም ደራሼ ልዩ ወረዳ የነበረው የጸጥታ ሁኔታ፣ አማሮ አካባቢ የነበረው የሸኔ እንቅስቃሴ በክልሉ ቱሪስቶች መተው ረጅም ጊዜ እንዳይቆዩ እና በርከት ብለውም እንዳይመጡ ተጽዕኖ መፍጠሩን ኃላፊው ተናግረዋል።

ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ አካባቢም ያለው የሸኔ እንቅስቃሴ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር ከኦሮሚያና ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመቀናጀት እየተሠራ መሆኑን ኃላፊው ተናግረዋል።

ክልሉ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እና አምስት ብሔራዊ ፓርኮች ያሉበት፣በርካታ ባሕላዊ ዕሴቶች የሚስተዋሉበት በመሆኑ በሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍ ላይ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች ትልቅ አቅም ያለው ክልል ነው ያሉት አቶ ኃይለማርያም በቱሪዝም እና አስጎብኚነት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ በመምጣት ኢንቨስት እንዲያደርጉም ጥሪ አስተላልፈዋል።



## መቄዶንያ አንድ ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማሰባሰብ ጥሪ አቀረበ

### - የሚረዳቸውን ዜጎች ቁጥር ወደ 20 ሺህ ለማሳደግ እየሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፍው**

አዲስ አበባ፡- መቄዶንያ የበጎ አድራጎት ማኅበር የፊታችን እሁድ በዶንኪ ቲዩብ አማካኝነት በሚደረገው አንድ ሚሊዮን ዶላር ገቢ የማሰባሰብ መርሐግብር ዜጎች እንዲሳተፉ ጥሪ አቀረበ።

መቄዶንያ የበጎ አድራጎት ማኅበር መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ብንያም በለጠ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የፊታችን እሁድ በኮሚዲያን እሸቱ አማካኝነት በዶንኪ ቲዩብ ለሚደረገው የአንድ ሚሊዮን ዶላር ገቢ የማሰባሰብ ፕሮግራም በመላ ዓለም የሚገኙ ዜጎች እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል።

ማኅበሩ አዲስ አበባ አያት ፀበል መድኃኒዓለም አጠገብ በሚገኘው ግቢ ውስጥ ሦስት ሺህ 600 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ዘመናዊ ሕንፃ እየገነባ መሆኑን የጠቁሙት ዶክተር ብንያም፤ ሕንፃው ዘመናዊ ሆስፒታል፣ 15 ወለሎች፣ የ120 የመኪናዎች ማቆሚያ ስፍራ፣ አምስት ሺህ ሰው የሚይዝ አዳራሽ ያካተተ መሆኑን በመጥቀስ ለአካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞች ምቹ ሆኖ እየተገነባ ያለ ነው ብለዋል።

በሦስት ዓመት ውስጥ የሕንፃው ግንባታ 70 በመቶ የደረሰ ሲሆን በሀገሪቱ ከተሞች በጎዳና ላይ ወድቀው የሚገኙ በርካታ አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማንን ለመረዳት ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

ሕንፃው ከ900 በላይ መስኮቶችና ከ810 በላይ በሮች የሚያስፈልጉት ሲሆን በሮችንና መስኮቶችን ገጥሞ ለተገልጋዮች ግልጋሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር ያስፈልጋል ብለዋል። ከዚህ ውስጥ አንድ ሚሊዮን ዶላር የሚሆነውን የፊታችን እሁድ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት በዶንኪ ቲዩብ ለማስባሰብ መታሰቡን ገልጸዋል።

መቄዶንያ የበጎ አድራጎት ማኅበር ከሰባት ሺህ 500 በላይ ምንም ጧሪና ደጋፊ የሌላቸውን በተለይም ደግሞ እራሳቸውን ችለው መፀዳዳት፣ መመገብ እና መንቀሳቀስ የማይችሉ የአልጋ ቁራኛ ሆነው የሰው ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማንን ከወደቁበት ጎዳና በማንሳት እየረዳ ይገኛል።

በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ማዕከሉን በማስፋፋት አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማንን እየረዳ እንደሚገኝ የገለጹት ዶክተር ብንያም፤ በአዲስ አበባ አያት ፀበል ፊትለፊት፣ አዳማ፣ ሐረር ፣ጋምቤላ፣ ድሬዳዋ፣ ደሴና በመሳሰሉት አካባቢዎች ተረጂዎችን እያገለገለ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ምንም ዓይነት የውጪ ሀገር እርዳታ ሳይጠቀም በሀገር ውስጥ ብቻ ከሰባት ሺህ 500 በላይ ለሚሆኑ ዜጎዎች በቀን አንድ ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ወጪ በማውጣት እገዛ እያደረገ ነው ብለዋል።

የፊታችን እሁድ በሚደረገው የገቢ ማሰባሰብ ፕሮግራም በመላው ዓለም የሚገኙ ዜጎች እጃቸውን በመዘርጋት አረጋውያንንና የአዕምሮ ሕሙማንን ከጎዳና ለማንሳት የድርሻቸውን እንዲወጡም ጥሪ አቅርበዋል።

በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የተረጂዎችን ቁጥር ከሰባት ሺህ 500 ወደ 20 ሺህ ለማድረስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ቢንያም፤ በአንድ ዓመት ውስጥ በመዲናዋ አስር ቅርንጫፎችን ከፍቶ በርካቶችን እያገለገለ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

# የነዳጅ ግብይት ሙሉ በሙሉ በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ሊፈጸም ነው

**አዲሱ ገረመው**



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- የነዳጅ ግብይት ሙሉ በሙሉ በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ሊፈጸም እንደሆነ ተገለጸ። ሥርዓቱ ተግባራዊ ሲሆን መመሪያውን የማይተገብሩ ማደያዎች ከገበያ ውጭ እንደሚሆኑ ተጠቁሟል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴርና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የነዳጅ ግብይትን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ሥርዓት ለማድረግ ትግበራ የሚጀመርበትንና አጠቃላይ ሂደቱን በተመለከተ ትላንት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል። ነዳጅን በዲጂታል ግብይት መፈጸም የሚያስችል ዝግጅት መደረጉንና በቅርቡ የታለመለት ድጎማ ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ተሽከርካሪዎችና ማደያዎች ወደ ሲስተሙ እንደሚገቡ ተገልጿል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ በመግለጫው እንደተናገሩት፣ የነዳጅ ግብይት ሪፎርሙ ከተጀመረ ወዲህ ክፍያን በኤሌክትሮኒክስ ለመፈጸም በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። ውጤቶችም ተመዝግበዋል። ይህንኑ መሠረት በማድረግ የነዳጅ ግብይት ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ሥርዓት መፈጸም የሚያስችል አሠራር በቅርቡ ይጀመራል።

በታለመለት የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት 130 ሺህ ተሽከርካሪዎችና አንድ ሺህ 24 ማደያዎች ወደ ቴሌ ብር ግብይት ሥርዓት መግባታቸውን ሚኒስትሩ ጠቅሰው፤ መንግሥት ሰባት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ለድጎማ ወጪ ማድረጉንም ጠቁመዋል።

ቀጣይ ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል ሥርዓት ውስጥ ለመግባት ዝግጅት መደረጉንና ከተለያዩ ኩባንያዎች ጋር ስምምነት ላይ መደረሱን አንስተዋል። ሁሉም ተሽከርካሪዎችና ማደያዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል ግብይት እንደሚገቡ እና ሥርዓቱን የማይተገብሩ ማደያዎች ከገበያው ሊወጡ እንደሚችሉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የነዳጅ ዋጋ ከዓለም ገበያ አንጻር ዝቅተኛ መሆኑ፣ ኮንትሮባንድ መስፋፋቱ፣ በተለያዩ ምክንያቶች የነዳጅ እጥረት መፈጠሩና በመንግሥት ላይ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ማስከተሉ የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት እንዲኖር ምክንያት መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሩ፤ በዚህም የነዳጅ ሪፎርሙ ተግባራዊ መደረጉንና በኑሮ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ ለማድረግ በሕዝብ ትራንስፖርት ላይ ድጎማው መቀጠሉን ጠቅሰዋል። ከጊዜ ሂደት በኋላ ሁሉም ከድጎማው ሊወጡ እንደሚችሉም አመላክተዋል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስትር ዶክተር ዓለሙ ስሜ በበኩላቸው፣ በትራንስፖርት ፖሊሲው ተደራሽ፣ የተቀናጀና የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ ሥርዓት ተዘርግቶ እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል።

የነዳጅ ዋጋ ተጽዕኖን ለመቋቋም፤ ኅብረተሰቡ በዋጋ እንዳይጎዳ የሕዝብ ትራንስፖርትን የመደገፍ፣ አማራጭ የታዳሽ ኃይል ተሽከርካሪዎችንና የብዙኃን ትራንስፖርትን የመጠቀም ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ እንዳለም ገልጸዋል።

ሀገሪቷ በየዓመቱ የሚያስፈልጋትን ነዳጅ በውድ ዋጋ እንደምትገዛና ይህም የውጭ ምንዛሪን በብዛት እንደሚወስድ የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ይህ ደግሞ ኅብረተሰቡ ላይ የኑሮ ውድነት ጫናን እንደሚያስከትል ጠቅሰዋል። በዚህም መንግሥት በትራንስፖርት ሴክተሩ የነዳጅ ዋጋን ተጽዕኖ ለመቋቋም ኅብረተሰቡ እንዳይጎዳ የሕዝብ ትራንስፖርትን እየደጎመ እንዳለ ተናገረዋል።

የክፍያ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ አለመሆን የድጎማ ሥርዓቱ ላይ ችግር መፍጠሩንና ለቁጥጥርም አስቸጋሪ መሆኑን በመግለጽ፤ ግልጽነትን ለመፍጠር፣ የመንግሥትን ወጪ ለመቆጣጠር፣ግዥን ዘመናዊ ለማድረግ ሁሉም ተሽከርካሪዎችና ማደያዎች ወደ ዲጂታል ግብይት እንደሚገቡ ሚኒስትሩ አመላክተዋል። ሥርዓቱ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊትም ሁሉም አካላት ለኤሌክትሮኒክስ ግብይቱ ዝግጅት እንዲያደርጉም አሳስበዋል።

# ወጪ ንግድንና ምርታማነትን ማሳደግ የዕዳ ጫናን ለማቃለል ያስችላል

## - የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች

**ፋንታነሽ ክንዴ**


ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ


አቶ ክቡር ገና

አዲስ አበባ፡- ወጪ ንግድን ማሳደግና ምርትና ምርታማነትን መጨመር ሀገራዊ የዕዳ ጫናን ለማቃለልና ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት የሚያሳካ መሆኑን የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ገለጹ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሀገራዊ የዕዳ ጫናው ካልተቃለለ ድሃ ተኮር የልማት ሥራዎችን ያስተጓጉላል። በመሆኑም ወጪ ንግድን ማሳደግና ምርትና ምርታማነትን መጨመርን ጨምሮ ሌሎችንም አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ሀገራዊ የዕዳ ጫናን ለማቃለል የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር ይገባል ።

እንደ ሀገር ያለንን እድል ሁሉ በመጠቀም እዳችንን በጊዜው መክፈል ካልቻልን አስቸጋሪ ችግር ውስጥ ልንገባ እንችላለን ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤መንግሥት በተለያዩ ዘርፎች የሚያደርጋቸውን ድጎማዎች ቀስ በቀስ ማንሳት፣ ለካፒታል ፕሮጀክቶች ሲወጡ የነበሩትን በጀቶች አስቸኳይ ካልሆኑ ማዘግየትም አንደኛው መፍትሔ መሆኑን አመላክተዋል።

ሀገራዊ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የውጪ ንግድን በማስፋፋት ዕዳችንን መክፈል ይኖርብናል የሚሉት ምሑሩ፤ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመቀነስ የንግድ ሚዛኑን በማስተካከል ዕዳችንን የመቀነስ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል ብለዋል።

አንድ አገር ላይ የዕዳ ጫናው እየጨመረ ሲመጣ የድህነት ቅነሳ ተግባራት ላይ ትልቅ እንቅፋት እንደሚፈጥር ጠቅሰው፤ አንዱ የድህነት ቅነሳ ተግባር ተደርጎ የሚወሰደው የተቀመጡ የሚሊኒየም ግቦችን ማሳካት ነው። በዚህ ግብ በተቀመጠው መሠረት ኢትዮጵያ ከ50 በመቶ በላይ ዕዳዋን ቀንሳለች ብለዋል።

በቀጣይነት የድህነት ቅነሳ ሥራዎችን ለማፋጠን እ.ኤ.አ በ2030 የሚያልቀውን የዘላቂ ልማት ግቦችን ማሟላት የሚቻልበትን መንገድ መፍጠር እንደሚገባ ጠቁመው፤ በመንግሥት በጀት፣ በዓለም የገንዘብ ድርጅት(አይኤም ኤፍ)ና በዓለም ባንክ እርዳታ ይህን ግብ ማሳካት ይቻላል ተብሎ አይታመንም። በመሆኑም የግል ዘርፉ ኢንቨስትመንትና በድህነት ቅነሳ ሥራዎች ውስጥ የሚኖረው ሚና ማሳደግ እንደሚያስፈልግም ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ የጀመረችው የእርሻ ልማት ሥራ ለድህነት ቅነሳ ሥራዎች ትልቅ አቅም የሚፈጥር በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ያሉት ምሑሩ ፤ የአፍሪካን ነጻ ንግድ ቀጠና እድሎችን በተገቢው መንገድ በመጠቀም ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበትን መንገድ መፈለግ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

የአገሪቱ ዕዳ ከውጭ በብድር የሚመጣና መንግሥት ከሀገር ውስጥ ባንኮች የሚበደራቸው መሆናቸውን የጠቀሱት ባለሙያው፤ ሀገራዊ እዳ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ችግር ስለሆነ ጂ 20 የሚባሉት የበለጸጉ አገሮች እገዛ ለማድረግና የታዳጊ አገሮች የውጭ እዳ የሚከፍሉበትን ጊዜ ለማራዘም ጥረት መኖሩን አመልክተዋል።

ሌላኛው የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ክቡር ገና በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ በተለይ የውጭ ሀገራዊ ዕዳን ለመክፈል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ያስፈልጋል።

ይህን ለማሳካት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ከሚልኩት ሀብት፣ ከብድርና እርዳታዎች ከሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ባለፈ በተጨማሪ የውጭ ንግድንና ቱሪዝምን በማሳደግ አገሪቱ የምታገኘውን ዶላር መጠን ማሳደግ የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

ከአበዳሪ ሀገራት ጋር በመነጋገር ብድሩ እንዲቀነስና የመክፈያ ጊዜው እንዲራዘም የተጀመረውን እንቅስቃሴ ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሀገራዊ ሰላምን በማረጋገጥ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንደሚገባም ገልጸዋል።

ከሀገራት ላይ ስምምነት በማድረግ የተማሩ ዜጎች በውጭ ሀገራት ሥራ ላይ እንዲሠማሩ ማድረግን ጨምሮ የውጭ ምንዛሪን ለማስገኘት የሚያስችሉ ተግባራት ላይም ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በመንግሥት በኩል የሚስተዋሉ የአሠራር ስልቶችን በማስተካከል የተፈጠረውን ዕድል በመጠቀም ምርቶችን ወደ አፍሪካ ገበያዎች በስፋት ማስገባት ሌላው መፍትሔ መሆኑን አስታውሰው፤ በኢንቨስትመትና በሌሎችም የንግድ ሥራዎች ለሚሠማሩ ዜጎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ አመላክተዋል።

ዜና

# በአማራ ክልል ከ10 ሚሊዮን በላይ መጽሐፍት ቢታተሙም የተሰራጨው 2 ነጥብ 7 ሚሊዮኑ ብቻ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከ10 ሚሊዮን በላይ የአዲሱ ሥርዓተ-ትምህርት መጽሐፍት ቢታተሙም በተለያዩ ችግሮች ሳቢያ ማሰራጨት የተቻለው 2 ነጥብ 7 ሚሊዮኑን ብቻ መሆኑን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ቢያዝን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ክልሉ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በአጠቃላይ 10 ሚሊዮን 33 ሺህ 366 ሚሊዮን የአዲሱ ሥርዓተ-ትምህርት መጽሐፍት አሳትሟል። ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች እስካሁን ማሰራጨት የተቻለው 2 ነጥብ 7 ሚሊዮኑን ብቻ ነው።

የታተሙት መጽሐፍት ቁጥርና የተሰራጨው ልዩነት የተፈጠረው እንደሀገር በተከሰተው የውጭ ምንዛሪ እጥረት በውጭ ሀገር የታተሙትን መጽሐፍት ማስገባት ባለመቻሉና በነበረው ወቅታዊ ሁኔታ ሳቢያ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፣ እስካሁን በውጭ ሀገር 8 ነጥብ 8 ሚሊዮን መጽሐፍት እንዲሁም አንድ ሚሊዮን 233 ሺህ 366 መጽሐፍት በሀገር ውስጥ አሳትሟል፣ ከዚህ ውስጥም ለየትምህርት ቤቶቹ ማዳረስ የተቻለው 2 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብቻ ነው።

በውጭ ሀገር ከታተመው ውስጥም ቢሮው ባገኘው የውጭ ምንዛሪ ወደ አንድ ሚሊዮን 425 ሺህ 502 መጽሐፍትን አምጥተን አሰራጭተናል ብለዋል።

የመጽሐፍ ሕትመት ዝግጅቱ በ2014 ዓ.ም መጠናቀቁን የጠቆሙት አቶ ጌታቸው፣ ለሕትመት የ500 ሚሊዮን ብር በጀት ተመድቦለት እንደነበር አመላክተዋል።

ለሕትመት ከተያዘው በጀት አኳያ በአጭር ጊዜ ችግሩን ለመፍታት ከባድ በመሆኑ መጽሐፍቱ ተደራሽ የሚሆኑበትን አማራጭ በመጠቀም ወደ ማሳተም ሂደት ተገብቶ ነበር ያሉት ኃላፊው፣ ያሉትን አማራጮች ተጠቅመን በሶፍት ኮፒ ለትምህርት ቤቶች በማዳረስ የመማር ማስተማር ሂደቱን አስቀጥለናል ብለዋል።

በእስካሁኑ ሂደት በመጀመሪያው ዙር በሀገር ውሰጥ 944 ሺህ 882 መጽሐፍትን አሳትመናል። በ2ኛው ዙር 288ሺህ 484 መጽሐፍትን አሳትመን ለትምህርት ቤቶች አከፋፍለናል ሲሉ ተናግረዋል።

ቀሪዎቹን መጽሐፍት ከታተሙበት ሀገር ለማምጣት ከ90 በመቶ በላይ ሥራዎች መጠናቀቃቸውን የተናገሩት ኃላፊው፣ የውጭ ምንዛሪው ተገኝቶ መጽሐፍቱን እንደመጡ ወደየትምህርት ቤቶች የሚሰራጩ ይሆናል ብለዋል።

# ለ20 ወራት የኤሌክትሪክ አገልግሎት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ማኅበረሰቡ ምሬትና እንግልት ውስጥ ነው ያለው ብለዋል። የሚመለከተው አካል ሁሉ ችግራችንን ተመልክቶ ጊዜ ሳይሰጠው አገልግሎቱን ማግኘት እንድንችል ሊደረግ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ሌላኛዋ የሐራ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ በላይነሽ ሲሳይ በበኩሏ፤ የመብራትና የውሀ አገልግሎት ለረጅም ጊዜ በመቋረጡ ችግር ውስጥ ነው ያለነው። በከተማዋ አቅራቢያ ምንም አይነት ውሃ ባለመኖሩ ምክንያት ከ15 ኪሎ ሜትር እስከ 20 ኪሎ ሜትር ተጉዘን ያልተጣራ ውሃ ነው እየተጠቀምን ያለነው ብላለች።

ከተለያዩ ቦታዎች በተሽከርካሪ ተጭኖ የሚመጣ አንድ ጀሪካን ውሃ ከ40 ብር በላይ ከፍለን ነው የምንገዛው፤ ይህ ደግሞ ለገንዘብ ኪሳራ እየዳረገን ነው ስትልም አክላለች። የሐራ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ መሀመድ ሰኢድ ኑር በበኩላቸው፤የተቋረጠው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማኅበረሰቡን ለበርካታ ችግር ዳርጎታል። ውሃ፣ወፍጮ እና ሌሎች ተያያዥ ፍላጎቶችን ለማሟላት ረጅም ኪሎ ሜትር ተጉዘው እንደሚያገኙ ተናግረዋል።

የተቋረጠው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከ15 ቀን በፊት የኃይል አገልግሎት የጀመረ ቢሆንም በከተማዋ ያሉት 11 ትራንስፎርመሮች በጦርነቱ፣ ረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ በመቆየታቸውና ውስጣቸው ያለው ዘይት በመዘረፉ ምክንያት 10 ትራንስፎርመሮች አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነ አብራርተዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ከሃይማኖት አባቶችና ሀገር ሽማግሌዎች ጋር በጋራ በመሆን ችግሩ እንዲፈታ ከዞን ጀምሮ እስከ ፌዴራል ተቋም ድረስ መጠየቃቸውን የጠቆሙት አቶ መሐመድ፤ እስካሁን ድረስ ችግሩ እንዳልተፈታና ከበፊቱ እንደባሰ ገልጸዋል።

ከተማዋ አዲስ እንደመሆኗ መጠን በርካታ ገቢዎችን መሰብሰብ የሚጠበቅባት መሆኑን ከንቲባው አንስተው፤ መብራት በመቋረጡ ምክንያት በርካታ ነጋዴዎች ከሥራ ወጪ በመሆናቸው እና ተቋማትም የሚጠበቅባቸውን ሥራ እየሠሩ ባለመሆኑ ገቢ መሰብሰብ እንዳልተቻለ ገልጸው ይህም ከተማዋ እንድትዳከም ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅዖ አለው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የዲስትሪቢዩሽን ሲስተም ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብዙወርቅ ደምሴ በበኩላቸው፤ ከፍተኛ የሆነ የትራንስፎርመር እጥረት ስላለ ለሕዝብ መገልገያ ተቋማት ቅድሚያ በመስጠት በተያዘው ሳምንት አገልግሎቱን ለማስጀመር በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ብዙወርቅ ገለጻ፣ ችግሩ ለመፍታት የትራንስፎርመር ምደባ የተደረገ ሲሆን፤ በቅርቡ የውሃ አገልግሎትና የጤና ተቋማት ላይ አገልግሎቱ እንዲጀምር ይደረጋል ብለዋል።

ካለው የትራንስፎርመር እጥረት የተነሳ በሐራ ከተማ ያሉትን 11ዱንም ትራንስፎርመሮች በአንድ ጊዜ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ አይቻልም ብለዋል። ከወልዲያ ዲስትሪክት ጋር በመነጋገር ቅድሚያ ለሕዝብ ተቋማት እንደሚሰጥ ገልጸዋል።

የሐራ ከተማን መብራት ወደነበረበት ለመመለስ በኛ አቅም ብቻ አይሠራም ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ የትራንስፎርመር አቅራቢዎችን አቅም የሚጠይቅ ነው። አቅራቢዎቹ ቅደም ተከተልና ኮንትራት የተሰጣቸው ቢሆንም የተበላሸውን ለይቶ እንዲሠራ ለማድረግ ጊዜ የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

በአካባቢው ያለው የኃይል አቅርቦት ችግር የተፈታ በመሆኑ የትራንስፎርመሮች ጥገና ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚችሉ ተናግረዋል።

# “ አፍሪካውያንን ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ድል ያደረገ ነው። የዓድዋ ድል አንድምታ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ነጭ ላልሆኑ ሕዝቦች ሁሉ ነው። ድሉ በወቅቱ ሁሉም ነጭ ያልሆነ ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ መጽናናት ያገኘበት ነው። ለአፍሪካውያን መነሳሳትና በኋላም ላደረጉት የነጻነት ትግል ሁሉ ከፍተኛ ምርኩዝ ሆኖ አገልግሏል።

ፓንአፍሪካኒዝምን ለማቀንቀን ኢትዮጵያኒስት መሆንን ይጠይቃል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ የኢትዮጵያን ፈተናዎች በሚገባ ገምግሞ ሁኔታውን ማስተካከልና ኢትዮጵያኒዝምን ማስፈን ያስፈልጋል። እየታዩ ያሉ ልዩነቶች በሰከነና በበሰለ መንገድ ሊታዩና ሊመረመሩ ይገባል። «የእኛ አርአያነት ከእኛ አልፎ ሌሎችን እንዲስብና በእኛ ዙሪያ እንዲሰለፉ እኛ ራሳችን ማግኘት አለብን። ብዙ የተፋለሱ ነገሮች አሉ፤ በአመራር ላይ ያለውም ሆነ ኃይልና ተሰሚነት አለኝ የሚለው ልሂቅ በምን ደረጃ እንዳለ፤ አገሪቱን ወደየት እየጎተትናት እንዳለ ልብ ብሎ ማጤንና መመልከት» ይገባናል ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ሹመት ገለጻ፤ አፍሪካን ነጻ ያወጣው የመጀመሪያው ትውልድ መሪዎች ከፍተኛውን አርአያነትና ተነሳሽነት አገኘን የሚሉት ከኢትዮጵያ ነው። እነ ጆሞ ኬንያታ፣ ከዋሚ ንኩሩማ፣ አዜኩዌና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ለነጻነት የበቃነው በኢትዮጵያ አርአያነት እንደሆነ ይገልጻሉ። ኢትዮጵያን የማይጠቅስ አንድም የአፍሪካ መሪ የለም። ለፖለቲካ ንቃታቸው መሠረቷ ኢትዮጵያ እንደሆነች ይናገራሉ። ስለዚህ ኢትዮጵያ ይህን ዓይነት ሚና እንድትጫወት መጀመሪያ ራሷን ማስተካከል ይኖርባታል። ብዙ ያልተስተካከሉ አስተሳሰቦችን ማስተካከል ይጠይቃል።

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ ዓድዋ ከኢትዮጵያውያን አልፎ የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ መሠረት እንዲሆን ለማድረግ የዓድዋን ድል የማጣጣል ትርክት ማስወገድ ያስፈልጋል። ድሉ ስኬታማና አንጸባራቂ የሆነ ስኬት ነው። ድሉን ለማኮሰስና የተለያየ ትርጉም የሚሰጡት ምንጫቸው ከየት እንደሆነ መመልከትና መለየት ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ በ1888 ዓድዋ ላይ ያስገኘችው ስኬት ለእነሱ ትልቅ የቅኝ ግዛት ዓላማ ከፍተኛ ተግዳሮት ነበር። የኢትዮጵያን ቀና ማለት በበጎ ያልተመለከቱት ብዙ የአውሮፓ የታሪክ ጸሐፊዎች ታሪኩን ለማጣጣል የተለያዩ ምክንያቶችን ለመፍጠር ሞክረዋል ሲሉም ጠቅሰዋል።

ዓድዋ ትልቅ ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ የታሪክ አንጓ መሆኑን ያስታወሱት የታሪክ ተመራማሪው፤ ኢትዮጵያውያን ሲተማመኑና በአንድ ላይ ሲሰለፉ በጋራ የተቀዳጁት ድል ምን ያህል ወደ ከፍታ እንደሚወስዳቸው ዓድዋ ምስክር ነው። ኢትዮጵያውያን በሚከፋፈሉበት ጊዜ የመከራና የሰቆቃ ታሪክ ይሆናል። ከዚህ የዘለለ ታሪክ አይኖርም። ዓድዋ በትብብር ኢትዮጵያውያንን የት እንዳደረሳቸው ምስክር ነው። ይህ ታሪክ የማይደገምበት ሁኔታ አይኖርም፤ ትልቁ መሠረት አንድነት በመሆኑ ይህን ማጠናከር ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

# እስራኤል በጤናው ዘርፍ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በቅርቡ ከእስራኤል የመጡ ሁለት የጤና ምሑራን የአመራር ችሎታንና ልሕቀትን ለማሳደግ «የጤና እንክብካቤ አመራር» በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ለሚገኙ 50 የሕክምና ዶክተሮች ልምዳቸውን አካፍለዋል።

በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አለልኝ አድማሱ እንደገለጹት፤ በእስራኤልና በኢትዮጵያ መካከል ጠንካራ ግንኙነቶች አለ። ይህን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር የኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ እንዲዘመን እስራኤል የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገች ነው።

ከሰሞኑን የዕውቀት ሽግግር እንዲኖር በማሰብ ሁለት የጤና ባለሙያዎች በእስራኤል ኤምባሲ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል ያሉት አምባሳደር አለልኝ፤ በጤናው ዘርፍ እስራኤል ያላትን ልምድ ለኢትዮጵያ በማካፈል ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በእስራኤል ያሉ የጤና ባለሙያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡና ኢትዮጵያውያን የጤና ባለሙያዎችም በእስራኤል ሀገር እንዲማሩ በማድረግ የኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ እንዲዘመን እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደር አለልኝ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ዘመናዊ የጤና ሥርዓት እንዲኖራት ከእስራኤል በኩል አስፈላጊው እገዛ እየተደረገ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በጤናው ዘርፍ አዲስ አበባን የአፍሪካ የጤና መስጫ ማዕከል እንድትሆን ከእስራኤል በኩል ጠንካራ ፍላጎት አለ። ልክ እንደ ዲፕሎማሲው በጤናውም ዘርፍ ለአፍሪካ መልስ መስጠት የምትችል እንድትሆን እስራኤል እገዛ ለማድረግ ዝግጁ መሆኗን ገልጸዋል።

የሁለቱን ሀገር የጋራ ትብብር በሁሉም ዘርፍ ለማሳደግ እየተሠራ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ በጤናው ዘርፍ ብዙ ልምድ ያላቸው እስራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ልምድ ያካፍላሉ፣ያስተምራሉ፣ የእውቀት ሽግግር ያደርጋሉ፣ ሕክምና ይሰጣሉ። እንዲሁም የተለያዩ እገዛዎችን እያደረጉ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ የጤና ባለሙያዎች እስራኤል በሚገኘው በአሱታ ሆስፒታል የትምህርት ዕድል አግኝተው ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ አገልግሎት እየሰጡ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ይህም ዘመናዊ እውቀትንና ልምድን ወደ ሀገራቸው ይዘው እንዲመለሱ እንዳስቻላቸው ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያን የጤና ዘርፍ ለማዘመን ብዙ ሥራዎች መሠራታቸውን ያነሱት አምባሳደሩ፤ በልብ ሕሙማን ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ከእስራኤል በኩል እገዛዎች አሉ፤ቀጣይነትም ይኖራቸዋል። በያዝነው ወር በርካታ የልብ ሕሙማን ሕጻናት ለሦስት ወር በእስራኤል ሀገር ያለምንም ወጭ ለሕክምና እንዲሄዱ ተደርጓል ብለዋል።

የአሱታ አሾዳድ ሆስፒታል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ኤረዝ ባረንቦይም በበኩላቸው፤ ባለፉት አምስት ዓመታት አዳዲስ የጤና ቴክኖሎጂዎችንና ዘዴዎችን በመትከል ላይ ነን። ይህን ለኢትዮጵያ ሆስፒታሎች በማካፈል ዘመናዊ ጤና ሥርዓት እንዲኖር እየሠራን ነው ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ የተማርነውን ትምህርት፣ የጤና ዘርፉን የእድገት ባሕልንና የምርምር ፈጠራን ለማካፈል ወደ ኢትዮጵያ መጥተናል። ይህን እውን ለማድረግ ከኢትዮጵያ በኩል አጋርነት እንፈልጋለን ብለዋል።

በኢትዮጵያ ከሚገኙ የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ጋር በትብብር መንገድ በጋራ ለመሥራት እንፈልጋለን ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለኢትዮጵያ ሕክምና ዘርፍ ልናካፍላቸው በምንችላቸው መስኮች ላይ እናተኩራለን ሲሉም ተናግረዋል።

የሕክምና ባለሙያዎችን እናሰለጥናለን። በተለይ በምርመራው ሆስፒታል ኢትዮጵያውን ባለሙያዎች ተምረው ወደ ሀገራቸው በመመለስ እንዲያገለግሉ እየተደረገ ነው። አሁንም በመማር ላይ ያሉ መኖራቸውን ገልጸዋል። የሁለቱን ሀገራት ዘላቂ ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር እንደሚጠቅም እምነት አለኝ ብለዋል።

ኢትዮጵያና እስራኤል በበርካታ ጉዳዮች ጠንካራ ግንኙነት እንዳላቸው የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ በጤናው ዘርፍም ግንኙነቱን ለማጠናከር በጋራ እየተሠራ ነው ብለዋል። እስራኤልም ያላትን እውቀት ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እያካፈለች እንደምትገኝ በማንሳት የኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ እንዲዘምን የተለያዩ እገዛዎች እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሄት



የ2015 ዓ.ም የተፋሰስ ሥራ ንቅናቄ ሁኔታ

ገጽ 17



«ድህነትን ለማሸነፍና አገራችንን በኢኮኖሚ ለመገንባት ልክ እንደዓድዋ ጀግኖች አንድ ሆነን መሥራት ይጠበቅብናል»

- አቶ ብርሃኑ ሞላ
የቀድሞ አየር ኃይል ማህበር መሥራችና ሊቀመንበር

ገጽ 6



በቴክኖሎጂው ዘርፍ አገርን ወደ ላቀ ደረጃ የማሻገር ግስጋሴ

ገጽ 13

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ለሚስተዋለው ሕገ ወጥነት የመፍትሔ ቁልፍ

**ሶሎሞን በየነ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመዲናዋ የሚስተዋለውን የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ልዩነት ለማጣጣም በተለይ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የተቀናጀ የቤቶች ልማት መርሐ ግብር ቀርጾ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባትና በማስተላለፍ ላይ ይገኛል።

ይሁን እንጂ በተለይ ቀደም ሲል የቤት ልማት፣ ማስተላለፍና ማስተዳደር ሥራው ለክትትልና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ባለመደራጀቱ የኅብረተሰቡን የቤት ፍላጎት ማርካት ካለመቻሉ ባሻገር በሕዝብ ገንዘብ የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የሕገወጦች መጠቀሚያ ሲሆኑ ተስተውሏል። ለአብነት ከዚህ ቀደም ከተማ አስተዳደሩ በጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ ባደረገው የፍተሻና የቁጥጥር ሥራ በሕገወጦች ተይዘው የነበሩ አምስት ሺ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ነጥቆ ለመምህራን በኪራይ እንዲተላለፉ በመቀጠልም ቤቱን በግዢ እንዲወስዱት መወሰኑ ይታወሳል። ከዚህ አኳያ በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ላይ የሚስተዋሉ ሕገወጥነትን በዘላቂነት ለመፍታትና ለመከላከል እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን በሚመለከት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ቶማስ ደበሌ የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው አሰናድተን አቅርበነዋል።

እንደ ኢንጅነር ቶማስ ገለጻ፤ ከተማ አስተዳደሩ ሰፊ የልማት ፍላጎት ያለበት ከተማ ነው። በዚህም በልማት የሚነሱ ሰዎች በዘላቂነትም ይሁን በጊዜያዊነት ወይም በኪራይ ቤት ያስፈልጋቸዋል። ከተማ አስተዳደሩ ይህን የቤት ፍላጎት የሚሸፈነው ደግሞ ኮርፖሬሽኑ በሚገነባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ነው። ስለዚህ



ኢንጅነር ቶማስ ደበሌ፤

ኮርፖሬሽኑ ገንብቶ በዕጣ ከሚያስተላልፋቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ከ10 እስከ 15 በመቶ ለልማት ተነሾች እና በልዩ ውሳኔ የሚተላለፉ መጠባበቂያ ቤቶችን ይያዛል።

ሆኖም በተለይ ከለውጡ በፊት የቤት ልማት፣ ማስተላለፍና ማስተዳደር ሥራው ለክትትልና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ባለመደራጀቱ እና አሠራሩ የተዝረከረከ በመሆኑ፤ ለመጠባበቂያ ተብለው ክፍት የተቀመጡ ቤቶችን ሰዎች ሰብረው በመግባት በሕገወጥ መንገድ ይይዛሉ። ምክንያቱም በዕጣ የተላለፉ እንዲሁም ለመጠባበቂያነት የተያዙ ክፍት ቤቶች ምን ያህል እንደሆኑ በግልጽ ለኅብረተሰቡ መረጃው አይገለጽም ነበር። በመሆኑም ከዚህ ቀደም በተለያየ ጊዜ ከተማ አስተዳደሩ ጋር በመቀናጀት በጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ በተደረገ የፍተሻና የቁጥጥር ሥራ ከአምስት ሺ በላይ በሕገወጦች ተይዘው የነበሩ ቤቶችን በመንጠቅ በሕጋዊ መንገድ ለልማት ተነሾችና ለመምህራን እንዲተላለፉ ተደርጓል።

ነገር ግን በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ለውጡ ከመጣ በኋላ አመራሩ ቁርጠኛ አቋም ይዞ የቤት ልማት፣ ማስተላለፍና ማስተዳደር ሥራው ለክትትልና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ በማደራጀት እየሠራ ይገኛል። በዚህም በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ላይ የሚስተዋለውን ሕገወጥነት ለመከላከል ከፍተኛ የቁጥጥርና የኦዲት ሥራ ይሠራል። ሆኖም አሁንም ቢሆን በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ላይ አልፎ አልፎ ሕገወጥ ተግባር ይስተዋላል።

ይህን በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ላይ የሚስተዋለውን ሕገወጥነት ለመከላከልና በሕገወጦች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሄዎች እየተተገበሩ ይገኛሉ። ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሄ ለመስጠት እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች አንዱ በአንድ ክፍለ ከተማ ላይ ምን ያህል የጋራ ቤቶች አሉ? የሚለውን ከክፍለ ከተሞች ጋር በቅንጅት የቤቶችን መረጃ የማናበብ ሥራ እየተሠራ ነው። ሌላው በቤቶች አስተዳደር ላይ የሚስተዋለውን ሕገወጥነት ለመከላከል ከከተማ አስተዳደሩ የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው። በዚህም ከወረዳ ጀምሮ እስከክፍለ ከተማ ድረስ ላሉ የሰላምና የጸጥታ አካላት ግንዛቤ ተፈጥሮላቸው ሕገወጥነቱን በቅንጅት የመከላከል ተግባር እየተከናወነ ነው። እንዲሁም ኅብረተሰቡ እራሱ የሕገወጥነቱ ምንጭና የመፍትሔው አካል ስለሆነ በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ላይ የሚስተዋለውን ሕገወጥነት እንዲከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል። ስለዚህ ኅብረተሰቡ ቤቶቹን በኔነት ስሜት እንዲጠብቅ እና እንዲቆጣጠር የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል።

ሌላው በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ላይ የሚስተዋለውን ሕገወጥነት በዘላቂነት ለመፍታት እና ቤቶች በሕገወጦች እንዳይያዙ ቤቶቹን ቆጥሮ መዝግቦ መያዝ ያስፈልጋል። ስለዚህ በቴክኖሎጂ ተደግፎ ሰዎች ጣልቃ ገብተው ሊሰርዙና ሊደልዙ በማይችሉበት መንገድ ሶፍትዌር አልምቶ በከተማ ደረጃ የመንግሥት ቤቶችና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምዝገባ እየተከናወነ ነው። በአዋጅ 74/14 መሠረት ቤቶችን የመመዝገብ ኃላፊነት የተሰጠው ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ነው። ነገር ግን ቤቶቹን ከማስተዳደር ጀምሮ መረጃቸው በኮርፖሬሽኑ እጅ የሚገኝ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ የምዝገባ ሥራውን ከቢሮው ጋር ተቀናጅቶ እየሠራ ይገኛል።

ስለዚህ በአሁኑ ወቅት የቤት ምዝገባ ሥራው በሁሉም ወይም በ11ዱም ክፍለ ከተሞች እየተከናወነ ይገኛል። ምዝገባው በግንባታ ላይ ያሉና ከዚህ ቀደም በዕጣ የተላለፉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባሻገር የንግድና የመኖሪያ የመንግሥት ቤቶችን ጭምር ስለሚያጠቃልል በጣም ሰፊና የተወሳሰበ ነው። ነገር ግን ችግሮችን ተጋፍጦ ቁርጠኛ አቋም ተይዞ የምዝገባ ሥራው እየተከናወነ ይገኛል። በዚህም ከ70 በመቶ በላይ የቤት ምዝገባ ሥራው ተከናውኗል። በመሆኑም ምዝገባው እስከ ሰኔ 30 ይጠናቀቃል። ምዝገባው ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ የለማው ሶፍትዌር ላይ የቤቶቹ መረጃ ስለሚሰፍር ምን ያህል ቤቶች አሉ? የትኛው ቤት ላይ ማን አለ? ምን ያህል ቤቶች ክፍት ናቸው? ወ.ዘ.ተ የሚሉ መረጃዎች ኦን ላይን ላይ እንደሀገር የቤቶች ቋት ላይ ማግኘት ይቻላል። ስለዚህ ሶፍትዌሩ ክፍት የሆነው ቤት ላይ ሰው ሲመደብ ወይም ቤቱ ሲሰጥ የቤቶቹን ቁጥር ስለሚከልስ ምን ያህል ቤቶች እንደተላለፉ እና ምን ያህል ቤቶች ክፍት እንዳሉ በየጊዜው መረጃውን በማደስ የቤቶቹን ትክክለኛ መረጃና ቁጥር መዝግቦ ያሳያል። ስለዚህ የቤት ምዝገባ ሥራው ሲጠናቀቅ በጥቅሉ የቤት አስተዳደር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመሠረታዊነት የሚቀርፍ እንደሆነ ኢንጂነር ቶማስ ይናገራሉ።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ድህነትን ለማሸነፍና አገራችንን በኢኮኖሚ ለመገንባት ልክ እንደዓድዋ ጀግኖች አንድ ሆነን መሥራት ይጠበቅብናል››

*- አቶ ብርሃኑ ሞላ*
*የቀድሞ አየር ኃይል ማህበር መሥራችና ሊቀመንበር*

ማህሌት አብዱል

አቶ ብርሃኑ ሞላ ከቀድሞው የአየር ኃይል አባላት አንዱ ናቸው ።የተወለዱት በአዲስ አበባ ከተማ ቢሆንም ያደጉትም ሆነ የተማሩት በአዳማ ከተማ ነው ።ከልጅነታቸው ጀምሮ አገራቸውን በውትድርና የማገልገል ፍላጎት ስለነበራቸው በ1970ዎቹ አጋማሽ በበረራ ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ሰልጥነው የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ተቀላቅለዋል ።በበረራ ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ከሰለጠኑ በኋላ በቀጥታ አየር ኃይሉን ተቀላቅለው በመላ አገሪቱ እየተዘዋወሩ አገልግለዋል ።በ1981ዓ.ም በአገሪቱ ተካሂዶ በነበረው መፈንቅለ መንግሥት ተሳትፈዋል የተባሉ በርካታ ጀነራሎች በወታደራዊ መንግሥቱ መገደላቸውን ተከትሎ አብዛኛው አባል ኩርፊያና ማጉረምረም ውስጥ ገባ ።ጥቂት የማይባለውም የሚያበረውን አውሮፕላን ይዞ እስከመጥፋት ድረስ በመንግሥት ላይ ያለውን ተቃውሞ አሰማ። አቶ ብርሃኑም መንግሥትን ተቃውመው አውሮፕላን ይዘው የመን ከተሰደዱት አባላት መካከል አንዱ ናቸው ።ለሁለት ዓመታት በየመን በስደት ከቆዩ በኋላም የአሜሪካ መንግሥትን ጥገኝነት ጠይቀው አሜሪካ ገብተዋል ።

አሜሪካ ቨርጂኒያ ግዛት በግል ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚኖሩት እኚሁ ሰው ከ30 ዓመታት በፊት የቀድሞ አየር ኃይል ማህበርን በማቋቋም በስደትና በአስቸጋሪ ሕይወት ውስጥ ያሉ አባላት የሚደገፉበት ሁኔታ ፈጥረዋል ።በተለይም በማህበሩ የነበረውን ሥርዓት ተቃውመው ከአገር የተሰደዱ አባላትን በመቀበልና ሕጋዊ የሆነ የጥገኝነት ሰነድና ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ረገድም የዛሬው የእኚህ ሰው ሚና የላቀ ነበር ።

የለውጡን መምጣት ተከትሎ የሚወዷትን አገር ዳግም ለማየት የቻሉት የዛሬው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ እንግዳችን በተለይም የለውጡ መንግሥት እየፈጠረ ባለው ምቹ ምህዳር በመደሰታቸው ይህ ሥርዓት ከዚህ በላይ ያብብ ዘንድ ለማገዝ ደጋግመው በመምጣት አጋርነታቸውን በተግባር አረጋግጠዋል ።አዲስ ዘመን ጋዜጣም ለ127ኛ ጊዜ ዘንድሮ የተከበረውን የዓድዋን የድል በዓል ምክንያት በማድረግ በዚህና በሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከቀድሞው አየር ኃይል ማህበር መሥራችና ሊቀመንበር አቶ ብርሃኑ ሞላ ጋር ውይይት አድርጓል ።እንደሚከተለው ቀርቧል ።

**አዲስ ዘመን፡- በመጀመሪያ እስቲ እንደአንድ የሰራዊቱ አባል የዓድዋ ድል ለእርስዎ ምን እንደሆነ ይግለፁልን?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** ዓድዋ ለሰራዊቱ አባላት ብቻ ሳይሆን ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ጥቁር ሕዝብ ክብር ነው። ዓድዋ አሁን ላለንበት ህልውና መሠረት የጣለ ሲሆን፣ በዚያ ጦርነት ዋጋ የከፈሉ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች ትልቅ ጀግንነትና ተምሳሌትነትን አስተምረው ነው ያለፉት። ዓድዋን ባሰብን ቁጥር ለነፃነት ሲባል የተከፈለውን የወገኖቻችንን የደም ዋጋ ነው የምናስታውሰው። እንደሚታወቀው እነዚያ የኢትዮጵያ ጀግኖች ለእናት አገራቸው በተዋደቁበት ሰዓት ልክ እንዳሁኑ ቴክኖሎጂ አልነበረም፤ ዘመናዊ መሣሪያና መረጃ መቀባበያ መንገድ በማይታሰብበት ወቅት በተቃራኒው ደግሞ በዘመናዊ ትጥቅ ታጥቆና ተደራጅቶ የመጣን ጠላት በጦር በጎራዴ ተዋግቶ አገርን ነፃ ያወጣበት፤ ብሎም ለአፍሪካም ሆነ ለመላው ጭቁን የዓለም ሕዝብ ከግፈኞች ቀንበር ነፃ መውጣት ጥርጊያ መንገድ ያበጃጀበት ነው ።

ዓድዋ በተለይ ለአፍሪካ ሕዝብ ትልቅ ኩራት ነው፤ በወቅቱ እንደሚታወቀው መላ አፍሪካውያን ከቀኝ ግዛት ቀንበር መላቀቅ የቻሉት ኢትዮጵያ የጣሊያንን ጦር ድባቅ ከመታችና ካሸነፈች በኋላ ነው ያ ድል የሞራል ስንቅ ሆኗቸው ለነፃነታቸው መታገል የጀመሩት ።ስለዚህ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውን ድል ብቻ አይደለም፤ የመላው ጥቁር

**ዓድዋ በተለይ ለአፍሪካ ሕዝብ ትልቅ ኩራት ነው፤ በወቅቱ እንደሚታወቀው መላ አፍሪካውያን ከቀኝ ግዛት ቀንበር መላቀቅ የቻሉት ኢትዮጵያ የጣሊያንን ጦር ድባቅ ከመታችና ካሸነፈች በኋላ ነው**



ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

ሕዝብ ነው ።ያ ድል ደግሞ እስካሁን የምንኮራበትና ወኔ ተላብሰን እንድንኖር ያደረገን ነው ።

እውነቱን ለመናገር በወቅቱ አፍሪካውያን ሳይቀሩ ኢትዮጵያ ታሸንፋለች ብለው አላሰቡም ነበር ።በመሠረቱ ብዙዎቹ የአፍሪካ አገራት ያለብዙ ችግር በቀጥታ ቅኝ መግዛት ስለቻሉ ኢትዮጵያ ሲመጡ በቀላሉ መውረርና መግዛት የሚችሉ መስሏቸው ነበር ።ግን የነበረው ምላሽ እንደጠበቁት ሳይሆን ቀርቶ ውርደትን ተከናንበው ነው የሄዱት ።ይህ ድል ለመላ አፍሪካ ትልቅ ተስፋ ሰጥቶ ነው ያለፈው ።በውጭ ያለን ኢትዮጵያውያንም በስደት አገር በኩራት አንገታችንን ቀና አድርገን መኖር የቻልነው በዓድዋ ምክንያት ነው ።አሁንም ያለው የኢትዮጵያ ሰራዊት በሚሰለፍበት የጦር ግንባር ሁሉ በጀግንነት እንዲያሸንፍ ያደረገው ዓድዋ ላይ የተፈፀመው ጀግንነትና የነበረውን ወኔ በመሰነቁ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- በሚኖሩባት አገር አሜሪካ ብዙ ጥቁር ሕዝቦች አሁንም በጭቆና ውስጥ ነው የሚኖሩት፤ ስመሆኑ ለእነዚህ ሕዝቦች በዓድዋ ስለተሠራው የጀግንነት ታሪክ በውል ማስተዋወቅ ተችሏል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** በመሠረቱ ስለዓድዋ የሚገባውን ያህል አስተዋውቀናል ብዬ አላስብም፤ ያም ቢሆን ግን በዚህ ዙሪያ ብዙ የታገሉ፣ መስዋዕትነት የከፈሉ፣ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ያጠፉ ብዙ ዲያስፖራዎች አሉ ።እንደተባለው ከዚህ ቀደም አሜሪካ ያለው ጥቁር ሕዝብ ስለዓድዋ እምብዛም አያውቅም ነበር፤ አሁን ግን የበለጠ እየታወቀና በዚያ ጊዜ የተሠራውን የጥቁር ጀግንነት ጀብዱ እንደምሳሌነት በመውሰድ ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ ።አንዳንዶቹም የመብት ታጋዮች ያንን የድል ታሪክ እየተጠቀሙበት ያለው ሌሎችን ለመቀስቀሻ እንደ አንድ ጥሩ መሣሪያ አድርገው ነው ።

ዓድዋንና የኢትዮጵያን ቅኝ አለመገዛት ለዓለም ሕዝብ በማስተዋወቅ ረገድ ፕሮፌሰር ኃይሌ ገሪማ በርካታ ሥራዎችን ሠርተወል ።የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት እኚሁ ሰው፣ በርካታ ፊልሞችን በመስራት ጭምር ታሪኩ ለትውልድ ተቀርፆ እንዲቀር በማድረግ ረገድ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም ።እኔ እንኳን ከዛሬ 24 ዓመት በፊት ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ በሊንከን ቴአትር ቤት እርሳቸው የሠሩት ፊልም ጥቁሩም ሆነ ነጩ ተሰልፎ ያየው እንደነበር አስታውሳለሁ ።ያ ፊልም ትልቅ ግንዛቤ ፈጥሯል ።ከዚያ በኋላም ሌላ ፊልም በመሥራት የኢትዮጵያን የጀግንነት ታሪክ እና ታላቅነት፤ ዓድዋ ምን ማለት እንደሆነ በአግባቡ እንዲታወቅ ያደረጉ በመሆናቸው ሊመሰገኑ ይገባል ።

በሌላ በኩል ከተወሰኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ‹‹ኢትዮጵያን ሄሪቴጅ ሶሳይቲ›› የሚባል ድርጅት አቋቁመን ነበር ።በዚያ ድርጅት አማካኝነት ለተወሰነ አመታት ባለንት አገር ሆነንም ዓድዋን እናከብር ነበር ።እኔም የዚያ ድርጅት ኮሚቴና ከመስራቾቹም አንዱ ነበርኩ ።የዚያ ድርጅት ዋነኛ አላማ አዲሱ ትውልድ ስለዓድዋ ድል በሚገባ ማወቅ አለበት የሚል ነው ።በበዓሉ ዕለት ትልቅ ዝግጅት በማዘጋጀትና ትልልቅ እንግዶችን ጋብዘን ታሪኩን እንዲያስተምሩ እናደርጋለን ።አሁን ያ ድርጅት ያለበትን ሁኔታ በትክክል ባላውቅም ለረጅም ዓመታት በየጊዜው የተለያዩ መርሃ-ግብሮችን እያዘጋጀ የበኩሉን ሚና ሲወጣ ቆይቷል ።ያም ቢሆን ዲያስፖራው በያለበት አገር የመላ ጥቁሮች ድል የሆነው ዓድዋንም ለማሳወቅ የራሱን ጥረት ያደርጋል ።ይህ ደግሞ አሁን የተጀመረ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ተደርጓል ።ግን ደግሞ የበለጠ መስራት ይጠበቅብናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስዓድዋ ድል ስኬት ዋነኛው ምስጢሮች ተብለው ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል ሕዝቡ ቋንቋ፣ ነገድና ሃይማኖት ሳይለየው መዝመቱ ነው ።በእርስዎ እምነት አሁን ያለው ትውልድ ከዚህ ምን ይማራል?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** እውነት ለመናገር ትክክለኛ የሆነ ኢትዮጵያዊነት የነበረው በዚያ ጊዜ ነው ብዬ ነው የማምነው ።አንቺም እንዳልሽው ብሔር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት ሳይለየው ሁሉም የመሪውን ጥሪ ተቀብሎና በአንድነት መትመሙ እጅግ አስደናቂና አኩሪ ታሪካችን ነው ። እናም ለዚህም ነው የዓድዋ ድል የአንድ ዘር ኀሳ አይደለም የምንለው ።ከዚያ ድል ብዙ ነገር መማር መቻል አለብን ብዬ አምናለሁ ።ምክንያቱም ከዚያ በኋላ ሁሉ ነገር እየሰለጠነ በመጣ ቁጥር መበታተንና መፈረካከስ ታይቶብናል ።አሁን ላይ እኮ አገርን የሚያክል ትልቅ የጋራ ጉዳያችንን ትተን ያበዛነው በጥቃቅን ነገር መቧቀሱና መቦጫጨቁን ነው ።እናም ይህንን ሳስታውስ በዚያ ዘመን የነበረው ኅብረተሰብ በኩሩ ኢትዮጵያዊነቱ አሁን ካለነው ሰዎች የበለጠ እንደነበር አስባለሁ ።

ምክንያቱም በአንድ ጥሪ ነው ያለምንም ማቅማማት ጓዜን ጨርቄን ሳይል የተመመው ።ሊያውም ደግሞ እንዲህ እንደአሁኑ መገናኛ ብዙኃን ሳይኖሩ በባህላዊ መንገድ የሰማው ላልሰማው አዳርሶ ነው በአንድ ድምፅ ከአራቱም አቅጣጫዎች ጥሪውን የተቀበለውና ዓድዋ ላይ የተገናኘው ።በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ላይ ከመጣው የጎጠኝነት በሽታ ጋር ሲታይ የዚያ ዘመን ኢትዮጵያውያን የምርም ቆራጦችና ጀግኖች ለአገራቸው ዋጋ የሚከፍሉ እንደነበሩ ያረጋግጥልናል ።ይህንን ስል አሁን ላይ አገሩን የሚወድ የለም ለማለት እንዳልሆነ ግን ግልፅ ሊሆን ይገባል። ግን ደግሞ አንድ ከሚያደርገን ይልቅ የሚያለያየንን ብቻ መርጠን ለአገራችን እድገት እንቅፋት መሆናችን ከምንም በላይ ሊያስቆጨን ይገባል ባይ ነኝ ።አስቀድሜ እንዳነሳሁት እነዚያ የዓድዋ ጀግኖች በቆራጥነታቸው፤ አይበገሬነታቸው፤ እንዲሁም ከጎጥ አጥር ወጥተው በኢትዮጵያዊነት ሥነ-ልቦና በመዋጋታቸው ነው ድል ሊያመጡ የቻሉት ።በመሠረቱ ጠላቶቻችን እንዲህ እንደአሁኑ በዘር ተከፋፍለን ቢያገኙን ኖሮ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ባልኖረች ነበር ።አሁንም ቢሆን በማንነትና በጎሳ መከፋፈል ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑን በተግባር አይተነዋል ።በአጠቃላይ በዚያ ወቅት ኢትዮጵያ ናት ያሸነፈችው፤ አሁንም ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ

## ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



ከከበበን የልዩነት እና የእኔ ብቻ ይታይ ከሚለው አስተሳሰብ ልንወጣ ይገባል የሚል እምነት ነው ያለኝ ።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ ጊዜ ድሉን የአንድ አካል ወይም ሕዝብ አድርጎ የማሰብ ችግር አለ። በመሠረቱ ይህ ዓይነቱ ግንዛቤ ከምን የመነጨ ነው ይላሉ?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** ይህ የጥቂት ግለሰቦች አስተሳሰብ ከጊዜ በኋላ የመጣ ነው ።ምንም ጊዜም ቢሆን በዘረኝነት ላይ የተዋጠ አስተሳሰብ ሲመጣ ያንን ድል የማኮሰስ ነገር ሊታይ ይችላል ።ግን ፈፅሞ ሊያጠፋው አይችልም ።እኔ እንደማምነው ዓድዋ የመላ ኢትዮጵያውያን ድል ነው ።ለአንዱ ብሔር ወይም ጎሳ የምንተወው አይደለም ።አስቀድሜ እንዳልኩት የዳግማዊ ምኒልክን ጥሪ ሰምቶ በጦርነቱ ላይ ያልተሳተፈ ብሔር ወይም ጎሳ እንዲሁም የእምነት ተከታይ የለም ።ሁሉም ከየአቅጣጫው ወጥቶ አገርን ከወራሪ ነፃ አድርጓል ።ስለዚህ ድሉ የሁላችንም ነው ።እርግጥ ነው ድሉን ወደአንድ ብሔር የምናስጠጋው ከሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የአገርንም ሆነ የድሉን ዝና ሊያበላሸው ይችላል ።

በዚያ የጦርነት አውድማ የተፈፀመውን ትክክለኛ ታሪክ ለትውልዱ በማውረስ ረገድ ሰፊ ክፍተት እንዳለብን አምናለሁ ።እንደሚታወቀው ታሪክን ከመጽሐፍ እና ከወላጆቻችን እናገኛለን ።ያንን ታሪክ በታሪክነቱ ተቀብለን እያሳደግነውና ለዓለም ማሳወቅ ሲገባን ከውስጡ ስንጥሮች እየመዘዝን የምንቀጥል ከሆነ በሌሎችም ጉዳዮች ላይ መስማማትም ሆነ መግባባት አንችልም ።አሁን ላይ በተወሰኑ ለአካላት ላይ የሚታየው ልዩነት በጊዜ ማስታረቅና ወደ ትክክለኛው መስመር መግባት ካልቻልን አሁንም የውጭ ጠላት ቢመጣ ልናሸንፍ አንችልም ።

ስለዚህ አሁንም የሚያስፈልገንና የሚጠቅመን አንድነታችን ነው ።ቀደም ሲል ጣሊያን ሲገባ በዘር ሊከፋፍለን ሞክሯል ።አንድነታችን ጠንካራ በመሆኑ ግን ሊያሸንፈን አልቻለም ።ለዚህ ደግሞ ጄነራል ጃጋማ ኬሎ በጻፉት መጽሐፍ ላይ እንደምንረዳው ጣሊያን እርሳቸው የተወለዱበት አካባቢ በመሄድ አባ ዶዮ የተባሉት የእሳቸው አጎት ጣሊያን ሰብስቦ አማራና ኦሮሞን ለማፋጀት ቅስቀሳ ሲያደርግ ተመልክተው የተናገሩት ጥሩ አስተማሪ ነው ብዬ አምናለሁ ።በወቅቱ እኚህ አባ ዶዮ የተባሉ ሰው ለሕዝቡ ነጭና ጥቁር ጤፍ አምጡልኝ ካሉ በኋላ ሁለቱን ደባለቁና ‹‹ከእነዚህ መካከል ጥቁርና ነጩን ለዩ›› ብለው ሕዝቡን መልሰው ጠየቁ ሕዝቡም ከባድ እንደሆነ ሲመልስላቸው ልክ እንደዚያ ሁሉ አማራና ኦሮሞን መለያየት ከባድ እንደሆነ ነው ምላሽ የሰጧቸው ።

በሌላ በኩልም ትውልድን ለማጥፋት ሆነ ብለው ታሪክን እያጣመሙ የሚፅፉ ሰዎች አሉ ። ግን ትክክለኛው ኢትዮጵያዊነት አንዱ በአንዱ ላይ የተገመደ ፈፅሞ ሊነጣጥሉት የማይችሉ መሆኑ ነው ።በዚያ ጊዜ የነበሩ ሰዎች አገር ማዳን ላይ ነው እንጂ ትኩረታቸው ጎሰኝነትን ማስፋፋት ላይ አልነበረም ።እርግጥ ነው ሁላችንም የመጣንበት ማንነት አለ፤ ይህንንም እንወደዋለን፤ ሆኖም ዋናችን አገር ናት ።አገር ስትኖር ነው ስለቋንቋም ሆነ ስለሌሎች ልዩነቶቻን ማውራት የምንችለው ።

**አዲስ ዘመን፡- አገራዊ አንድነትና ሕዝባዊ ህብረት ኢትዮጵያን እንደአገር አፅንቶ ለማቆየት ያለው ፋይዳ ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንደሚባለው ሁሉ ህብረታችንና አንድነታችን አገርን አፅንቶ ለማቆየት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ነገር ጠቃሚ ነው ።በተለይ በአሁኑ ሰዓት በመካከላችን የመግቢያ ቀዳዳ እያነፈነፉ ያሉና ኢትዮጵያን ለማፍረስ የቋመጡ ኃይሎች በዙሪያችን በበዙበት ወቅት አንድ መሆን ካልቻልን አደጋው የከፋ ነው የሚሆነው ።ድህነትን ለማሸነፍና አገራችን በኢኮኖሚ ለመገንባት ልክ እንደዓድዋ ጀግኖች አንድ ሆነን መሥራት ይጠበቅብናል ።አንዱ ሲሠራ ሌላው እያፈረሰ የሚኖርበት ሁኔታ ሊቆም ይገባል ።አሁን ላይ እውነተኛ እድገት ከተፈለገ ልዩነቶቻችን ወደ ጎን ትተን ህብረታችንን ማጠናከር ያስፈልገናል ።

በዚህ አጋጣሚ ጠላቶቻችንም የእኛን መከፋፈል ስለሚፈልጉት አይተኙልንም ።በነገራችን ላይ ጠላት ፊት ለፊት መጥቶ አይጋጨንም፤ እርስ በርስ እያባላን ነው መጠቀም የሚፈልገው ።ባለፈው ዓመት እንዳየነው እኛ እንድንፍረከረክ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሲደረግብን ነበር፤ ይህንን ተፅዕኖ ማሸነፍ የቻልነው ውጭ ያለነው ሆነ በአገር ውስጥ ያለው እንደአንድ ሰው በአንድነት በመጮህና ተባብሮ በመሥራቱ ነው ።ይህም ህብረት ድል እንደሚያመጣ ትልቅ ምሳሌ ነው ።እንደዚህ አሰፍስፈው ሊበትኑን የነበሩት ሁሉ አንገታቸውን ደፍተው ተመልሰው ተደራድረው አገራችን ሰላም መሆን ችላለች ።እናም ምንጊዜም ቢሆን ህብረት ከሌለ መፍረስ አይቀርም። ስለዚህ አንድ ሆነን ለአገራችን መቆም እንጂ እርስበርስ መባላታችንን የምቀጥል ከሆነ ጥፋቱ ቀላል አይሆንም ።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከአባቶቹ የተረከበውን የአገርን ህልውና በማስጠበቅ ረገድ የተጫወተውን ሚና እንደአንድ አባል እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** የኢትዮጵያ አየር ኃይል ታሪክ በዓለም ላይ ገናና እና የደመቀ ነው ።ከአፍሪካም ቀደምት የሚባል አየር ኃይል ሲሆን፣ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአህጉሪቱም ኩራት የሆነ ነው ።አየር ኃይሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በትጥቅም ሆነ በሰው ኃይል በአግባቡ የተደራጀ ሆኖ ብዙ ውጊያዎችን ሁሉ በድል ማጠናቀቅ የቻለ ሰራዊት ነው ።በተለይ ደግሞ ከሱማሊያ ጋር በነበረን ጦርነት ብቃቱን በሚገባ ያስመሰከረ ሲሆን፣ በተለያየ ጊዜ ጎረቤት አገሮች ችግር ሲያጋጥማቸው ድጋፍ በማድረግም አለኝታነቱን አረጋግጧል ።

በተለይ በውጊያ ብቃቱ ትልቅ የነበረ ከአፍሪካ ስመጥር ከሚባሉት አንዱ የነበረ፤ አገርን ያዳነ ኃይል ነው ።ይህንን ደግሞ አስቀድሜ እንዳነሳሁት በሱማሊያ ጦርነት ተፈጥኖ ብቃቱን በሚገባ አስመስክሯል ።በዚያ ጦርነት ላይ የታጠቀው መሳሪያ አነስተኛ እና ጊዜው የለውጥ ሰዓት በመሆኑ ከባድ ፈተና ገጥሞት ነበር ። ሆኖም በተቃራኒ ወገን ደግሞ ዘመናዊ የተባሉ አውሮፕላኖችን ነበር የያዙት።ግ ን ደግሞ የሕዝብ አንድነትና የአየር ኃይላችን በወኔና በስልጠና የማይታማ በመሆኑ ድል መቀዳጀት ችሎ ነበር ።የተቀዳጀው ድል በአየር ውጊያ በምሳሌ የሚጠቀሱ እነጄነራል ለገሰ ተፈራ ሚግ 21 የተባሉ ዘመናዊ አምስት የጠላት አውሮፕላኖች በአየር ላይ አመድ አድርገዋል። ይህ ሁኔታ የሱማሊያን ጦር ተስፋ ከማስቆረጡም ባሻገር እንዲያውም አንዳንዴ በእነሱ አየር ክልል እየተገባ ብዙ ውርደትን አሸክሟቸው ነው የተመለሰው፡፡

በነገራችን ላይ ለአንድ ተዋጊ ኃይል በሰላሙ ጊዜም ቢሆን ስልጠና እና ልምምድ በጣም ወሳኝ ነው። የእኛ አየር ኃይል በስልጠና ረገድ የሚታማ አልነበረም። በየጊዜውም ልምምድ ያደርግ ስለነበር እነኚህን ሁሉ ዘመናዊ አውሮፕላኖች በተወሰኑ አውሮፕላኖች ጥለው ተመልሰዋል ።በወቅቱ አየር ኃይላችን በማሸነፉ ምክንያት የእኛ አብራሪዎች ይይዙት የነበረው ኤፍ 5 አውሮፕላን በገበያ ላይ ከፍተኛ ተፈላጊነት እንዲኖረው አድርጓል። ያንን ያመጣው አየር ኃይል ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ስልጠና እና የውጊያ ብቃት በመኖሩ ነው ።

አየር ኃይሉን ለድል ካበቁት ጉዳዮች ዋነኛው ምስጢር ስልጠናውና ልምምዱ ነው ።በሰላሙ ጊዜ በአግባቡ የሰለጠ ከሆነ ለሚመጣ ማንኛውም ጦርነት አሸናፊ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም ።በዚያ ጊዜ በየአመቱ የሚቀጠረው ሰራዊት በቁጥር ከ300 ላይበልጥ ይችላል። ግን ስልጠናው ጠንካራ ነበር ።በሰላሙ ጊዜ ሳይሰለጥኑ ጦርነት መጣ ሲባል ብታሰልፊ ልምድ የሌለው ወታደር አሸናፊ ሊሆን አይችልም ።ከዚህ በተጨማሪም ወታደራዊ ዲሲፕሊኑ በጣም ጠንካራ መሆኑ ለድሉ ሌላው ምክንያት ነው ባይ ነኝ ።ምንጊዜም ቢሆን አንድ ሰራዊት ከዲሲፕሊኑ ጋር አብሮ የሚቀረፀው ከአገር ፍቅር ጋር ነው ።አገር ፍቅር የሌለው ጦር አሸናፊነቱም አጠራጣሪ ነው ።ማንኛውም የሰራዊት አባል አገሩን ሊወድ ይገባል ።

እውነት ለመናገር ለአገር ፍቅር እንጂ ለደመወዝ ብሎ ውትድርና የሚገባ የለም ።በመሠረቱ አገርን ለማገልገል እንጂ የረባ ደመወዝ የለውም ።በአጠቃላይ ስልጠናው፤ ዲሲፕሊኑ፤ በአገር ፍቅር የታነፀ መሆኑ ነው ለውጤት የሚበቃው ።እኔ በነበርኩበት ጊዜ ቅዳሜና እሁድ ሳንል ነበር የምናገለገለው፤ በትርፍ ሰዓት ስለሠራሁ ደመወዝ ይጨመርልኝ ማለት አይቻልም ።ያንን ሰራዊት ያቆየው የአገር ፍቅሩና ዲሲፕሊኑ ነው ።ምድር ጦሩ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነገር ነበር የሚታየው ።ለምሳሌ በፈንጂ የታጠረ ወረዳ ሲያጋጥም ከአገር ፍቅር የተነሳ ያንን ፈንጂ ላዩ ላይ አፈንድቶ ሌላው ጦር እንዲረማመድ ያደረጉ ብዙ ሰዎች አሉ ።ያንን ያህል አገር መውደድ ነበር ።

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ አሁን ያለውን ሰራዊትንም ሆነ አዲሱን ትውልድ እንዲህ ባለ የአገር ፍቅርና ዲሲፕሊን ለማነፅ መሥራት ይገባል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** ከሁሉ በላይ በትውልዱም ሆነ በሰራዊቱ ላይ መሠራት አለበት ብዬ የማምነው ከጎጠኝነት ይልቅ የአገር ፍቅር ስሜት እንዲኖረው ብዙ መሥራት ላይ ነው ። ምክንያቱም ደግሞ በታሪክ ባየንባቸው አገራት በሙሉ ጎጠኝነት ለማንም አላዋጣም፤ አልበጀምም ።ግን አንድ ሆነን አዲሱን ትውልድ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ካነፅነውና በጋራ ሠርተን ካሳየነው ብዙ ለውጥ ማምጣት እንችላለን ።ለዚህ ደግሞ ታሪክን በትክክል ማስተማር ወሳኝ ሚና አለው ብዬ አምናለሁ ።ምክንያቱም ደግሞ አስቀድሜ እንዳነሳሁልሽ መከፋፈሉ ጥፋት እንጂ ጥቅም አላመጣልንም ።በመሆኑም ተባብረን ከሠራን ጠላትን መሸነፍ ብቻ ሳይሆን ትልቁ ጠላታችንን የሆነው ድህነትን እናስወግዳለን ።ይህንን ዓይነት ትምህርት ለወጣቱ በሚገባ ከተሰጠው አስቀድሞ የነበሩት ዓይነት አገር ወዳድ ዜጎች ይፈጠራሉ ።አለበለዚያ ግን እንዲሁ በፍሬከርስኪ የምንቦጫጨቅ ከሆነ ጠላትም ሳይመጣ እርስበርሳችን ተባልተን እናልቃለን ።

**አዲስ ዘመን፡- ባለፉት አራት ዓመታት አየር ኃይሉ ወደቀድሞ ገናና ዝናው ለመመለስ እየተሠራ ያለውን ሥራ እንዴት ተመለከቱት? ምንስ ይቀራል?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** እኔ ከለውጡ በኋላ ስመጣ ለአምስተኛ ጊዜ ነው ።በመጣሁባቸው ጊዜያት ሁሉ አየር ኃይሉን የመጎብኘት አጋጣሚ አግኝቼ ስለነበር ለውጡ በሚገርም ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ስለመምጣቱ ታዝቤያለሁ ።ለውጡ እንደመጣ ያየሁት አየር ኃይልና አሁን ያለው ከፍተኛ ልዩነት አለው ።ያም ሲባል ባለፉት አራት ዓመታት ብዙ እድገት አሳይቷል ።የቀደሙት ሰዎች ጥለው የሄዱት የደከመ አየር ኃይል ነው ።ከጊቢው አቅም እንኳን ቆሻሻ የበዛበት፤ የጦር ካምፕ የማይመስል ነበር ።እናም ከለውጡ በኋላ ከሕንፃ ግንባታው ጀምሮ የትምህርት ሥርዓቱን ከማሻሻልና አጠቃላይ አየር ኃይሉን ዳግሞ እስከማዋቀር ድረስ የተሰራው ሥራ ጥሩ ውጤት ያየሁበት ነው ።ይህ ማለት ግን የሚፈለገው ደረጃ ደርሷል ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም ደግሞ ለ27 ዓመታት የወደመን ተቋም በአንድ ጊዜ መተካት የማይቻል በመሆኑ ነው ።

በአራት ዓመት ውስጥ ግን ከምጠብቀው በላይ ብዙ ለውጦችን አይቻለሁ ።የጎደሉትን ነገሮች ደግሞ በሂደት ያሟላል ብዬ እገምታለሁ ።ያሉት አመራሮችም ሰራዊቱንም ሆነ የቀደሙ አባላትን የሚቀበሉበት መንገድ ትህትና የተሞላው ነው ።በቀድሞ አየር ኃይል ተጀምረው የነበሩ ዴፖዎች ዛሬ ትልቅ መጠገኛ ሆነው የውጭ አውሮፕላኖችን አምጥቶ እስከመጠገን ደርሰዋል። ድሮ ራሺያና ሌሎች ቦታዎች ተልከው ይጠገኑ የነበሩ አውሮፕላኖች አገር ውስጥ መሠራት ጀምረዋል ።በዚህ ረገድ ትልቅ ውጤት እየታየ ነው ያለው ።ጊቢውን በማሳመር ረገድ የተሰራው ሥራ በጣም አስገራሚ ነው። ቆሻሻ ተሞልቶበትና ጥሻ ሆኖ የነበረው ያ አየር ኃይል አሁን የደብረዘይትን ሕዝብ በሙሉ ሊመግብ የሚችል ትልቅ የእርሻ ቦታ ሆኗል ።በጦሩ ብቃት፣ በስልጠና እና ዲሲፕሊን ረገድም ጥሩ ጅምሮች ነው ያሉት ።ወደነበረበት ክብርና ዝና ለመመለስ ግን የሚቀሩት ነገሮች አሉ፤ ይህንንም አሁን ያለው አመራር ያሳካዋል ብዬ አምናለሁ ።

**አዲስ ዘመን፡- ዲያስፖራው አንድነቱን አጠናክሮ ለአገሩ ዘብ ከመቆምና ለእድገቷ በመሥራት ረገድ ምን ይቀረዋል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** በዚህ ረገድ ከዲያስፖራው ብዙ ሥራ ነው የሚጠበቅብን ብዬ አምናለሁ ።በእርግጥ የእኛ ማህበርም ኃላፊነት አለበት፤ ሆኖም ከእኛ በላይ በተለይም የማህበረሰብ አንቂ የሆኑ የዲያስፖራ አባላት ከፍተኛውን የማስተባበርና የመቀስቀስ ሥራ ሊሠሩ ይገባል ብዬ አምናለሁ ።በተለይ ሁሉንም ሊያሳትፍና ኢትዮጵያዊነትን በተላበሰ መልኩ ዲያስፖራውን በአንድ ማሰባሰብና ለአገሩ በጋራ እንዲቆም ማድረግ ያስፈልጋል ።እንደቀድሞ ኢትዮጵያዊነት የሚሰበክ፤ የአገር አንድነት እንዲኖር ማድረግ ከተቻለ ማንኛውንም የውጭ ኃይል የማናሸንፍበት ምክንያት አይኖርም ።

ብዙ ጊዜ ዲያስፖራው የሚከፋፈለው በአገር ውስጥ ካለው ፖለቲካ ሁኔታ አንፃር ነው፤ እዚህ የሆነ ችግር ሲፈጠር እዚያ ሲደርስ ይጋነኑና መከፋፈልና ልዩነት እንዲፈጠር ያደርጋል ።አገር የሚለው ትልቁ ቁምነገር ይረሳና ወደተራ ነገር ውስጥ እንገባለን ።መንግሥት ይመጣል፤ ይሄዳል፤ ጥያቄው ያ አይደለም፤ ከሁሉ በላይ አገር ናት የምትቀድመው ።ተደጋግሞ እንደሚባለው በአገር ተስፋ አይቆረጥም፤ ዞሮ መግቢያችን አገራችን ናት፤ ከአገር ልንሸሽ አንችልም ።በዚህ ጉዳይ ላይ የማህበረሰብ አንቂዎች በተከታታይ ግንዛቤ ማስጨበጥና ዲያስፖራውን ማንቃት አለባቸው ።ይሁንና ጥቃቅን ነገሮችን እያነሳን ከአገር ጋር ካያያዝን አገር ላይ የሚያሳርፈው ጠባሳ የከፋ ነው የሚሆነው ።በመሆኑም በየአመቱ ሰልፍ እየወጣን ዓድዋን ከማክበር በዘለለ በዓድዋ ስለአገር የተከፈለውን ዋጋ በማሰብ አሁንም ቂምና ቁርሾ በመተው ስለአገር ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል ።ለአዲሱ ትውልድም ከአባቶቻችን የወረስነው ጀግንነትና የአገር ፍቅር ስሜትን ማስተማር አለብን ።

**አዲስ ዘመን፡- የአሁኑ ዘመን ዓድዋ ምን ሲሆን ይገባል ይላሉ?**

**አቶ ብርሃኑ፡-** ዓድዋን ለመድገም የግድ በጦርነት ብቻ መሆን የለበትም ።የጦርነት ታሪክ ከመጣም መልሰን ዓድዋን መድገም ያቅተናል ብዬ አላምንም ።ግን ደግሞ አሁን ያለብን ትልቁ ተግዳሮት ድህነት ነው፤ ከዚያ በተጨማሪ አገራዊ አንድነት መፍጠሩ ላይ ያሉብን ችግሮች ናቸው ።አስቀድሜ እንደገለፅኩት ያ ትውልድ ታጥቆ የመጣን ጠላት ማሸነፍ የቻለው አንድ ስለሆነ ነው፤ እኛም አሁን በልማቱም ሆነ በአገራዊ አንድነት አንድ ሆነን ኢትዮጵያዊነትን ሊያጎላና ሊያሳድግ በሚችል መልኩ ተባብረን መስራት አለብን ።ለዚህ ደግሞ ከምንም በላይ ልዩነታችንን አጥብበን አንድነታችንን ማስፋት መቻል አለብን ።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ብርሃኑ፡-** እኔም አመሰግናለሁ ።

# ማህደረ ጤና

## ኢንፌክሽንና የጤና መዘዙ

**እፀገነት አክሊሉ**

ኢንፌክሽኖች በሰውነት ውስጥ በማንኛውም ቦታ ሊጀምሩና በሰውነታችን በሙሉ ሊሰራጩ ይችላሉ፤ ኢንፌክሽን በሰውነት ውስጥ በሚከሰትበት ቦታ ላይ በመመርኮዝ ትኩሳትና ሌሎች የጤና ችግሮች ይከተላሉ። የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርዓት ጠንካራ በሚሆንበት ጊዜ ጀርሞችን በመዋጋት ኢንፌክሽንን ይቋቋማል። አንዳንድ የካንሰር ህክምናዎች በሽታ የመከላከል ስርዓትን ሊያዳክሙ ስለሚችሉ ይህ ሁኔታ ደግሞ ወደ ኢንፌክሽን ሊያመራ ይችላል።

ኢንፌክሽኑ እንዴት እንደሚሰራጭ እና በሰው አካል ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እንደ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን አይነት ሊለያይ ቢችልም ኢንፌክሽኖች ግን የሚያስከትሉት ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በቤተ ዛታ ሆስፒታል የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት የሆኑት ዶክተር ሄኖክ ዘውዱ በኢንፌክሽንና ተያይዘው ስለሚመጡ በሽታዎች ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

የሰውነት በሽታን የመከላከል ስርዓቱ በተላላፊ በሽታዎች ላይ ውጤታማ መከላከያ ቢሆንም በሽታ አምጪ ተህዋሲያን አንዳንድ ጊዜ የሰውነትን በሽታ የመከላከል ስርዓትን በማዳከም አቅምን ሊጠይቅ ይችላሉ። በዚህ ደረጃ ደግሞ ኢንፌክሽን ጎጂ ይሆናል።

አንዳንድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን እምብዛም ተጽእኖ አይኖራቸውም። ሌሎች ደግሞ በሰውነት ውስጥ አሉታዊ ምላሾችን የሚቀሰቅሱ መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ያመነጫሉ። የዚህ ልዩነት ደግሞ አንዳንድ ኢንፌክሽኖች ቀላል እና በቀላሉ የማይታዩ ሲያደርጋቸው ሌሎች ደግሞ ከባድ እና ለሕይወት አስጊ እንዲሆኑ አቅም ይፈጥርላቸዋል። አንዳንድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ህክምናንም ሊቋቋሙ ይችላሉ።

ኢንፌክሽን በሰውነት ውስጥ እንዲሰራጭ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ባክቴሪያዎች፣ ቫይረሶች፣ ፈንገሶች እና ጥገኛ ተውሳኮች የተለያዩ አይነት በሽታ አምጪ ተህዋስያን ይገኙበታል። እነሱ በተለያዩ መንገዶች ይለያያሉ ፣ ከእነዚህም መካከል መጠን፣ ቅርጽ፣ ተግባርና የጄኔቲክ ይዘት ይጠቀሳሉ።

ኢንፌክሽኖች በሰውነት ላይ እንዴት እንደሚሠሩ ለማወቅ የተለያዩ መንገዶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ቫይረሶች ከባክቴሪያ ያነሱ በመሆናቸው ወደ ሰውነት ገብተው ሴሎችን ይቆጣጠራሉ።

ጀርሞች የእለት ተእለት ህይወት አካል ሲሆኑ በአየር፣ በአፈር፣ በውሃና በሰውነታችን ውስጥ ይገኛሉ። አንዳንድ ጀርሞች ጠቃሚ የሚሆኑበት አጋጣሚ ያለ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ጎጂ ናቸው። ብዙ ጀርሞች በሰውነታችን ውስጥ እና በሰውነታችን ላይ ምንም ጉዳት ሳያስከትሉ ይኖራሉ እና አንዳንዶቹ ጤናማ እንድንሆን ይረዱናል። ኢንፌክሽኑን እንደሚያመጣ የሚታወቀው ጥቂት የጀርሞች ክፍል ብቻ ነው።

ኢንፌክሽን የሚከሰተው ጀርሞች ወደ ሰውነት ውስጥ ገብተው ቁጥራቸው ሲጨምር እና የሰውነት ምላሽ ሲፈጠር ሲሆን ጀርሞች ወደ ሰውነት ውስጥ የሚገቡበት መንገድ ያለው ተጋላጭ ሰው መተላለፍ፣ ጀርሞች ወደ ተጠቂው ሰው የሚዘዋወሩበት መንገድ ተላላፊ በሽታዎች ቫይራል፣ ባክቴሪያ፣ ጥገኛ ወይም የፈንገስ በሽታዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ቫይረሶች ከሴሎች በጣም ያነሱ ናቸው እና በራሳቸው ለመራባት ምንም መንገድ የላቸውም። ወደ ሴሎች ውስጥ ገብተው የራሳቸውን ቅጂ ለመስራት የሴሎችን ማሽኖች ይጠቀማሉ። የባክቴሪያ ኢንፌክሽን ተህዋሲያን አንድ ሕዋስ ያላቸው ፍጥረታት ሲሆኑ መመሪያቸው በትንሽ ዲ ኤን ኤ ላይ የተፃፈ ነው። በሰውነታችን ውስጥ እና በቆዳችን ላይ ጨምሮ ባክቴሪያዎች በዙሪያችን አሉ። ብዙ ባክቴሪያዎች ምንም ጉዳት የላቸውም አልፎ ተርፎም ጠቃሚ የሚሆኑበት ጊዜ አለ። ነገር ግን አንዳንድ ባክቴሪያዎች ሰዎች ህመም ላይ እንዲወድቁ ሊያደርጉ የሚችሉ መርዞችን ይለቃሉ።

የፈንገስ በሽታዎች ልክ እንደ ባክቴሪያ ብዙ ዓይነቶች ሲሆኑ በሰውነት ውስጥ ይኖራሉ። ጎጂ የሆኑ ፈንገሶች በአፍ፣ በአፍንጫ ወይም በቆዳ ውስጥ ወደ ሰውነት ሊገቡ ይችላሉ።

ተላላፊ በሽታዎች በዓለም ዙሪያ በጣም የተለመዱ ናቸው፤ ነገር ግን አንዳንዶቹ ከሌሎቹ የበለጠ የተለመዱ ናቸው። ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ በየዓመቱ ከ5 ሰዎች ፣ዱ በኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ ይያዛል።

ማንኛውም ሰው ተላላፊ በሽታ ሊይዘው ይችላል። በሽታን የመከላከል አቅም ከተዳከመ ወይም አንዳንድ በጣም ተላላፊ በሽታዎች ወዳለባቸው አካባቢዎች ከተጓዙ የበለጠ አደጋ ሊያጋጥምዎት ይችላል።

የታፈነ ወይም የተዳከመ የበሽታ መቋቋም ስርዓት ያለባቸው፣ ለምሳሌ የካንሰር ህክምና የሚያገኙ፣ ከኤችአይቪ ጋር የሚኖሩ ወይም አንዳንድ መድሃኒቶች የሚወስዱ፣ ህጻናት ልጆች፣ እርጉዝ እናቶች እና ከ 60 ዓመት በላይ የሆኑ አዋቂ ሰዎች ፣ በተለመዱ ተላላፊ በሽታዎች ላይ ክትባት ያልወሰዱ፣ ጤና ባለሙያዎች፣ እንደ ወባና ሌሎች በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ለሚይዙ ትንኞች ሊጋለጡ ወደሚችሉበት ቦታ የሚጓዙ ሰዎች በኢንፌክሽን የመያዝ እድላቸው ከፍ ያለ ነው።

ተላላፊ በሽታዎች የሚከሰቱት ከውጭ ወደ ሰውነትዎ በሚገቡ የተለያዩ ወኪሎች ሲሆን እነዚህም ውስጥ ቫይረሶች፣ ባክቴሪያዎች፣ ፈንገሶች፣ ጥገኛ ተሕዋስያንና ሌሎችም ይገኙበታል።

ሕዋሳትዎ በወራሪው አካል ሲጎዱ ወይም ሲወድሙ እና የበሽታ መከላከያ ስርዓታችን ለኢንፌክሽኑ ምላሽ ሲሰጥ ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ።

ዶክተር ሄኖክ እንደሚሉት ኢንፌክሽን ማለት የበሽታ አምጪ ተዋህስያን ወይም ጀርም ብለን የምንጠራቸው ነገሮች ወደሰውነታችን ገብተው የሚያስከትሉት ጉዳት ማለት ነው። ኢንፌክሽኖች የተለያዩ መነሻዎች ያሏቸው ቢሆንም ዋነኞቹ ግን ወደሰውነታችን የሚገቡትና ሰውነታችን በአግባቡ ኃላፊነቱን እንዳይወጣ ስራውን የሚያስተጓጉሉት ጀርሞች ናቸው።

ጀርሞች ስንል ባክቴሪያዎች ፈንገሶች ፓራሳይቶችና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉት ዶክተር ሄኖክ፤ እነዚህ ኢንፌክሽን አምጪ ነገሮች መነሻቸው የተለያየ ሲሆን በተለይም ሰውነታችን ውስጥ ገብተው ወረው በሽታን ከማስከተላቸው ጋር በተያያዘ መከሰቻቸውም የቅርብ አካባቢያችን ሊሆን እንደሚችል ያብራራሉ።

ኢንፌክሽን መነሻ ምክንያቶቹ ይለያዩ እንጂ በሰውነታችን ውስጥ ከገቡ በኋላም ቢሆን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻችንን ሊያጠቃ የሚችል ነው፤ ለምሳሌ ለውጪው ችግር የተጋለጡ የሰውነት ክፍሎች እንደ ቆዳ፣ በጉንፋን አማካይነት የአየር መተላለፊያ ቱቦዎቻችን የበሽታ የመከላከል አቅማችን ሲወረድ ደግሞ የውስጥ አካላቶቻችንን እንደ ጉበት ጣፊያ መግል መያዝ ሊከሰቱ ይችላሉ።

እዚህ ላይ ግን ልብ ሊባል የሚገባው ነገር የሰዎች በሽታን የመከላከል አቅም የሚቀንሱ በርካታ ምክንያቶች አሉ፤ ከነዚህ መካከል ደግሞ የስኳር በሽታ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስና ሌሎችም አቅምን ሊያሳጡ ይችላሉ፤ እነዚህ ባሉበት ሁኔታ ደግሞ ጀርሞች ወደሰውነታችን ከገቡ ለኢንፌክሽን የመጋለጣችን መጠን እንዲጨምር ከመሆኑም በላይ ለተባባሰ ችግርም የመጋለጥ እድላችን ሰፊ ነው እንደ ዶክተር ሄኖክ ገለጻ።

ኢንፌክሽን መምጫው ጀርም ይሁን እንጂ የቆዳ ንክኪዎች የሰውነት ፈሳሾች እንደ ምራቅና ሌላም የሰዎችን አይነምድር መንካት የተበከለ ምግብና መጠጥ በመጠቀም በሽታ አምጪ ጀርሞችን የታቀፈ አየርን ወደውስጣችን መሳብ ሊሆን ይችላል ፤ በመሆኑም ኢንፌክሽኖች መምጫቸው ብዙ እንደሆነ ሁሉ ከሰው ወደሰውም ለመተላለፍ መንገዳቸው ብዙ ነው።

በአገራችን በጣም የተለመዱት የኢንፌክሽን አይነቶች የመተንፈሻ አካል ኢንፌክሽኖች ሲሆኑ፤ የሚቀሰቀሱበት ምክንያት እንደ ጉንፋን ሳይነስ ቶንሲልና ሌሎችም የተለመዱ ሲሆኑ በተጨማሪነት የተቅማጥ ህመመም ተከትሎ የሚመጣው የአንጀት ኢንፌክሽን ተጠቃሽ ነው ብለዋል።



ዶክተር ሄኖክ ዘውዱ

> **ኢንፌክሽን መምጫው ጀርም ይሁን እንጂ የቆዳ ንክኪዎች የሰውነት ፈሳሾች እንደ ምራቅና ሌላም የሰዎችን አይነምድር መንካት የተበከለ ምግብና መጠጥ በመጠቀም በሽታ አምጪ ጀርሞችን የታቀፈ አየርን ወደውስጣችን መሳብ ሊሆን ይችላል ፤ በመሆኑም ኢንፌክሽኖች መምጫቸው ብዙ እንደሆነ ሁሉ ከሰው ወደሰውም ለመተላለፍ መንገዳቸው ብዙ ነው ።**

እነዚህ የተለመዱ አይነት የኢንፌክሽን አይነቶች ጉዳታቸው ለተባባሰ ችግር የማጋለጣቸው መጠንም እንደ ሰው የሚለያይ ሲሆን፤ በተለይም ህጻናት በተለያዩ ህመሞች ምክንያት በሽታ የመከላከል አቅማቸው የተዳከሙ ሰዎች እንዲሁም አረጋውያንን በተፈጥሮ በሽታን መቋቋም የማይችሉ ሰዎች ላይ ጉዳታቸው የበረታ ይሆናል።

ለምሳሌ በቫይረሶች ምክንያት የሚመጣው የቶንሲል ህመም ብዙዎችን ለተባባሰ ችግር የሚዳርግ እየዳረገም ያለ የህመም አይነት ነው፤በተለይም እንደእኛ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ በባክቴሪያ ምክንያት የሚመጣው የቶንሲል ህመም በብዛት የሚስተዋል ሲሆን የሚያስከትለው ችግርም ሰፊ ነው።

ይህ የቶንሲል ህመም ደግሞ በተገቢው ሁኔታ ህክምና ካላገኘ መግል የመያዝ አካባቢውን ሁሉ የማወክ አልፎ ተርፎም መተንፈስ አለማስቻል ይስተዋልበታል። ባስ ሲልም ወደልብ የኩላሊት የመገጣጠሚያ የማጅራት ገትር የነርቭ ህመሞችን ያስከትላል።

በእኛ አገር የኑሮ ሁኔታችን ንጽህናን የመጠበቅ ግንዛቤያችን ብዙም ያደገ ባለመሆኑ በተለይም የቶንሲል ኢንፌክሽን በልጆችም ሆነ በአዋቂዎች ላይ በተደጋጋሚ የሚከሰት በሽታ ነው ያሉት ዶክተር ሄኖክ፤ ይህንን ህመም በአስፈላጊው ልክ መታከም ደግሞ የሚጠበቅ ነው።

ኢንፌክሽን በጣም ህጻናት በሆኑ በሽታ የመከላከል አቅማቸው እጅግ በደከመና በተለያዩ በሽታዎች ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ በአዛውንቶች እንዲሁም በተፈጥሮ በሽታን የመቋቋም አቅም በሌላቸው ሰዎች ላይ አቅማቸው የጠነከረ ነው። በደም ውስጥ ኢንፌክሽን ገባ ማለት ደግሞ ቀን ጠብቆ በመላው ሰውነት ላይ ይሰራጫል ይህ ሆነ ማለት ደግሞ ተሰራጭቶ ከሚሄድባቸው ቦታዎች መካከል አእምሮ ወይም የነርቭ ክፍል ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ ደግሞ በታማሚው ላይ ሰውነትን ለማዘዝ ከመቸገር ጀምሮ እንደ ማጅራት ገትር የኩላሊትና የልብ ህመም ሁሉ ሊያስከትል ይችላል ማለት ነው።

ኢንፌክሽኖችን ለመከላከል ትልቁ መደረግ የሚገባው ነገር በአግባቡ የግል ንጽህንን መጠበቅ፤ የምናበስለውን ምግብ በአግባቡ መስራት ለምግብ መስሪያነት የምንጠቀምባቸውን እቃዎች ንጽህናም በተገቢው ሁኔታ ማጽዳት ምግብ በሚቀመጥበት ወቅት በአግባቡና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መሆኑን ማረጋገጥ ከችግር የሚያድን ሲሆን ሌላውና ወሳኙ ነገር ደግሞ ክትባቶችን መከተብ ነው።

ሰዎች የተለያዩ ህመሞች ሲሰሟቸው ነው ወደህክምና የሚመጡት በዚህን ጊዜ ደግሞ አስፈላጊው የደምና ሌሎች ምርመራዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል ከዚህ በኋላ ኢንፌክሽኑ የትኛው የሰውነት ክፍላቸው ላይ ነው ያለው የሚለውን በአግባቡ ከተለየ በኋላ አስፈላጊውን ህክምናና መድሃኒት በመስጠት ግለሰቡ ካለበት ችግር እንዲያገግም ይሆናል።

ነገር ግን ህመም እየተሰማቸው ወደህክምና ተቋም የማይሄዱ ሰዎች ኢንፌክሽኑ በደማቸው ውስጥ ተሰራጭቶ መላ ሰውነታቸውን እንዲቆጣጠረው ከዛም አለፍ ሲል የተባባሰ የጤና ችግር ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ማንኛውም ሰው ምንም ዓይነት ህመም ሲሰማው በፍጥነት ወደህክምና ተቋም ቢሄድ መፍትሔው ቀላል መሆኑን ዶክተር ሄኖክ ያብራራሉ።

በሌላ በኩል ሰዎች አመመኝ በሚል ሰበብ ብቻ ተገቢውን ምርመራ ሳያደርጉ ምንም ዓይነት ጸረ ተዋህሲያን (አንቲባዮቲክ) መድሃኒቶችን መውሰድ የለባቸውም። ምክንያቱም ጸረ ተዋስያን (አንቲባዮቲክ) መድሃኒቶች ተደጋግመው በተወሰዱ መጠን የማዳን ሃይላቸው እየተዳከመ ከመምጣቱም በላይ አላስፈላጊ ችግር ውስጥም የሚያስገቡ በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከሁሉም በላይ ሰዎች ጤናማ ኑሮን መኖር ከፈለጉ የግልና የአካባቢን ንጽህና በአግባቡ መጠበቅ የግድና መሰረታዊ መሆኑን ዶክተር ሄኖክ መክረዋል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ድርቅ "የርሃብ ስንቅ" መሆኑ ይብቃ!

**የንባባችን መደላድል፤**

ድርቅ፡- በዝናብ መጥፋት ወይንም እጥረት መንስዔነት ለተራዘሙ ጊዜያት የሚፈጠር የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ነው ። ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የድርቅን ዐውዳዊ ትርጉምን ለመበየን የመዝገበ ቃላት ድጋፍ ወይንም የሳይንሳዊ ምርምሮች ትንታኔ እጅግም አስፈላጊዎቻችን አይደሉም ። ታሪካችን ራሱ በድርቅና በርሃብ ሰነዶች የታጨቀ መሆኑን ችላ ብለን ወደ ሌሎች ምንጮች ብናንጋጥጥ ትርፉ፤ "ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ሲሸከም ያነጋል" ይሉት ብጤ ይሆንብናል ።

"ቀና ብዬ ባየው ደመናው ቀለለኝ፣
እግዜሩን ሠፈራ ወሰዱት መሰለኝ ።
ግዴለም እግዜሩስ እንዳሻው ብለናል፣
መንግሥት ምነው ከፋ ድምጡ ከእኛ ርቋል ። "

በማለት በራሱ ጥበባዊ የግጥም ሥነ ቃል ለሚራቀቀው የሀገሬ ባለ ሀገር የባዕዳንን ቋንቋ እያደበላለቅን የሚከተለውን መሰል ፈረንጅኛ ትንታኔ ብንግተው እንደለመደው እንደ እሳት በሚፋጀው ትዝብቱ "ንቆን" ይገላምጠናል እንጂ "ጎሽ አበጃችሁ! ትምህርቱ ደግ ነው!" በማለት በእንቱፍቱፍታ አይመርቀንም ።

"ከመደበኛ ሥርጭት ያነሰ ዝናብ ሲከሰት የሚቲዮሮሎጂካል ድርቅ (A Meteorological Drought) ይባላል ። በዝናብ እጥረት ምክንያት የእርሻ መሬት የእርጥበት ችግር ሲገጥመው የግብርና (Agricultural Drought) ይሉት ዓይነት ድርቅ ይከሰታል ። ወንዞች፣ ሃይቆች፣ ኩሬዎችና ምንጮች በዝናብ መጥፋት ምክንያት ክው ብለው ሲደርቁ ደግሞ የውሃ እጥረት ድርቅ (Hydrological Drought) ይከሰታል" እያልን ለደጉና ለገራገሩ የሀገሬ አርሶ አደር የተራቀቀውንና አንዳንዴም ለባለሙያዎቹ ለራሳቸው በማይገባቸው "የተወሳሰበ የሳይንስ" ፍልስፍና ልንሸነግለው ብንሞክር ምላሹ፤ "ይብላኝ ለራሳችሁ! ለኔውስ ድርቅ የሕይወቴ አንዱ አካል ስለሆነ ምክንያቱን አውቀዋለሁ" እንደሚለን አይጠፋንም።

በኢትዮጵያ ዐውድ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የአንበጣ መንጋና የተምች ወረርሽኝ ተከስቶ የተዘራውን ሰብል እምሽክ አድርጎ እየበላ ድርቅ እንደሚያስከትል የውጭ "አጥኚ" ተብዬዎቹ ስለምን እንደሚዘሉት ለጊዜው ግልጽ አይደለም ። ይልቅስ ከሀገሬ ባይተዋር አርሶ አደር የተፈጥሮ ድርቅ ተጠቂ ጋር ልንግባባ የምንችለው ነፍሰ ሄሩ ባለቅኔያችን ጸጋዬ ገ/መድኅን የዚያን ምስኪን ወገናችንን ስሜትና የልቡን ትርታ በብዕሩ የገለጸበትን ውብ ግጥም አንብበንለት "እህ" ብንለው ልብ ተቀልብ ሆኖ በማድመጥ ብሶቱን እንደሚዘረግፍልን ጥርጥር የለውም ።

"እስቲ እናንተ ተናገሩ ተርባችሁ የምታውቁ፣
ከቸነፈር አምልጣችሁ ተርፋችሁ እንደው ሳታልቁ።
ትንፋሽ ቀርቷችሁ እንደሆን ያስችላችሁ እንደሆን ጥቂት፣
ቀጠሮ ይሰጣል እልቂት?
ስንት መዓለት? ስንት ሌሊት?
ጥንብ አንሳው ሳይወርድ በፊት፤ ሳይሞዠርጣችሁ ጥፍሩ፣
በጣረ-ሞት አክናፋቱ አንዣቦ በመቅሰፍት እግሩ፣
አንደበት ተርፏችሁ እንደሁ ሳትነግሩን ከምትቀሩ፣
ካስቻላችሁ ተናገሩ ።

[የእኔ ቢጤማ ምሁሩ የት ይገባዋል የርሃብ ምሥጢሩ] ።

ከባለ ሀገሩ መጻተኛ ጋር በዚህ ቋንቋ ስንግባባ ነው መደማመጥና መግባባት የምንችለው ።

"የርሃብ ስንቅ" ያልነውን ጥቂት እናፍታታ፤

አንድን ጉዳይ ቢያሻ ለማሳጠር፤ ካስፈለገም ለማስረዘም ሲፈለግ፤ "ስንቅና ማሕሌት እንደያዢው ነው" ይባላል ። የሀገሬ ብሂለኛ እውነቱን ተናግሯል ። ስንቅ፡- ዓይነቱ ቢለያይም ለመንገድ ወይንም ለረጂም ጉዞ ተዘጋጅቶ የሚያዝ የበሰለ ምግብ ነው ። "እጃቸው ያጠረ" መንገደኞች ቆሎ፣ በሶ፣ ድርቆሽ እና መሰል ቤት ያፈራውን ቋጥረው ለጉዞ ይነሳሉ ። ኑሮውና ማጀቱ ደምቆ የተባረከለት ወገን ደግሞ በቅቤ የወረዛ ጩኮ፣ በጨው የታሸ ቋንጣ፣ ቅባት የጠገበ ጭብጦ በስንቅ መያዢያ አገልግሉ ውስጥ በወግ በወጉ ሊሰደርለት ይችላል ። "ስንቅህን በአህያ፤ አምልህን በጉያ" እንዲሉም የጉዞ ዝግጅቱ የሚጀመረው የራስን ባህርይ በራስ ቤት ቆልፎ፣ የስንቅ ኮሮጆን በአግባቡ ሸክፎ ጉዞን መያያዝን የሚያመለክት ነው ።

"ርሃብ እንዴት የስንቅ ማዕረግ ሊሰጠው ይችላል?" ብሎ ለክርክር ለሚጣደፍ ተሟጋች "ሀገራዊ ታሪክህን ፈትሽ!" ብሎ አጭር መልስ መስጠት ይቻላል ። ቀዳሚዎቹ መንግሥታዊ ሥርዓቶቻችን "ትተውልን አልፈዋል ከምንላቸው በጎ አሻራዎች (ሌጋሲዎች) ጎን ለጎን" ርሃብንም አንደ በጎ ነገር ለተከታዩ ትውልድ "ቅርስና ውርስ" አድርገው ሲያቀባብሉ የኖሩት "እንደ ስንቅ እየቆጠሩ" ጭምር ይመስላል ።

የድርቅና የርሃብ፣ የጠኔና የቸነፈር ታሪካችን በዝርዝር የተሰነደባቸው የፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስትንና የሌሎች መሰል የታሪክ መጻሕፍትን ገጽ በገጽ ብንፈትሻቸው በየትኞቹም ሥርዓተ መንግሥታት ውስጥ ድርቅና ርሃብ ሳይከሰት እንዳልቀረ ማስተዋል አይገድም ።

"እከሌ በሚባለው የሀገራችን ንጉሥ/መሪ ዘመን ከዚህ ዓመት እስከዚህ ዓመት ድረስ የቆየ ድርቅ፣ ርሃብና ቸነፈር ተከስቶ ይህንን ያህል የሞት እልቂት አስከተለ፣ ይህንን ያህል ከብት ፈጀ፣ በእንቶኔ የአገዛዝ ዘመንም ተፈጥሮ ፊቷን በማጥቆር ተቀይማን በዚህን ያህል መጠን ዜጎቻችን ረገፉ፤ እንስሳት አለቁ ይህንን ያህል ሰውም አካባቢውን ለቆ ተሰደደ ወዘተ." በማለት በርካታ ታሪኮችን ማንበብ ይቻላል ።

ለምሳሌ፡- በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የርሃብ እልቂት ተከሰቶ ነበር ከሚለው የዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የስንክሳር ታሪክ ተነስተን፣ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት (1880 - 1883) ደርሶ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቦ እስከሚገኘው እጅግ ዘግናኝ የድርቅና የርሃብ ታሪክ እንተንትን በማለት የ"ጥቁሩን የርሃብና የቸነፈር መከራችንን" ገጾች ብንገልጥ ብዙ ታሪካዊ እድፋችንን ማስተዋል ይቻላል ።

የሩቅ ዘመኑን ታሪካዊ ትንተና ለጊዜው "በተከድኖ ይብሰል" ትዝብት አልፈን ዕድሜውን ያደለን ዜጎች በኖርንባቸው ያለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ ብቻ በድርቅና በርሃብ ምክንያት ምን ያህል የተፈጥሮ ቅጣት እንደደረሰብን በቃላትና በምስል እንዘክር ብንል በተመደበልን ዐምድ ብቻ ሳይሆን የዚህን አንጋፋ ሙሉ የጋዜጣ ገጾች የሚያጣብቡ መረጃዎችን መዘርገፍ ይቻላል ።

ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የሰማኒያኛ ዓመታቸውን ባከበሩ ማግሥት (1965/66 ዓ.ም) በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሰተው ድርቅና ርሃብ ምክንያት በደረሰው የወገን እልቂት መንስዔነት የሀገሪቱን ሕዝብ ከዳር ዳር ያነቃነቀና መዘዙም የከፋ አመጽ በማስነሳቱ በወቅቱ የታየውን ሥር ነቀል ለውጥ ማስከተሉ አይዘነጋም ። ይኸው የድርቅና የርሃብ መዘዝ ዋና ምክንያት ስለሆነም ንጉሡ ነገሥቱን ከዙፋን ላይ ገፍትሮ እንዴት እንደጣላቸው የምናስታውሰው የቅርብ ዘመን ክፉ ትዝታችን ነው ።

ንጉሡን ከመንበረ ሥልጣናቸው ያስወገደው የወታደራዊ የደርግ መንግሥትም "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲን (ኢሠፓ)" መሠረትኩ ብሎ ጮቤ በረገጠበት ማግሥት (1977 ዓ.ም) በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረው ድርቅና ርሃብ ምን ያህል ዜጎቻችንን ቀርጥፎ እንደበላ አንዘነጋም ።

ወያኔ/ኢህአዴግ "ከተሰነጣጠቀበት እንሽፍሽፍ" በኋላ እና "ከኤርትራ ወረራ በአሸናፊነት ተወጥቻለሁ" በማለት ባስተጋባበት ማግሥትም በሀገሪቱ ተከስቶ ለሌላ መራራ ልቅሶና ዋይታ ያበቃንንና አንገት ያስደፋንን የ1990 ዓ.ም መባቻ የድርቅና የርሃብ ክስተትም የሚዘነጋ አይደለም ።

ዛሬም "ከርሃብ የስንቅ አገልግላችን" ውስጥ አሳራችን ተዝቆና ታፍሶ ስላላለቀ እነሆ "ለመከራ የጣፈው ቢነግድ አይርፈው" ሆኖብን ስለ ልማትና እድገት እየደከምን ነው ብንልም የየዕለቱ ዜናና መርዷችን ድርቅና ርሃብ ሆኖ ዳግም አንገት አስደፍቶናል ። በቦረናና በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢ የተከሰተው የድርቅ አደጋ ለጊዜው እንደሚፈራው በሰዎች ነፍስ ላይ ያለመሰልጠኑ ተገልጾልናል ። ከሕዝቡ ነፍስና ሥጋ ጋር ቁርኝታቸው የጠበቀው እንስሳቶቻቸው ግን በየመስኩ ረግፈውና ተረፍርፈው ማየት በእምባ ሊገለጽ ከሚችለው በላይ በስሜት ላይ ታትሞ የሚቀር ክፉና መራር ታሪክ ነው ።

እርግጥ ነው እንኳንስ እኛን መሰል የተፈጥሮ ሀብታቸውን በአግባቡ መጠቀም ተስኗቸው የዑደት ጊዜውን ሳያዛንፍ ለድርቅ ለሚጠቁት ሀገራት ቀርቶ የዓለም ኢኮኖሚና የፖለቲካው ጡንቻ የሚገኘው በእኔ ጓዳ ነው እያለች "ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ" በማለት የምትዘምረው አሜሪካም ብትሆን ከድርቅ በላ ነፃ ሆና አታውቅም ። ከ1900 - 2014 በነበሩት 115 ዓመታት ውስጥ ብቻ 13 ታላላቅ የድርቅ ክስተቶችን ይህቺው "ታላቅ ተብዬ" ሀገር ማስተናገዷ በታሪኳ ውስጥ በግላጭ ተመዝግቦ ይገኛል ።

ቀረብ እንበል ካልንም "The 1930 Dust Bowl Drought" ተብሎ በታሪካቸው የተመዘገበው ከ1928 - 1942 የቆየው እጅግ የከፋው ድርቅ፤ ከ1949 - 1957 (The 1950s drought) በሚባል የሚታወቀው ድርቅ እና ከ1998 - 2014 የተፈተኑበት (The early 21st century drought) እያሉ የሚጠቅሱት ታሪካቸው ብዙ ዋጋ አስከፍሏቸዋል"

አሜሪካንን እየተገዳደረች ባለችው በሌላዋ ልዕለ ኃያል ሀገር በቻይናም እንዲሁ ከ1936 - 37 አምስት ሚሊዮን ዜጎቿን በሞት የነጠቀና ከሃምሳ ሚሊዮን በላይ የድርቅ ተፈናቃዮች የተመዘገቡበት "Sichuan famine" በመባል የሚጠቀሰውን የተፈጥሮ አደጋ ማስታወስ ይቻላል ። ከ1942 - 1943 እና ከ1959 - 1961 የቆዩት ሁለቱ የድርቅ ወቅቶች፣ የታይፉ ዐውሎ ነፋስና የተምች አደጋዎችም እንዲሁ ከ46 ሚሊዮን በላይ የሚገመቱ ዜጎች ህልፈተ ሕይወት የተመዘገበበት ጥቁር ታሪካቸው ነው ።

የእኛን የድርቅ አደጋ ከእነርሱ የሚለየው በተቻለ መጠን የሞት መጠን እንዲቀንስና ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎችም ዳግመኛ ሌላ ድርቅ እንዳያገረሽ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ዜጎቻቸውን የመታደግ ከፍተኛ ሥራዎች ይከናወናሉ ።

መቼም "እናቱ የሞተችበት ሕጻን ልቅሶ እናቱ ወንዝ በወረደች ሕጻን ይቀማል" እንዲሉ ሆኖ "ርሃብ" የሚለው ስያሜ ለድርቅም ለሰዓታት የምግብ እጦትም እኩል ስለምንገለገልበት እንጂ እውነታው ቢፈተሽ ቃሉ እንጂ ውጤቱ በእጅጉ የተለየ ነው ። ከላይ የጠቀስነው ገጣሚያችን እንዳለው፤

"ላልቀመሰው ለእኔ ብጤማ ትርጉሙ፣
የአንድ ፊደል ድምጽ ነው
ርሃብ የሚሉት ከነስሙ ።
እንጂማ የት አውቆት ጠባዩንማ፣
ብቻ ሲነገር ይሰማል ይህንን አንድ ፊደል ቃል ።
ቃሉማ ያው በዘልማድ ይነገራል ይለፈፋል፣
ይተረካል፣ ይዘከራል፣ ይደጋገማል ይተቻል ። "

እናስ ምን ይደረግ? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው። አንድም፡- ርሃባችን ወደ ትውልዶች "በቅርስነት" እንዳይተላለፍ መንግሥት የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል። በቦረናም ሆነ በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች "ለሦስት ዓመታት ይህል ዝናብ ስላልዘነበ ነው" ተብሎ ምክንያት ሲሰጥ "እናስ ሦስት ዓመት ሙሉ ዝናብ አለመዝነቡ እየታወቀ የየክልል መንግሥታትም ሆኑ የፌዴራሉ መንግሥት ምን ሲሰሩ ከረሙ?" ብለን በካርዳችን መንበር የሰጠናቸውን መሪዎች ብንሞግት ተገቢ ይመስለናል ። መልሱም ከሚመለከታቸው አካላት ለጠያቂው ሕዝብ በአግባቡ ሊገለጽ ይገባል እንጂ ተድበስብሶ ሊዘለል አይገባም ።

"ርሃቡ የሰው ሕይወት አልቀጠፈም" የሚለው ገለጻም ቢታረም ይበጅ ይመስለናል ። የሰው ሕይወት ባያልፍ እንኳን ለኑሯቸው ዋስትና የሆኑት እንስሳቶቻቸው እንደቅጠል ሲረግፉ የመከራው ተሸካሚዎች "እንስሳቶቹ ካለቁ እኔስ ኖሬ ምን እፈይዳለሁ አንደኛውን ሞት በስንት ጣዕሙ" ብለው ተስፋ እንደሚቆርጡና መኖርን እንደሚጠየፉ እንዴት ሊረሳ ይችላል ።

ማሳረጊያችን እንደተለመደው ለሕዝባችን አቤቱታ ማቅረብ ነው ። ምንም ተባለ ምን ድርቁ በወገኖቻችን ላይ ከፍ ያለ የመከራ ውርጅብኝ እያዘነበባቸው ስለሆነ የተጀመረው የትድግና ጥረት በመንግሥትም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ። መቼም እየታዘቡንም ቢሆን ከጎናችን የሚቆሙ ዓለም አቀፍ የተራድኦ ድርጅቶችም እጃቸውን ከመዘርጋት ችላ ስለማይሉ እነርሱንም የማስተባበሩ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ይገባ ይመስለናል ።

እንደ ልማድ የተጣባንን "ይህ መቼ ጠፋን፤ ነጋሪም ሆነ መካሪ አንፈልግም" ለሚለው የሹሞቻችን የመከራከሪያ አባዜ ለጊዜው ጆሮ ባለመስጠት ዜጎች ሁሉ የአቅማቸውን እንዲያደርጉ አደራ ከማስተላለፍ ልንቦዝን አይገባም ። ቀድመው ለተጉት አርአያ ሰብ ወገኖቻችን የአክብሮት ምሥጋናችንን ማድረሱንም አንዘነጋም ። በዚያም ተባለ በዚህ ጩኸታችን "ድርቅ የትውልዶች ተወራራሽ የርሃብ ቅርስ እንደሆነ የመታሰቡ ምዕራፍ ተዘግቶ መከራችን ያብቃ" የማጠቃለያ መልእክታችን ነው ። ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ ።

# ተናጋሪው ዶሴ

# የስፍቶ አዳሪዋ አሳዛኝ መጨረሻ

አስመረት ብስራት



በጠዋት የሚጀምረው ኳኳታ እንደወፎቹ ዝማሬ ከእንቅልፉ ማልዶ ይቀሰቅሳታል። ለማኝ ምን ሲያደርግ..... በሚባልበት ሰዓት ተነስተው በውደቀት የሚገቡት የሱማሌ ተራ ሰፈር ነዋሪዎች እንቅልፍ ያላቸው አይመስሉም። ነጋዴው፣ ሠራተኛው፣ ሌባና ቀማኛውም እኩል በሱማሌ ተራ መንገዶች ይርመሰመሳሉ። ሱነሜ አሕመድም ማልዶ ከቤቱ የወጣውን ሰው ለመመገብ እስከ እኩለ ሌሊት ያዘጋጀችውን ሳንቡሳና ፓስቲ ይዛ በመንገዱ ዳር ትቆማለች።

ያፈላችውን ሻይና ቡና በፔርሙዝ ይዛ፤በመጥበሻ ላይ በሚፈላ ዘይት ውስጥ ለመጥበስ ያዘጋጀችውን የሳንቡሳና የፓስቲ ሊጥ እያድቦለቦለች በፈገግታ አላፊ አግዳሚውን ትጋብዛለች። ማለዳ ላይ ቁርስ ለሚፈልገው ሰው በሙሉ ቁርስ አብልታ ስትጨርስ ደግሞ ለምሳ የሚሆኗትን ፈጣን ምግቦች ማዘጋጀት ትጀምራለች።

እርጥብ ፤ ዳቦ በአትክልትና ሌሎች ፈጣን በሱማሌ ተራ ጥድፊያ ውስጥ የሚሠሩትን ሠራተኞች መግቦ ወደ ሥራ የሚያስገባ ምግብን ታዘጋጃለች። ሰዓቱ እንደተጠናቀቀ ወደ የቤቱ ሊገባ የተዘጋጀው ሠራተኛ አፉ ላይ ጣል እያደረገ የሚያልፋቸውን ምግቦች እየሠራች ሙሉ ቀን በትጋት ታሳልፋለች። የእለቱ ሥራ ሲያበቃ ደግሞ ቤቷ ገብታ ለነገ የሚሆነውን ስታዘጋጅ እስከ እኩለ ሌሊት ታመሻለች። በዚህ ሁሉ ጥረት ውስጥ ነገን የተሻለ ለማድረግ ሕልሟን ሰንቃ የምትሠራው ሱነሜ አንድም ቀን የከፋ ነገር ይገጥመኛል ብላ አስባ አታውቅም ነበር።

## የሱኔሜ የሕይወት ጅማሬ

ከተወለደችበት ስልጤ አካባቢ አክስቷን ተከትላ አዲስ አበባ የገባችው በልጅነቷ ነበር። ከአክስቷ ጋር ስትኖርም ሥራ ከመሥራት ባለፈ ለትምህርትና ለሌላ ነገር ምንም ጊዜ አልነበራትም። እድሜዋ እየጨመረ ሲሄድ ዓረብ ሀገር ሄዳ የተወሰነ ጥሪት ለመያዝ ትታትር ጀመር። ለሁለት ዓመታት ብቻ እንደሠራች ያሳደገቻት አክስቷ በጠና መታመሟን ሰምታ ወደ ሀገር ቤት ተመለሰች።

አክስቷ ምንም ልጅ ያልነበራት በመሆኑ እሷው አስታማ ሕይወቷ ሲያልፍ በወገ ማዕረግ ሸኘታለች። በመቀጠል የያዘቻትን ጥሪት በመያዘ አክሰቷ ትሠራው የነበረውን ሥራ በመሥራት ሕይወቷን ለመቀየር ትታትር ጀመር።

ከዓረብ ሀገር ስትመለስ የተለያዩ እንደ ቴሌቪዥን፣ ጂፓዝ ቴፕ እና የመሳሰሉ ኤሌክትሮኒክሶችን ጨምሮ በርካታ ነገ የትዳር ሕይወት ውስጥ ስገባ ያገለግሉኛል ያለቻቸውን እቃዎች ይዛ ተመለሰች። በርካታ ብርድ ልብሶች እና ያልጋ ልብሶች ቢኖሯትም ነገ የተሻለ ነገር ላይ ስሆን እለብሳቸዋለሁ ብላ በአሮጌው የአክስቷ አልጋ ላይ አሮጌ ብርድ ልብሷን ለብሳ ትተኛ ነበር።

ምንም አይነት ምቾት ሳትፈልግ ነገን ውብ ለማድረግ የምትታትረው ይህች ወጣት ሳይሠሩ የሚያድሩ፤ የሰውን በመቀማት የሚደሰቱ ግለሰቦች ዓይን ውስጥ ገባች። ሥራዋ ላይ ትኩረት አድርጋ የምትታትረው ሱነሜ አንድም ቀን ሰው እየተከታተለኝ ነው ብላ አስባ አታውቅም ነበር።

ዘወትር ከሥራ ወደ ቤት ከቤት ወደ ሥራ እንጂ ቀና ብላ ማንንም አታይም ነበር። በብዛት ብቻዋን ገባ ወጣ ማለቷ ክፋት በልባቸው ሰንቀው ለሚከታተሏት ወጣቶች የልብ ልብ እየሰጣቸው ነው። በየቀኑ ብቻዋን ያውም በጥድፊያ ወጣ ገባ የምትለዋን ወጣት አጥምዶ ለመጣል ምቹ ጊዜን መጠበቅ ጀመሩ።

## ቀማኞቹ

ቀማኞቹ ወንድወሰን ተስፋዬና በረከት በዛብህ ይባላሉ። በሱማሌ ተራ አካባቢ የመኪና አካል በመስረቅ የሚተዳደሩ ወጣቶች ናቸው። ከመኪና እስፖኪዮ እስከ ዝናብ መጥረጊያ ባስ ሲልም ጎማ እስከ መፍታት መኪናዋን ሙሉ ለሙሉ እስከማረድ የሚደርሱ ዓይነት ዓይን ያወጡ የሰው ንብረትን ፍለጋ የሚቅበዘበዙ ሌቦች ነበሩ።

ለሚሠሩት እኩይ ሥራ እንዲያመቻቸው ሦስት በመሆን እዛው ሱማሌ ተራ አካበቢ ተከራይተው ይኖሩ ነበር። በሂደት ከሰፈሩ ሰው ጋር መላመድ የአካባቢውንም ሰው የእለት ከእለት እንቀስቃሴ በመመልከት ከመኪና መለዋወጫ ስርቆት በተጨማሪ ኪስ ማውለቁንም ተያያዙት።

በዚህ መካከል ሱነሜ ዓረብ ሀገር ደርሳ እንደመጣችና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ይዛ መምጣቷን ሰሙ። ይሄን ጊዜ ይህች ወጣት ከማን ጋር እንደምትኖር፤ በስስት ያስቀመጠቻቸው ንብረቶቿ ምን ምን እንደሆኑ ማጥናት ጀመሩ። በአካባቢውም ሲያንጥብቡ ለራሷ መጠቀም ሰስታ ነገዬን ውብ አደርግባቸዋለሁ በማለት ከሻንጣና ከበርሜል ያላወጣቻቸው በስደት ያፈራችውን ንብረት ለመቀማት ቀን ቆረጡ።

## የጥፋት ቀጠሮ

የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ፒያሳ ሱማሌ ተራ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ነው። ወንድወሰንና በረከት ከሌላ አንድ ግብረ አበራቸው ጋር በመሆን ሱነሜ ቤቷ ገብታ ለነገ የሚሆናትን የምግብ ግብዓት አዘጋጅታ እስክትጨርስ አድፍጠው ይጠብቁ ጀመር። አንዱ ግብረ አበራቸው ደጅ እንዲቆም ካስጠነቀቁት በኋላ የዕለት ሥራዋን አጠናቃ ወደ መኝታዋ ለመሄድ እየተዘጋጀች የነበረችው ወጣት ላይ ፈጣን ጥቃት ያደርሳሉ። በሩ ገርበብ ብሎ መከፈቱንና አካባቢው ጭር ማለቱን የተመለከቱት ቀማኞቹ በሩን በሰፊው ከፍተው እንዳትጮህ ያዟት።

እነዚህ የክፋት መልዕክተኞች ሱነሜ አሕመድ ተከራይታ ከምትኖርበት የመኖሪያ ቤት ውስጥ በመግባት በላቧ ያፈራችውን ንብረት ለመውሰድ ወንደሰን አፏን በሻርፕ ጨርቅ አፍኖ ሲይዛት፣ በረከት ደግሞ በካርቶን ማሰሪያ ፕላስቲክ ገመድ የወጣቷን ሁለቱን እግሮች እና ታፋዋን እንዲሁም ሁለቱን እጆችዋ ወደ ኋላ በማድረግ በሻርፕ አስሮ ሕይወቷን እንዲያልፍ አደረገ። ባላሰበችው አጋጣሚ ጥቃት የደረሰባት ወጣት የእርዳታ ጥሪ ሳታሰማ እስከ ወዲያኛው አሸለበች።

ሕይወቷ ማለፉን ያረጋገጡት ቀማኞች በቤቱ ውስጥ የነበሩትን የሟች ንብረት የሆኑትን 32 ኢንች ቴሌቪዥን እና ሞባይል ከነሲም ካርዱ እንዲሁም ሌሎች ንብረቶችን ወስደው ከአካባቢው ሊሰወሩ ሲሉ አንድ የዓይን እማኝ ይመለከታቸዋል።

አይቷቸው ይጮሃል፤ በተሰማው ድምፅ መሠረት የፀጥታ ኃይሎች በቦታው ቢደርሱም ጩኸቱን የሰሙት ቀማኞች በፍጥነት ከቦታው በመሰወራቸው ሳያገኟቸው ይቀራሉ። የተፈጠረውን ለመመልከት ግን ወደ ወጣቷ መኖሪያ ቤት የገቡት ፖሊሶች በአሰቃቂ ሁኔታ ሕይወቷ ያለፈውን ሴት ተመለከቱ።

## የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ በቦታው ሲደርስ ወጣቷ ሕይወቷ አልፎ ንብረቷ ተዘርፎ ይመለከታል። ይህን የተመለከቱት የፀጥታ ኃይሎች ምርመራቸውን ይጀምራሉ። የድረሱልኝ ጥሪ ያሰማው የዓይን እማኝ በሰጠው ምልክት መሠረት ቀማኞቹ ወንደሰንና በረከት መሆናቸው ፍንጭ ሰጥቷል። የወጣቷ አስከሬንም ሲመረመር የተገኘው አሻራ የእነሱ መሆኑን ለማረጋገጥ በቁጥጥር ስር ለማዋል ፍለጋው ቀጠለ።

ወጣቶቹ ለቀናት ተደብቀው እንደልማዳቸው ወደ ስርቆት ሊመለሱ ሲሉ ክትትል ሲያደርግ የነበረው የምርመራ ቡድን በቁጥጥር ስር ያውላቸዋል። የተጠርጣሪዎቹም አሻራ ከሟች አስከሬን ላይ ከተገኘው ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ፤ ፖሊስ ምርመራውን አጠናቆ ወደ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በከባድ የውንብድና ወንጀል ክፍል ላከው።

## የፍርድ ቤት ክርክር

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በከባድ የውንብድና ወንጀል በመክሰስ ተከሳሾቹ በጽኑ እስራት እንዲሁም ከማኅበራዊ መብቶች እንዲታገዱ ለማድረግ ፍርድ ቤት መከራከረ ጀመረ።

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው 1ኛ ወንድወሰን ተስፋዬ፣ 2ኛ በረከት በዛብህ የተባሉ ተከሳሾች የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ፒያሳ ሱማሌ ተራ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ሱነሜ አሕመድ ተከራይታ ከምትኖርበት የመኖሪያ ቤት ድረስ በመሄድ የሟች ንብረትን ለመውሰድ 1ኛ ተከሳሽ የሟችን አፏን በሻርፕ ጨርቅ አፍኖ ሲይዛት፣ 2ኛ ተከሳሽ በካርቶን ማሰሪያ ፕላስቲክ ገመድ የሟችን ሁለቱን እግሮች እና ታፋዋን እንዲሁም ሁለቱን እጆችዋ ወደ ኋላ በማድረግ በሻርፕ አስሮ ሕይወቷን እንዲያልፍ ካደረጉ በኋላ በቤቱ ውስጥ የነበሩትን የሟች ንብረት የሆኑትን 32 ኢንች ቴሌቪዥን እና ሞባይል ከነሲም ካርዱ የወሰዱ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት ከባድ ውንብድና ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ተከሳሾች ቀርበው የተከሰሱበት ክስ በችሎት ተነቦላቸው የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምንም ጥፋተኛም አይደለንም ያሉ ሲሆን፤ አቃቤ ሕግም ተከሳሾች ክደው የተከራከሩ በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አቅርቦ በክሱ መሠረት ያስረዳ በመሆኑ በቀረበባቸው ክስ መሠረት እንዲከላከሉ ቀጠሮ በተሰጣቸው መሠረት ተከሳሾች 6 የሰው ምስክር አቅርበው ቢያሰሙም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን በተገቢው ያላስተባበሉ በመሆኑ ተከሳሾች ይከላከሉ በተባለበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ናችሁ ብሏቸዋል፡፡

## ውሳኔ

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ጥር 15 ቀን 2015 ዓ.ም ባስቻለው ችሎት የቅጣት እርከኑን 38 ስር መነሻ ቅጣት በመያዝ፣ ሁለቱም ተከሳሾች የወንጀል ሪከርድ የሌለባቸውና ማኅበራዊ ተሳትፎ ያላቸው በመሆኑ፣ 2 የቅጣት ማቅለያዎች ተይዘውላቸው በእርከን 36 ስር በማሳረፍ ተከሳሽን ያርማል ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያስተምራል ያለውን በእያንዳንዳቸው ላይ በ20 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ እና እንዲሁም ተከሳሾች ከማኅበራዊ መብታቸው ለ4 ዓመት እንዲታገዱ ሲል ወስኖባቸዋል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# ጾም የስጋ ረሃብ ወይስ የነብስ ምግብ ?

**ተስፋ ፈሩ**

ሰሞኑን የተፈጠሩ ከጾም ጋር የተያያዙ ሁለት ክስተቶች ሲያነጋግሩን ከርመዋል።አንደኛው ጉዳይ ሞዛምቢካዊው ፓስተር እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ 40 ቀን ለመጾም ሲሞክር በ25ኛ ቀኑ ሞቶ መገኘቱ ነው።ሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን የሚጾሙትን አብይ ጾም መግቢያ በማስመልከት "የቅበላ ኮንሰርት" አዘጋጅተናል ያሉ የምሽት ጭፈራ ቤቶች ጉዳይ ነው።ሁለቱ ክስተቶች ጾም የስጋ ረሃብ ነው ወይስ የነብስ ምግብ የሚል ጥያቄ እንዳነሳ አድርገውኛል።

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ አቡነ ሺኖዳ ሦስተኛ "The Spiritual of Fasting" (የጾም መንፈሳዊነት) በሚል ርዕስ ያሳተሙት መጽሐፍ መንፈስ ይህን ጽሁፍ እንደተጫነው አስቀድሜ መናዘዝ እፈልጋለሁ።እነዚህን ሁለት ክስተቶች ለአደባባይ ያበቃቸው ስለጾም የተያዘ ትክክል ያልሆነ ግንዛቤ ይመስለኛል።ይህ ግንዛቤ ጾምን የስጋ የስቃይ መድረክ አድርጎ የሚወስድ ነው።ለሀገሩ ሊሰዋ ጦር ሜዳ ለሚወርድ ወታደር የሚደረግ ሽኝትን የሚያስንቅ ድግስና ኮንሰርት እየተዘጋጀ ያለው ለተወሰነ ጊዜ ረሃብን ሊጋፈጥ የተዘጋጀውን ስጋን ለማጽናናት ነው።ይህ በእውነት ያስተዛዝባል!

40 ቀን ለመጾም ሲሞክር በ25ኛ ቀኑ የሞተው ሰውም ጾምን የተረዳበት መንገድ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው።አቡነ ሺኖዳ ከላይ በጠቀስኩት መጽሀፋቸው፣ "ሰው ጠቢብ ወይም ብልህ ሊባል የሚችለው ራሱን መቆጣጠር ሲችልና የሆዱን አሰራር ሲጠብቅ ነው።ብልህ ሰውነቱን ልፍስፍስ እስኪሆን ድረስ አይመግበውም፤ የሚያስፈልገውን መጠን በማሳጣትም እጅግ አያኮማትረውም" ይላሉ። ይህ ሰው በህይወት ለመቆየት ያህል እንኳን የሚያስፈልገውን ጥቂት ምግብ ራሱን ከልክሎ ነው ስጋው እስከ መጨረሻው የተኮማተረው።በአጭሩ ብልህ ባለመሆኑ ተበልቷል።ይህ ጾምን የስጋ ረሀብ አድርጎ በመቁጠር የመጣ ውጤት ነው፡፡

ስለ ጾም የተያዘውን ይህን ታማሚ ግንዛቤ ሳይንስ እንኳን አይደግፈውም።ሳይንስ ጾም ጠቃሚ መሆኑን አረጋግጧል።ሳይንስና ሃይማኖት ከሚገናኙባቸው ጥቂት ድልድዮች አንዱ ጾም ነው።አንድ ሀኪምና የሃይማኖት አባት በእኩል ደረጃ ስለ ጾም ጠቀሜታ ሲናገሩ ሊደመጡ ይችላሉ።ሳይንስ ደግሞ ከመቼ ወዲህ ነው ጾምን መስበክ የጀመረው? የሚል አንባቢ አይጣፋም።ሳይንስ ለጾም የበኩሉን እውቅና ከሰጠ ሰነባብቷል።ለምሳሌ ሩሲያዊው ሳይንቲስት አሌክሲ ሶፍሪን (Alexi Soforin) ከ92 አመታት በፊት በጾም የሚከናወን ህክምና (ትሪትመንት ባይ ፋስቲንግ) በሚል ርዕስ አንድ መጽሃፍ ጽፏል።ሶፍሪን በዚህ መጽሐፉ ለረጅም ጊዜ ከምግብ ተከልክሎ መቆየት ብዛት ያላቸው በሽታዎችን እንደሚያክም ገልጿል።በጾም ወቅት ሰውነት በቂ ምግብ አለማግኘቱ የተከማቹ ስቦች እንዲቃጠሉ እንዲሁም የታመሙና ያመረቀዙ ጡንቻዎቻችን እንዲፍታቱና እንዲዝናኑ እድል እንደሚሰጥ ጠቅሷል።

በሃይማኖቶች ሰፈር ጾም ሳይንስ ከደረሰበት ጠቀሜታው በዘለለ ትልቅ መንፈሳዊ መሳሪያ ነው።ስለ ቡዲዝም፣ ብርሃማኒዝም፣ ኮንፊሺኒዝም እና ዮጋ የሚያነብ ሰው በጾም ስጋቸውን ለነብሳቸው በማስገዛት ነብሳቸው ሙሉ ለሙሉ የበላይ እንድትሆን ማድረግ እንደሚችሉ ይገነዘባል።በታዋቂው የሃይማኖት መሪ ማህተመ ጋንዲ ህይወት ውስጥም ጾም ትልቅ ስፍራ ነበረው።ጋንዲ እጅግ ለረጅም ጊዜ ከመጾሙ የተነሳ በአንድ ወቅት ሀኪሞች ደሙ እንደ ወተት መበጣጠስ መጀመሩን ነግረውት ነበር።

ዮጋዎች በጾም አማካኝነት ጥቅም ላይ ይውል ያልነበረን ከፊል የሰውነታቸውን ኃይል ማግኘት እንደቻሉ ይናገራሉ።ይህ ኃይል ሰው ለሥጋው በሚያደርገው እንክብካቤ የሚሸሸግ በመሆኑ ከጾም በቀር በምንም መንገድ ሊገኝ እንደማይችል ያምናሉ።ሂንዱዎች ደግሞ በጾም ሥጋን ከነብስ የመለየት (ኒርቫና) ደረጃ ላይ ስለምንደርስ ከአምላካችን ጋር አንድ እንሆናለን የሚል እምነት አላቸው።እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ታዲያ ጥብቅ ምናኔ፣ ጾምና ከስጋዊ ነገሮች መከልከል ያስፈልጋል።

በሀገራችን ብዙ ተከታዮች ባሏቸው በክርስትና እና እስልምና ሃይማኖቶች ውስጥ ለጾም የሚሰጠው ቦታ ትልቅ ነው።በመጽሐፍ ቅዱስ በጊዜያዊው የስጋ ረሃብ ዘላለማዊዋ ነብስ እንደምትጠግብ ለማጠየቅ "እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁሐን ናችሁ ትጠግባላችሁና" (ሉቃ6፡21) ተብሎ ተጽፏል።በክርስትና እሳቤ ሰው በተራበ ጊዜ የሚያቀርበው ልመና (ጸሎት) ይበልጥ ተሰሚነት አለው።በመንፈሳዊነት የተሞላ ጸሎት በምግብ ከተሞላ ሰውነት ሊወጣ አይችልም።ሆድህ ምግብ ተሞልቶ ከምትጸልየው ሰዓታት ከሚወስድ ጸሎት ይልቅ በረሃብ ውስጥ ሆነህ የምታቀርበው የሁለት ደቂቃ ጸሎት ጥልቀት፣ ተሰሚነትና ተቀባይነት አለው።መነኩሳትና መንፈሳውያን አባቶች ሰው የህይወት ዘመኑን ዕኩሌታ የሰውነቱን ጡንቻ ለማዳበር አውሎ፣ ቀሪ ዘመኑን ደግሞ በሂደቱ በሰውነቱ የተከማቸውን ስብ ለማጥፋት መድከሙ እንደ ምን ያለ አሳዛኝ ነገር ነው ? ብለው ይጠይቃሉ።እነሱ ጾምን ለማያውቁት እንዲህ እያዘኑ በጾም ደስታን ያደርጋሉ እንጂ የስጋ ረሃብ አድርገው አያዩትም።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ወግሪስ እና ወቅሪስ፣ የውጪጭ ሀገር ሰዎች ደግሞ (Evagrios) እያሉ የሚጠሩት በአራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን በግብጽ ምድር የነበረ መናኒ የእርሱን መንፈሳዊ ተጋድሎና ልምምድ ለሚፈልጉ መናንያን ይጽፍ በነበረው መልዕክት፣ ጤነኛ ትሆን ዘንድ የምግብ ሸክምን አቅልል።የዛገ መስታወት ፊትን እንደሚያጠቁር ጥጋብም አስተዋዩን ያደነቁራል።ደካማ ሥጋህን አትራራለት።አንተ ከተንከባከብከው በአንተ ላይ በጠላትነት ይነሳብሃልና።የተለጎመ ፈረስ እንደሚታዘዝ ሥጋችንም ከገራነው ታዛዥ ይሆናል፤ ፈጽሞም አይናወጽም ይላል።

አቡነ ሺኖዳ ሦስተኛም እንደሚገልጹት፣ ጾም የስጋ ሥቃይ ወይም መስቀል አይደለም።ሥጋ ከነብስ ጋር የሚተባበርበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከፍ ከፍ የሚልበት እንጂ።የጾም ዓላማ ስጋን ማንገላታት ሳይሆን ጠባዩን መግራት ነው።ነብስ ከፍ ብላ ሥጋ ዳዙንና ሸክሙን አራግፎ አብሯት ከፍ እንዲል የምታደርግበት ነው።በጾም ወቅት ነብስና ስጋ በኅብረት መንፈሳዊ ተግባር ለመከወን ይነሳሉ።ስለዚህ ጾም የስጋ ረሃብ ሳይሆን የነብስ ምግብ ነው።

ለእስልምናም ጾም ከአራቱ የሃይማኖቱ መሰረቶች መካከል አንደኛው ነው።እስልምና መጾም የሚችል ሰው ከምግብ ከመከልከል ባለፈ ጾምን ከሚያበላሹ ነገሮች እንዲቆጠብ ግዴታ ይጥላል።የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት አስጠንቅቀዋል፣ ‹‹እኩይ ንግግሮችንና በእነርሱም መስራትን የማይተው ሰው፣ ምግቡንና መጠጡን በመተው አላህ ምንም ጉዳይ የለውም፡፡›› (ቡኻሪ 1804)።አንድ ሙሰሊም በተፈቀደለት ስጋዊ ስሜት ላይ ለተወሰኑ ሰዓታትና ቀናት ድልን ሲቀዳጅ የነፍሱ ንጉሥ ለመሆን ከመቻሉ ባሻገር ስሜቱን በአግባቡ ለመቆጣጠርና ስሜቱ ክልክል በሆኑ ስፍራዎች ላይ እንዳይውል ለመለጎም አቅም ይኖረዋል።

ከላይ ያነሳናቸው ሃይማኖታዊ እሳቤዎች በጾም አማካኝነት ነብስ ከስጋ ፍላጎቶችና ቁጥጥር ነጻ በመውጣት የተፈጥሮ እምቅ ኃይሏን እንደምታገኝ የሚያስረዱ ናቸው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን "ቅበላ" ተብሎ የሚጠራው፣ ጾም ከመግባቱ በፊት ቀደም ብሎ ያለው ቀን ወይም ሰሞን ነው።በቤተክርስቲያኗ ሥርዓትና ትውፊት መሰረት አጽዋማት አቀባባል የሚደረግላቸው በዋዜማው በሚቀርብ የጸሎት ስነ ስርዓት ፣ መዝሙርና ትምህርተ ወንጌል ነው። ቅበላን ለስጋ በመራራት ኮንሰርት በማዘጋጀት የሚደረግ ተድላና ደስታ ነብስን ምግቧን አሳጥቶ ለረሃብ የሚዳርጋት ዋጋ የሚያሳጣ ተግባር ነውና ሊወገዝ ይገባል።የነብስ ምግብ ስታርተር የስጋ ተድላ ሊሆን አይችልም።

## ዓለም አቀፍ



# አሜሪካ የአማጺ ቡድኑን መሪ ለመያዝ ለረዳ 5 ሚሊዮን ዶላር ልትሸልም ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካ በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የሚንቀሳቀሰው አማጺ ቡድን መሪን ለመያዝ የሚያስችል መረጃ በመስጠት ለተባበረ 5 ሚሊዮን ዶላር ሽልማት እሰጣለሁ ማለቷን ቢቢሲ ዘግቧል።

በአሜሪካ የሚፈለገው ሴካ ሙሳ ባሉኩ የተባለው ግለሰብ በምስራቅ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ በስፋት የሚንቀሳቀሰውን አላይድ ዴሞክራቲክ ፎርስ (ኤዲኤፍ) የተባለ ጽንፈኛ ቡድንን ይመራል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ይህ ከእስላሚክ ስቴት ቡድን ጋር ቁርኝነት ያለው ቡድን በርካታ ሰላማዊ ሰዎችን ገድሏል፤ የሰውነት አካልን ቆርጧል፣ አስገድዶ ደፍሯል እንዲሁም ሕጻናትን ጨምሮ በርካቶችን ጠልፎ ወስዷል ይላል።

በፈረንጆቹ 2021 ላይ አሜሪካ አላይድ ዴሞክራቲክ ፎርስ አሸባሪ ድርጅት ነው ስትል ፈርጃዋለች።

የኤዲኤፍ መሪው ሴካ ሙሳ ባሉኩ ትውልዱ ኡጋንዳ ሲሆን እአአ 1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ በትውልድ አገሩ ጥቃት ይሰነዝር ነበር።

የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቪኒ ሙስሊሞችን ይበድላሉ በማለት መንግሥት ላይ አንጃ አነስቶ የነበረው ቡድን ወደ ዴሞክራቲክ ኮንጎ ከተሻገረ በኋላ ጂሃዲስት በመሆን ሌላ ገጽታን ተላብሷል።

ቡድኑ ከሁለት አስርት ዓመታት በኋላ በኡጋንዳ ጦር ሽንፈት ከደረሰበት በኋላ ወደ ዴሞክራቲክ ኮንጎ ተሻግሮ ሰሜን ኪቩ ግዛት መሸጎ ይገኛል።

እአአ 2015 ላይ የቀድሞ የቡድኑ መሪ በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ አሁን በአሜሪካ የሚፈለገው ግለሰብ ጽንፈኛ ቡድኑን ላለፉት 8 ዓመታት ሲመራ ቆይቷል።

እንደ የተባበሩት መንግሥታት የስደኞች ከፍተኛ ኮሚሽን አሃዝ ከሆነ ሴካ ሙሳ ባሉኩ የሚመራው ቡድን ባለፉት ሁለት ዓመታት በተለይ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ዒላማ በማድረግ ከ200 በላይ ሰላማዊ ሰዎችን የገደለ ሲሆን ከ40ሺህ የማያንሱትን ደግሞ ከመኖሪያቸው አፈናቅሏል።

# ብሊንከን ከሩሲያው አቻቸው ጋር ፊት ለፊት ተገናኙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ከከፈተ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንተኒ ብሊንከን ከሩሲያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጂ ላቭሮቭ ጋር ፊት ለፊት መገናኘታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ሁለቱ ሚኒስትሮች በሕንድ ዋና ከተማ ደልሒ እየተካሄደ ባለው የቡድን 20 ሀገራት ስብሰባ ላይ ነው የተገናኙት።

ብሊንከን ከጦርነቱ ባለፈ ፖል ዌላን ስተለባለ ሩሲያ ውስጥ እሥር ላይ ስለሚገኝ አሜሪካዊም ተናግረዋል። አንድ ነባር የአሜሪካ ባለሥልጣን እንዳሉት ሁለቱ ግለሰቦች ደልሒ ላይ ያደረጉት ውይይት ከአስር ደቂቃ በታች የወሰደ ነው።

ባለሥልጣኑ እንደሚሉት የሩሲያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከአሜሪካው አቻቸው የቀረበባቸውን ወቀሳ ሲያጣጥሉ ነበር።

"ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ የነገርኳቸው ከዚህ ቀድም ለተባበሩት መንግሥታት ያልኩትንና የቡድን 20 ሀገራትም የሚጋሩት ነገር ነው። ወረራው ይቁም። ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ እንፍታው። ዘላቂ ሰላምና ፍትሕ ይስፈን" ሲሉ ብሊንከን ከውይይታቸው በኋላ ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

አልፎም ሩሲያ 'ስታርት' የተሰኘው የኒውክሌር መሣሪያ ስምምነት መልሳ እንድትፈርም ለሰርጌ እንደነገራቸው ገልጸዋል።

ሩሲያው ከዚህ ስምምነት ራሷን ማግለሏ "ኃላፊነት የጎደለው" ነው ብለዋል ብሊንከን።

የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ማርያ ዛካሮቫ ሁለቱ ባለሥልጣናት እንደተገናኙ ቢያረጋግጡም ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ተቆጥበዋል።

ሚኒስትር ብሊንከንና የሩሲያው አቻቸው ሰርጌ ላቭሮቭ ለመጨረሻ ጊዜ በአካል የተገናኙት ጥር 2022 ጀኔቫ ውስጥ ነበር።

ሐሙስ ዕለት የሩሲያው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ ምዕራባዊያን በዩክሬን ጦርነት ጉዳይ ከየትኛውም ወገን ያልሆኑ ሀገራት ሩሲያን እንዲቃወሙ ያስገድዳሉ ሲሉ ወቅሰዋል።

"የምዕራቡ ዓለም ሁሉንም ነገር መግፋት ይወዳል፤ እየገፋም ይገኛል" ብለዋል።

ሚኒስትር ላቭሮቭ ከአሜሪካው አቻቸው ጋር ስለነበራቸው ቆይታ ምንም ሹክ ባይሉም ውይይታቸው ዲፕሎማሲያዊ ድርድር እንዳልነበር መናገር ይቻላል።

ሚኒስትሩ፤ በቡድን 20 ሀገራት ስብሰባ ወቅት ምዕራባዊያን፤ ዩክሬን በጦርነቱ እንድትገፋ እያስገደዱ ነው ሲሉ ተደምጠዋል።

ብሊንከን፤ ከስብሰባው ጎንዮሽ ከተለያዩ ሃገራት ዲፕሎማቶች ጋር ለዩክሬን ድጋፍ ስለማሰባሰብ ውይይት አድርገዋል።

የዓለማችን 19 ሀብታም ሀገራትና የአውሮፓ ሕብረት የተካተቱበት የቡድን 20 ጥምረት 85 በመቶ የዓለም ምጣኔ ሀብትን ማንቀሳቀስ የሚችሉ ሀገራት ጥምረት ነው።

# ዓድዋ -የፓን አፍሪካኒዝም መነሻ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ በሰፊው ካስተዋወቁ ክስተቶች መካከል አንዱና ዋነኛው የአድዋ ድል ነው። የአድዋ ድል ከዚህም ያለፈ ታላቅ ፋይዳ አለው። የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ቀንዲል በሚልም ይጠራል። ድሉ ለነጻነታቸው የታገሉ ጥቁር ህዝቦች ነፃነታቸውን እውን ማድረግ እንዲችሉ ተነሳሽነት ፈጥሮላቸዋል። ለጥቁር ህዝቦች ሁሉ መኩሪያና መመኪያ የሆነው ይህ ታላቅ ድል፣ ለጥቁር ህዝቦች ነፃነትም አይነተኛ ሚና የነበረውና የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄን ማቀጣጠል ያስቻለ ክስተት እንደሆነም የታሪክ ምሁራን ያስረዳሉ።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪ እንዲሁም የገዳ ጥናት ተቋም ዳይሬክተር ዶክተር ረታ ዱጉማ፤ አውሮፓውያኑ አፍሪካን ለመቀራመት በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የትኛውን አፍሪካ አገር ማን ይውሰድ በሚል ተከፋፍለው እንደነበር በማስታወስ፣ ‹‹አብዛኞቹን የአፍሪካ አገራት በቅኝ ሲገዙ ኢትዮጵያን ግን አልቻሏትም›› ይላሉ። አውሮፓውያኑ እጅግ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎችንና የተደራጀ ወታደር ይዘው አፍሪካን በኃይል ለመቆጣጠር በመጡ ጊዜ አፍሪካውያን የገጠሟቸው በባህላዊ መሳሪያዎች እንደነበር ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ በወቅቱ ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረርና አገሪቷን ለመከፋፈል ሙከራ ባደረገ ጊዜ ህዝቡ በአንድነት ከጫፍ እስከጫፍ በነቂስ ወጥቷል። አገልጋዮች፣ ሴቶች፣ መኳንንቶችና መሳፍንቶች ሳይቀሩ ባደረጉት ተጋድሎም ድሉ የኢትዮጵያውያን መሆን ችሏል። ወቅቱ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገራት ተሸንፈው በቅኝ የተያዙበት እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር ረታ፤ ኢትዮጵያ ጣልያንን ድል የማድረጓ ዜና በተሰማ ጊዜ በአውሮፓውያኑ ዘንድ ከፍተኛ መደናገጥ ተፈጥሮ እንደነበር ያስታውሳሉ።

በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተጽዕኖ የተፈጠረባቸው ጣልያኖችም ‹‹ቪቫ ምኒልክ፤ ቪቫ ጣይቱ›› ‹‹በርታ ምኒልክ፤ በርቺ ጣይቱ›› ይሉ እንደነበርም ታሪክ ያመለክታል። ጣልያኖች ከአገራቸው ውጭ ሄደው በዘመናዊ መሳሪያና በተደራጀ ወታደር ባደረጉት ጦርነትና በደረሰባቸው ሽንፈት የተነሳ በወቅቱ በነበረው የጣልያን መንግሥት ላይ ትችት እንደቀረበበትም አስታውሰዋል።

በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና የስነቅርስ መምህር አቶ ሰለሞን ኪዳኔ ‹‹የአድዋ ድል በታሪክ ውስጥ ትልቅ የታሪክ እጥፋትን ፈጥሮ ያለፈ ነው›› ሲሉ ይገልጻሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ የአድዋ ድል ሁሌም የሚወሳ የጥቁር ህዝቦች የማንነት መገለጫ ነው። አውሮፓውያን በተለይም በ19ኛው ክፍለ ዘመን ለአፍሪካ የነበራቸው አመለካከትና አፍሪካን የሚስሉበት መንገድ እጅግ ዝቅ ያለ እንደነበር ጠቅሰው፣ ያ ዘመን አፍሪካን የጨለማው አህጉር በሚል የፈረጁበት ወቅት እንደነበር ያስታውሳሉ።

በዚያ ወቅት የተገኘው የአድዋ ድልም ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካውያን ትልቅ ብርሃን መሆን የቻለና በተለይም ቅኝ ገዢዎችን በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የከተተ ክስተት ነው ይላሉ። የአድዋ ድል የአፍሪካውያን የነጻነት ቀንዲል ነው የተባለውም በዚሁ ምክንያት መሆኑን በማስታወስ፤ ‹‹የአድዋ ድል የኢትዮጵያውያንን ስነልቦና ከመገንባት ባለፈ የቅኝ ግዛትን ተጽዕኖ በሚገባ የተረዱትና የሚያውቁት አፍሪካውያን በተገኘው ድል እጅጉን ኮርተዋል። አሁንም ይኮራሉ›› ሲሉ ያብራራሉ።

‹‹እንደ አለመታደል ሆኖ ከቅኝ ግዛት በፊት አፍሪካ በባሪያ ንግድ ብዙ ዋጋ ከፍላለች›› የሚሉት መምህር ሰለሞን፤ የባሪያ ንግድ ሲያበቃ ከኢንዱስትሪው አብዮት በኋላ የሰው ጉልበት ዋጋ ሲያጣና በማሽን ሲተካ አውሮፓውያን ፖሊሲያቸው አፍሪካን በአፍሪካ መበዝበዝ ያውም በቅኝ ግዛት የሚል እንደነበር አስታውሰው፤ ‹‹ይሁንና አውሮፓውያኑ ከሰው ተራ የማይቆጥሩት ጥቁር ያሸንፈናል የሚል ግምት ያልነበራቸው በመሆኑ በአድዋ ድል ከፍተኛ የሆነ የመደናገጥና የስነልቦና ጫና ተፈጥሮባቸው አልፏል። በወቅቱም ጣልያን በመሸነፏ ምክንያት የተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ የመንግሥት ለውጥ ለማድረግ ያስገደደ ነበር›› ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ መምህር ሰለሞን ማብራሪያ፤ ይህን ታላቅ ድል ተከትሎም አፍሪካውያን በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን ከአውሮፓውያን ቅን ገዢዎች ነጻ ለማድረግ ታግለዋል። ከእነዚህም እንቅስቃሴዎች መካከል ኢትዮጵያኒዝም የተባለው ንቅናቄ በዋናነት ይጠቀሳል፤ ትግሉ ብዙ አፍሪካውያንን ዋጋ ከማስከፈል ባሻገር በስኬት የተመዘገበው ብቸኛው ድል የአድዋ ድል መሆኑን አንስተዋል።

**ጥቁሮች ለዓላማቸው መሳካት በአንድነት ከታገሉ ጠላትን ማሸነፍ እንደሚችሉ ጽኑ እምነት እንዲያዝ ማድረግ ያስቻለው የአድዋ ድል፤ አውሮፓውያኑ ትምህርት ያገኙበት መሆኑን ይናገራሉ፤ ወራሪ ቅኝ ገዥዎች የአገዛዝ ፖሊሲያቸውን ጭምር እንዲመረምሩ አድርጓል**

ድሉ ከሚታሰበው በላይ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ያነሱት መምህር ሰለሞን፤ ‹‹በተለይም አፍሪካውያን ጥቁሮች ነጮችን እንዴት ማሸነፍ ቻሉ በሚል ተገርመው ነበር። ምክንያቱም በወቅቱ ነጮች በቴክኖሎጂና በሌሎች ዘርፎች የተሻሉ ነበሩ። ከአድዋ ድል በኋላ ግን ‹‹ጥቁር ነጭን ማሸነፍ ይችላል፤ጥቁርም እንደ ሰው እኩል ነው››የሚል ከፍተኛ የሆነ የሞራል ስንቅና የስነልቦና መነቃቃት ተፈጥሯል። ‹‹የታሪክ እጥፋት› ነው የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው›› ሲሉ ያብራራሉ።

ኢትዮጵያ ጣልያንን ድል በማድረጓ የተገኘው የአድዋ ድል በቅኝ ግዛት ሥር ለወደቁ አፍሪካውያን ከፍተኛ አቅም፣ ጉልበትና የሞራል ስንቅ ሆኗል›› የሚሉት ዶክተር ረታ፤ ድሉ ለፓንአፍሪካኒዝም ይበልጥ መቀጣጠል መነሻ የሚሆን መሰረት የጣለ ነው ይላሉ። ነጮችን ማሸነፍ እንደሚቻል ያሳየ ድል በመሆኑ እህትና ወንድም የሆኑ አፍሪካውያን በአንድነት ሆነው ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ አሳይቷል። በተለይም በወቅቱ በአፍሪካም ሆነ በአውሮፓ ውስጥ ሆነው በባሪያ ንግድ ለተያዙ አፍሪካውያንና ለአፍሪካ አገራት ትልቅ ሞራል በመሆን ከፍተኛ ንቅናቄ ፈጥሯል ሲሉ ያብራራሉ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በተለያዩ አፍሪካ አገራት በቅኝ ገዢዎች ላይ የተጀመሩ ንቅናቄዎች እንደነበሩ ያነሱት ዶክተር ረታ፤ የአድዋ ድል ለእነዚህ ንቅናቄዎች ጭምር መሰረት እንደሆነ ነው የተናገሩት። ጣልያኖች በድጋሚ ሲመጡም በርካታ አገራት ለኢትዮጵያ ድጋፍ በማድረግ ከኢትዮጵያ ጎን ቆመው እንደነበር ጠቅሰው፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከቅኝ ግዛት ነጻ የመሆን ፍላጎት የነበራቸው አብዛኞቹ ሚሲዮናውያን ቤተ ዕምነቶች ኢትዮጵያኒዝም በሚል ከፍተኛ ንቅናቄ አድርገው እንደነበር ነው ያመለከቱት። የኢትዮጵያኒዝም ንቅናቄ በተለይም በአፍሪካ ውስጥ በደቡብ አፍሪካ ተፈጥሮ እንደነበርም አንስተዋል።

ጣልያኖች ኢትዮጵያን ለሁለተኛ ጊዜ ለመውረር በመጡ ጊዜ ከአፍሪካውያን በተጨማሪ ሌሎች የዓለም አገራት ኢትዮጵያን ‹‹የጥቁር ተስፋችን›› በሚል በተለያየ መንገድ ሲደግፉ እንደነበር የጠቀሱት ዶክተር ረታ፤ ይህም ኢትዮጵያ ለጥቁር ህዝቦች የነጻነት ቀንዲል ተምሳሌት በመሆኗ ነው ይላሉ። የአድዋ ድል በተለይም በቅኝ ግዛት ሥር ለነበሩ አፍሪካውያን ትልቅ የሞራል ስንቅ ያስታጠቀ በመሆኑ ሁሌም ሲዘከር ይኖራል ብለዋል።

ዶክተር ረታ እንዳሉት፤ በአድዋ ድል ይበልጥ የተቀጣጠለው የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በመፍጠር፤ የአፍሪካውያንን ችግር በአፍሪካውያን የመፍታት፤ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ትስስር የመፍጠር አቅምን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። በፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄ አፍሪካ ክብሯና ነጻነቷ እንዲጠበቅ፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲፈጠር፣ ፖለቲካዊ ችግሮች እንዲቃለሉ ብዙ ተሰርቷል ።

የተባበረችና አንድ የሆነች አፍሪካን ለመፍጠር በሚል እሳቤ በንቅናቄው የተሰሩ ሥራዎች እንዳሉ ሁሉ እንቅፋት የሆኑ በርካታ ችግሮች ስለማጋጠማቸውም ዶክተር ረታ ጠቁመዋል። በተለይም የቅኝ ግዛቱ ካበቃ በኋላ አስተሳሰቡ በተለያየ መልኩ ያደገ በመሆኑ ጠባሳ ጥሎ አልፏል። በመሆኑም ምዕራባውያኑ የራሳቸውን ፍላጎት ለማስፈጸም መሪዎችን የማስቀመጥ አዝማሚያና ፍላጎቶችን በማሳደር በተለያዩ አገራት እጃቸውን እያስገቡ አገራትን በጥብጠዋል ይላሉ።

እነዚህና መሰል ችግሮች በመፈጠራቸው ምክንያት የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄ በሚፈለገው መጠን ጠንካራ መሆን ባይችልም ጉልህ አስተዋጽኦ እንደነበረው፣ ከፍተኛ መነቃቃትንና ሰፊ ግንዛቤን በመፍጠር ረገድም በጎ ተጽዕኖ ማምጣቱን ያመለክታሉ። የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄ ግቡን መምታት እንዲችል አሁን ላይ የተጀማመሩ እንቅስቃሴዎች እንዳሉ ሆኖ ነው በቀጣይ ብዙ ርቀት በመሄድ ግብን ማሳካት እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

በመሰረታዊነት የአፍሪካንና የጥቁርን አንድነት ለማምጣት የተጀመረው የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄ ከአፍሪካ ውጭ በነበሩ ጥቁር ጃማይካውያን የተጀመረ ስለመሆኑ የሚገልጹት መምህር ሰለሞን፤ ፓንአፍሪካኒዝም ጥቁሮች ያለምንም ገደብ የሚስተናገዱበት አፍሪካን አንድ የማድረግ እሳቤ ያለው መሆኑን ያስረዳሉ። ለዚህም የአድዋ ድል እንደ ስንቅ ሆኖ ያገለገለ መሆኑንም ይገልፃሉ።

አፍሪካን አንድ በማድረግ ማዋሃድ በሚል የተጀመረው የፓንአፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረትም ትልቅ ድርሻ እንደነበረው አንስተዋል። እሳቸው እንደሚሉት፤ አፍሪካውያን ከነጻነት በኋላ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ገጥሟቸዋል። ቅኝ ግዛት ጥሎት ያለፈው ጠባሳ ብዙ ችግሮችን ፈጥሯል። ድህነትን ጨምሮ በምግብ ራስን አለመቻል፣ በርካታ መፈንቅለ መንግሥቶች፣ የድንበር ግጭቶችና ሌሎች ፖለቲካዊ ቀውሶች አጋጥመዋቸዋል። ስለሆነም ፓንአፍሪካኒዝም በታሰበው ልክ ውጤታማ መሆን አልቻለም ይላሉ።

‹‹ይሁንና በቅርቡ በተካሄደው በ36ኛው የአፍሪካ የመሪዎች ስብሰባ ላይ የፓንአፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ እንደገና መነሳቱ ለአፍሪካውያን ትልቅ ኩራት ነው›› የሚሉት መምህር ሰለሞን፤ አሁን ያለው ጅማሬ መልካም ነው ይላሉ። ያለፈውን ከመውቀስ ይልቅ ካለፈው ችግር በመማር አፍሪካውያን የጋራ ችግራቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያደርጉትን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባም ያስረዳሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ለአፍሪካውያን ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ በማፈላለግም ኢትዮጵያ ምሳሌ ሆናለች። ለእዚህም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር በተያያዘ የተወሰደው እርምጃ ጥሩ ጅምር ነው። ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም በመሆን አፍሪካዊ የዲፕሎማሲ መፍትሔ ማምጣት ችላለች። የአፍሪካን ችግር አፍሪካዊ በሆነ መፍትሔ ለመፍታት የተደረገው ጥረትም የአድዋን ድል መሰረት በማድረግ የተጀመረው የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄ አንዱ ማሳያ አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

አፍሪካውያን ኢትዮጵያ ላይ ትልቅ ተስፋ አላቸው የሚሉት አቶ ሰለሞን፤ ለኢትዮጵያ ያላቸው ክብርም ከፍተኛ እንደሆነም ያነሳሉ። ኢትዮጵያውያን ግን ይህንን በልኩ እንዳልተረዱት በመጥቀስ አፍሪካውያን ለኢትዮጵያ የሰጡትን ቦታ በሚገባው ልክ መረዳት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ‹‹አፍሪካውያን ወንድም እህቶች ለሰጡት ፍቅርና ቦታ በወጉ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል። በቀጣይም አሁን በፖለቲካው የተገኘውን ድል በኢኮኖሚው በመድገም ኢኮኖሚያዊ ትስስሩን አጠናክሮ ለመቀጠል ኢትዮጵያ የማንቂያ ደውል መሆን አለባት›› በማለት ይገልፃሉ።

አድዋን ታላቅ ድል ያሰኘው የህዝቦች መተባበር፣ የህዝቦች በአንድነት መቆምና መነሳት መሆኑን ያነሱት ዶክተር ረታ፤ አሁን በአገሪቱ ያሉትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በአንድ ልብና ሀሳብ ሆኖ በጋራ መቆም ከተቻለ እንደ አድዋ ሁሉ ችግሮቹን ድል መንሳት እንደሚቻል ጠቅሰው፤ የአድዋ ድል የሚያስተምረንም ይህንኑ ነው ይላሉ።

የዶክተር ረታን ሃሳብ የተጋሩት መምህር ሰለሞን በበኩላቸው፤ አሁን ያለው ትውልድ የአድዋን ድል ምሳሌ ማድረግ እንደሚኖርበት ይገልጻሉ፤ በሃይማኖት፣ በብሔርና በተለያዩ ሃሳቦች መከፋፈሉን በመተው ታሪክን መማሪያ እንጂ ቂም መወጣጫ ባለማድረግ እንዲሁም አንድነትን በማጠናከር ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ጉዞ ማሻገር እንደሚገባ አጽንዖት ሰጥተው አስገንዝበዋል።

ጥቁሮች ለዓላማቸው መሳካት በአንድነት ከታገሉ ጠላትን ማሸነፍ እንደሚችሉ ጽኑ እምነት እንዲያዝ ማድረግ ያስቻለው የአድዋ ድል፤ አውሮፓውያኑ ትምህርት ያገኙበት መሆኑን ይናገራሉ፤ ወራሪ ቅኝ ገዥዎች የአገዛዝ ፖሊሲያቸውን ጭምር እንዲመረምሩ አድርጓል ባይም ናቸው።

በወቅቱ የነበሩት የአሜሪካና የአውሮፓ ጋዜጦችና መጽሔቶች ጭምር አቋማቸውን በመቀየር ድሉ ታላቅ ገድል መሆኑንና ዳግማዊ አፄ ምኒልክም ታላቅ መሪ እንደነበሩ መመስከራቸው ይታወሳል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# በቴክኖሎጂው ዘርፍ አገርን ወደ ላቀ ደረጃ የማሻገር ግስጋሴ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በአገራችን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት እየተስፋፋ ይገኛል።በአሁኑ ወቅት በርካታ አገልግሎቶች በዚሁ ቴክኖሎጂ እየተሰጡ ናቸው።አገልግሎቱ የዘመነ፣ እንግልትን የሚያስቀር፣ ፈጣን፣ ወዘተ. መሆኑ ተመራጭ እንዲሆን እያደረገውም ነው።አንዳንድ ተቋማት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎትን የግድ እስከማድረግም ደርሰዋል።መንግሥት የዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት እየሠራ እንደመሆኑም ቀጣይ አገልግሎቶች በዚሁ መንገድ የሚፈጸሙ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡

በዘርፉ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከመሳሰሉት በርካታ ወጣቶች እየተመረቁ ሲሆን፣ የአገልግሎቱ እየተስፋፋ መምጣት ለእነዚህ ምሩቃንና ሌሎች የዘርፉ ሰልጣኞች የሥራ ዕድሎች እየተፈጠረ ነው።ይህ ብቻም አይደለም በዘርፉ የተመረቁ ወይም የሰለጠኑ ልምዶችን እያካበቱ ሥራ እስከመፍጠር ደርሰዋል፤ በዘርፉ ውጤታማ የሆኑ ሙያተኞች ድርጅቶችን፣ ኩባንያዎችን እስከመክፈት የደረሱበትም ሁኔታ ይታያል።

እኛም በዘርፉ ተሰማራቶ ውጤታማ የሆነውንና ለሌሎችም አርአያ ይሆናል ያልነውን የዘርፉን ባለሙያ የዛሬ የስኬት እንግዳችን አድርገነዋል።እንግዳችን አዲስ አበባ ከተማ ሸራተን ሆቴል ከተሰራበት ስፍራ ፍልውሃ አካባቢ ነው የተወለደው።ያደገውም፣ የተማረውም በዚሁ አካባቢ ነው።ይህ የዛሬው የስኬት እንግዳቸውን አቶ መርእድ በቀለ ይባላል፤ አቶ መርዕድ የአይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ መስራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው።

አቶ መርዕድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን፣ ጥበብ መንገድና ጆንኤፍ ኬኔዲ፣ ሁለተኛ ደረጃውን ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ነው የተከታተለው።ጎበዝ ከሚባሉት ተማሪዎች መካከል እንደነበር ይናገራል።ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ የአንደኝነት ደረጃውን አሳልፎ አልሰጠም።በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ መፈተናም በሰባት የትምህርት ዓይነቶች ‹ሌ› በማምጣት በስኬት ነው ያጠናቀቀው።‹‹ዶክተር እሆናለሁ፤ ፓይለት እሆናለሁ ወዘተ...›› የልጅነት ምኞቶቹ ነበሩ።

በወቅቱ ባስመዘገበው ከፍተኛ ውጤት የመገናኛ ብዙሃንን ቀልብ ስቦም እንደነበር ጠቅሶ፣ በአንድ ሬዲዮ ጣቢያው ቃለ መጠይቅ ሲያደርግለት ሦስት ነገሮችን የመሆን አማራጭ እንደነበረው መግለጹን ያስታውሳል።‹‹አንደኛ ኤሌክትሪካል ኢንጅነር፣ ሁለተኛ ወደ ሶሻል ሳይንስ ከተሳብኩ ኢኮኖሚስት፤ ሦስተኛው የቲዮሎጂስት ፍላጎት ስላለኝ ቲዮሎጂስት የመሆን ፍላጎት አለኝ›› በማለት የወደፊት ፍላጎቱን በወቅቱ ለጣቢያው ተናግሮ እንደነበር ይገልጻል።

እንግዳችን የመጀመሪያ ምርጫውን አገኘ።በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ተመድቦ የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ ትምህርቱን በዚያው ተከታተለ።በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ቆይታው ያገኛቸውንና ፍላጎቱን ለማሳካት ያስቻሉትን የተለያዩ ዕድሎች በአግባቡ እንደተጠቀመባቸው ይናገራል።

በትምህርት ቆይታው ያደረጋቸው ጥረቶች ሁሉ ለዛሬ ስኬቱ እንዳደረሱት ይገልጻል።ዛሬ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂው ዘርፍ አንቱ ለመባል በቅቷል።በዘርፉም ብዙ ሙያተኞችን አፍርቷል።

በኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግና እና በኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ያገኘው አቶ መርዕድ፣ በዩኒቨርሲቲው የትምህርት ቆይታው ከተከታተለው ትምህርት አብላጫው ከኮምፒዩተር ሳይንስ ጋር የተያያዘ ስለነበር ውስጣዊ ፍላጎቱ ለሆነው ለኮምፒዩተር ዕውቀት ያደላ እንደነበር ያስታውሳል።

በዩኒቨርሲቲ ቆይታው ወቅትም ዝንባሌው ለኮምፒዩተር ኢንጅነሪንግ ያደላ ነበር።የሦስተኛ ዓመት ተማሪ በነበረበት ወቅት ከጓደኞቹ ጋር የአይ ሲቲ ክለብ በማቋቋም የክለቡ ፕሬዚዳንት ሆኖ አገልግሏል።በሚያስመዘግበው የላቀ ውጤት እንዲሁም ለዘርፉ ባለው ውስጣዊ ፍላጎት የተነሳ ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም ለዘርፉ ያለውን ፍላጎትና እምቅ ችሎታ አውጥቶ እንዲጠቀም ዕድል ሰጥቶታል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ኔትዎርክ ላይ የመሥራትና የማስተማር ዕድልም አግኝቶ ነበር።በክረምት ወቅትም



አቶ መርዕድ በቀለ

**‹‹አንደኛ ኤሌክትሪካል ኢንጅነር፣ ሁለተኛ ወደ ሶሻል ሳይንስ ከተሳብኩ ኢኮኖሚስት፤ ሦስተኛው የቲዮሎጂስት ፍላጎት ስላለኝ ቲዮሎጂስት የመሆን ፍላጎት አለኝ**

እንዲሁ የልምምድ ጊዜውን ያሳለፈው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የኔትዎርክ ሥራ በሚሠራ መስሪያ ቤት ነው።ይህም ገና ተማሪ እያለ በኔትዎርክ ሥራ ዓለም አቀፍ የምስክር ወረቀት እንዲያገኝ አስችሎታል።እነዚህ መልካም አጋጣሚዎች ተደማምረው በኔትዎርክ ኢንጅነሪንግ ዘርፍ እንዲሰማራና አሁን የደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ አግዘውታል፡፡

ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በጥሩ ውጤት ያጠናቀቀውና ጥሩ የሥራ ልምድንም ያካበተው አቶ መርዕድ፤ በዩኒቨርሲቲው የላቀ ውጤት ካስመዘገቡ አራት ተማሪዎች መካከል አንዱ በመሆኑ በዩኒቨርሲቲው የመቅረት ዕድልም ገጥሞት ነበር።ይሁንና የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪውን የመቀላቀል ከፍተኛ ፍላጎት የነበረው በመሆኑ በተመረቀ ማግስት የኔትዎርክ ኢንጂነር ሆኖ ልምምድ ሲያደርግበት ለነበረው ተቋም ተቀጥሮ ለአንድ ዓመት አገልግሏል።

በዘርፉ አዳዲስ ዕውቀቶችን መጨመር የሚያስችለውን ዓለም አቀፍ ስልጠና ለማግኘት ፍላጎት የነበረው አቶ መርዕድ፤ ለዚህም ምቹና አስተማማኝ መንገድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መሆኑን በማመን ይሠራበት ከነበረው የግል ድርጅት ደመወዝ ቀንሶ ወደ መንግሥት ተቋም አምርቷል።ቀደም ባለው ጊዜ አይ ሲቲ ዴቨሎፕመንት ኤጀንሲ ይባል የነበረው፤ በአሁኑ ወቅት ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የመንግሥትን የዳታ ሴንተር በማልማት ከፍተኛ የኔትዎርክ ባለሙያ በመሆን አገልግሏል።

በመንግሥት መስሪያ ቤት ከአንድ ዓመት አገልግሎት በኋላ በዘርፉ የሚሰጠውን ስልጠና እንግሊዝ አገር ሄዶ የመሰልጠን ዕድል አግኝቷል።በመርፌ ቀዳዳ የመሽሎክ ያህል ጠባብ የሆነውን ዕድል ውጤታማ ሆኖ በማለፍ ነው ስልጠናውን ያገኘው፡፡

እጅግ ፈታኝና ጠባብ ዕድል የነበረውን ስልጠና ለማግኘት ፈተናውን በጃፓን አገር መውሰድ የግድ ነበርና ወሰዷል።ፈተናውን ከሚወስዱ ሰዎች መካከልም የሚያልፉት ሦስት በመቶ ያህሉ ብቻ ቢሆኑም፣ አቶ መርዕድ ግን ጥሩ ውጤት በማምጣት ፈተናውን ማለፍና ዓለም አቀፍ ስልጠናውን ከእንግሊዝ አገር ማግኘትና በዚህም ብቸኛው ኢትዮጵያዊ መሆን ችሏል።

ከመንግሥት አገኛለሁ ብሎ የተማመነውን የስልጠና ዕድል ማግኘት የቻለው አቶ መርዕድ፤ ሙሉ ወጪውን መንግሥት ሸፍኖለት ነው የሰለጠነው።መንግሥትም ወጪውን ሸፍኖ ማስተማሩ ተመልሶ አገሩን በማገልገል እንዲክሰው በሚል ነው።ያም ባይሆን በአገሩ የመሥራት ቀና ልብ ያለው በመሆኑ፤ በገባው ቃል መሠረት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል።በተለያዩ የዓለም አገራት ከፍተኛ ተከፋይ ሆኖ መሥራት የሚያስችለውን የምስክር ወረቀት ያገኘው ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ቢሆንም፣ ህልሙ በቴክኖሎጂው ዘርፍ አገሩን ወደ ላቀ ደረጃ ማሻገር በመሆኑ በአገሩ በዘርፉ ተሰማርቶ ትውልድ እያፈራ ይገኛል።

ከውጭ አገር ትምህርት ሲመለስ ኢትዮ ቴሌኮም ትልቅ የኔትዎርክ ማስፋፊያ ሥራ እየሠራ ነበር።አቶ መርዕድም በያዘው ከፍተኛ የምስክር ወረቀት ምክንያት ኢትዮ ቴሌኮምን ተቀላቀለ።በዚሁ አጋጣሚም ዕድለኛ በመሆን ዓለም አቀፍ ተከፋይ መሆን ቻለ፡፡

ከኢትዮ ቴሌኮም መደበኛ ሥራው በተጨማሪም ሞያዊ ዕውቀቱንና አገልግሎቱን የሚፈልጉ በርካታ ተቋማት እንደነበሩ የሚያስታውሰው አቶ መርዕድ፤ በተለይም ኢሚግሬሽን፣ ባንኮችና የተለያዩ ተቋማት አገልግሎቱን በስፋት ይጠቀሙ ነበር።የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ቁጥራቸው ሲበራከት በኢኮኖሚ እየደረጀ መጣ።ይህም የኢኮኖሚ ነፃነት እንዲያገኝ በር የከፈተለት ከመሆኑም በላይ በተጨማሪ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያ መገንባት አስችሎታል፡፡

‹‹በዘርፉ ያካበትኩት ሞያዊ ክህሎት ወደ ቢዝነሱ እንድገባ መንገድ ጠርጎልኛል›› የሚለው አቶ መርዕድ፤ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያውን አስቦና አቅዶ እንደ አንድ የቢዝነስ ዘርፍ የገባበት አለመሆኑን አጫውቶኛል።ከኢትዮ ቴሌኮም ሥራ በተጨማሪ በቤት ውስጥ በግሉ ይሠራ የነበረውን ሥራ የሙሉ ጊዜ ሥራው ያደረገውም የኢትዮ ቴሌኮም ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ እንደሆነ ያስታውሳል፤ በ2011 ዓ.ም ቢሮ ተከራይቶ አምስትና ስድስት ሠራተኞችን በመያዝ ነው ኩባንያውን ያቋቋመው፡፡

ሥራ ስለበዛበት ብቻ ኩባንያ ያቋቋመው አቶ መርዕድ፤ ኩባንያውን ለመምራት ደግሞ አሜሪካን አገር በሚገኝ አንድ ዩኒቨርሲቲ በኦን ላይን የቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ትምህርትን ተምሯል።ይህን ጊዜ ከኢንጅነሪንግ ውጪ የሆነውን የአስተዳደር ሙያን በመማር የአስተዳደር ሥራ ምን እንደሚመስል በመረዳት ኩባንያውን መምራት ችሏል።በዚሁ ሂደት ውስጥም ባለቤቱ የላቀ ድርሻ የነበራት መሆኑንም አጫውቶናል፡፡

የተማረውንና ያነበበውን ሁሉ ወደ ተግባር የመቀየርና የመሞከር ልምድ ያለው አቶ መርዕድ፤ የተማረውን በሠራተኞቹና በኩባንያው ላይ ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ መሆን ችሏል።ዕለት ዕለት በሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረትም ኩባንያ እያደገና እየተደራጀ ሄዷል።ከአምስት ሠራተኞች አስር፣ ሃያ፣ ሰላሳ፣ አርባና ሃምሳ እያለ ተቋሙ በራሱ መቆም የጀመረው ‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ›› ተቋማዊ ሥርዓት በመገንባት ሥራን በጥራትና በፍጥነት የሚሠራና የጀመረውን የሚጨርስ ስመ ጥርና ደንበኞች የሚተማመኑበት ኩባንያ መሆን ችሏል።

ሁሉም ነገር ወደ ቴክኖሎጂ እየተቀየረ በመጣበት ወቅት ወደ ሥራው መግባት የቻለው አቶ መርዕድ፤ ቴክኖሎጂ በአገር ውስጥ ያመጣውን ለውጥ ተሳታፊ በመሆን የማየት ዕድል ያጋጠመው የመጀመሪያው ሰው መሆኑን ይናገራል።አገሪቷ ቴክኖሎጂን በስፋት መጠቀም የጀመረችበት ወቅት እንደመሆኑ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ባንኮች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና በሌሎችም ትላልቅ ተቋማት ውስጥ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተደራሽ በማድረግ ‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ›› አሻራውን ማኖር ችሏል።

ቴክኖሎጂው ገና እየተስፋፋ በመሆኑ በዘርፉ የሥራ ልምድ ያለው ሰው ገበያው ላይ ለማግኘት እንደሚቸግር የገለጸው አቶ መርዕድ፤ የሚቀጥራቸው አብዛኞቹ ሠራተኞችም ልምድ የሌላቸውና ሰልጥነው የሚሠሩ መሆናቸውን ያመለክታል።

በ‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ›› ሰፊ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች የሥራ ልምድ የሌላቸው በመሆናቸው የተቋሙን የሥራ ባህል በቀላሉ የመለማመድ ዕድል ያገኛሉ።ተቋሙ የሚከተለው የሥራ ባህልም የአሜሪካ አገር የሥራ ባህል መሆኑን ጠቅሶ፣ ለአብነትም ጠዋት አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ሥራ ይጀምራሉ፤ ዕለት ተዕለትም ማን ምን እንደሚሠራ በግልጽ ይታወቃል ውጤቱም የሚታይ ይሆናል ሲል ያብራራል።

በአሁኑ ወቅትም 165 ለሚደርሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለው ‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ›› እያንዳንዱ ሠራተኛ በየዕለቱ በሚያስመዘግበው ውጤት ተለክቶ ተጨማሪ ተከፋይ ይሆናል።ይህም የበለጠ ለመሥራትና ሠራተኛው ለሥራ የሚኖረውን ትጋት የሚጨምርለት ይሆናል።ይህንን የሥራ ባህል ከትምህርት ቤት የሚወጡ አዳዲስ ሠራተኞች በቀላሉ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ አቶ መርዕድ አጫውቶናል፡፡

የ‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ›› እሴትና ተልዕኮው የአፍሪካን ሕይወት በጥሩ የሥራ ሥነምግባርና በሥርዓት አስተሳስሮ መቀየር የሚል እንደሆነ የሚናገረው አቶ መርዕድ፤ በዚህ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ስለመኖራቸው ይገልፃል።አንደኛው ሥነሥርዓትን የተከተለ የሥራ ባህልን መፍጠር ሲሆን ሁለተኛው ጠንካራ ሥርዓት መዘርጋት የሚል ነው።እነዚህን ሁለት ጉዳዮች ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ የአፍሪካን ሕይወት መቀየር ይችላል የሚል ዕምነት አለው።ወደ ተቋሙ የሚገቡ ሠራተኞችም በዚሁ መንገድ መቃኘት እንዲችሉ ስልጠና የሚሰጣቸው ይሆናል።

‹‹በአስተዳደጌ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ካላቸው ቤተሰቦቼ በተጨማሪ በጎ ምግባርን ተግባራዊ ማድረግ እንድችል በሰንበት ትምህርት ቤት የነበረኝ ቆይታም አግዞኛል›› የሚለው አቶ መርዕድ፤ ለሠራተኞቹ አርአያ በመሆን ከሠራተኞቹ እኩል እንደሚሠራና በሥራውም ተመራጭና ቀዳሚ ለመሆንና ይህን ጠንካራ የሥራ ባህል ለሌሎችም ለማስተላለፍ አብዝቶ ይተጋል።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም ለወጣቶች ነፃ ስልጠና ይሰጣል።ሥልጠናውን ካገኙት መካከልም ገሚሶቹን በድርጅቱ የሚቀጥራቸው ሲሆን ሌሎቹም ስልጠናውን አግኝተው በተለያየ ቦታ የመቀጠር ዕድል ይኖራቸዋል።ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋርም በጋራ በመሥራት ለተማሪዎች ስልጠና ይሰጣል።ለአብነትም በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ለሴት ተማሪዎች ስልጠና ሰጥቷል፤ የሕይወት ልምዱን አካፍሏል።

‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ›› ከመቋቋሙ አስቀድሞ በዘርፉ የተሰማሩ አገር በቀል ተቋማት ባለመኖራቸው ከኬንያ፣ ከሕንድና ከተለያዩ አገራት ዶላር ተከፍሏቸው ይመጡ እንደነበር ያነሳው አቶ መርዕድ፤ ለዚህም በመቶ ሺዎች ዶላር ይወጣ ነበር ብሏል።በአሁኑ ወቅት የእሱ ኩባንያ ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ በመሆኑ ለዘርፉ ይወጣ የነበረውን ዶላር በማስቀረት የድርሻውን መወጣት ችሏል።

ይህ ብቻ አይደለም።ኬንያ በመሄድ አገልግሎት በመስጠት ዶላር ማምጣት የምንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል ይላል።በ14 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከመቶ በላይ የሚደርሱ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ የቻለው ‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ››፣ ሥነምግባር ያላቸው ሠራተኞችን እንዲሁም ጥሩ የሥራ ባህልንና የሥራ አካባቢን መፍጠር እንደቻለም አስታውቋል።

‹‹ትልቅ ነገርን ማሰብና መመኘት፤ ግን ደግሞ በትንሹ መጀመር›› የሚል ዕምነት ያለው አቶ መርዕድ፤ ትልቅ ራዕይ ሰንቆ በየዕለቱ ትንሽ ትንሽ በመሥራት ካሰበበት መድረስ እንደቻለም አጫውቶናል።በቀጣይም ‹‹አይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ›› ከአገር ውስጥ ባለፈ ኢትዮጵያን ሊያስጠራ የሚችል ጠንካራ ተቋም እንደሚሆን ያለውን ዕምነት ገልጿል።

# መሠረተ ልማት

## የዓድዋ ድልን እንዲዘክር ተደርጎ እየተገነባ ያለው ፕሮጀክት

**መሳኩ ሔርሴ**



**ግንባታው 78 ነጥብ 2 በመቶ የደረሰው የዓድዋ ሙዚየም**

የኢትዮጵያውያን አንድነት መገለጫ እና የኅብረታቸው ልዩ ተምሳሌት ነው፤ የዓድዋ ድል ። ኢትዮጵያውያን የዓድዋን ድል የተቀዳጁት የመሪያቸውን የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክን ጥሪ ተቀብለው በአንድትነት እንደ አንድ ሰው ሆነው በመፋለማቸው ነው።

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን የቅኝ ግዛት አሳቢዎችን ድል የነሱበት ብቻ አይደለም ። የይቻላል መንፈስን በመላ ዓለም በሚኖሩ ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ በማስረጹም ይታወቃል ። አፍሪካውያን ቅኝ አገዛዝን አሻፈረኝ ብለው ይታገሉ በነበረበት ወቅት የዓድዋ ድል ትልቅ አቅም ሆኗቸዋል ። በተለይ በፓንአፍሪካኒዝም ንቀናቄያቸው የበለጠ እንዲንቀሳቀሱ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል ። እናም ድሉ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በቅኝ ግዛት ስር ሲማቅቁ የነበሩ የአፍሪካ ሕዝቦችም ጭምር ነው፡፡

በኋላ ቀር የጦር መሳሪያዎች ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀን የጣልያን ሰራዊት ድል ማድረግ የተቻለበትና ይህን በመላ ዓለም ጭምር ታላቅ ዜና ሆኖ የወጣበትና ኢትዮጵያ ይበልጥ እንድትታወቅ ያደረገ ድል መሆኑን የታሪክ ድርሳናት ያስገነዝባሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን ይህን ታሪክ በየአመቱ በተለያዩ መንገዶች ሲዘክሩት ኖረዋል፤ እየዘከሩትም ይገኛሉ። ድሉ በአደባባይ፣ በውይይት፣ በኤግዚቢሽንና በመሳሰሉት ይዘከራል ። የዓድዋን ድል የሚዘክሩ አንዳንድ ስያሜዎች ቢኖሩን፣ የተለያዩ ወገኖች ዓድዋን የሚዘክሩ ተቋማት፣ መሠረተ ልማቶች፣ ወዘተ በበቂ ሁኔታ እንደሌሉ ሲያመልክቱ፣ ድሉን የሚመጥኑ መዘከሪያዎች መገንባት መሰየም እንዳለባቸው ሲያሳስቡ ኖረዋል ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለእዚህ የዜጎች ጥያቄ መልስ ሊሰጥ፤ የዓድዋን ድልም በሚገባ ይዘከረዋል ያለውን አንድ ግዙፍ ፕሮጀክት በከተማዋ እምብርት ፒያሳ ላይ እየገነባ መሆኑ ይታወቃል። ይህ የዓድዋ ድል እንዲመዘገብ ጉልህ ድርሻ ያበረከተውን የኢትዮጵያውያንን የአንድነት ስሜት፣ ተጋድሎ፣ ጀግኖችንና የመሳሰሉትን ሊዘክር የሚችል ፕሮጀክት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታላላቅ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት አማካይነት ነው እየተገነባ ያለው። ፕሮጀክቱ የዓድዋ ሙዚየምን ጨምሮ በርካታ አገልግሎቶችን ሊሰጡ የሚችሉ ግንባታዎች የተካተቱበት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ግንባታው 78 ነጥብ 2 በመቶ ደርሷል፡፡

ከፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የዓድዋ ሙዚየም ግንባታ ፕሮጀክት በከተማዋ አስተዳደር እየተገነቡ ካሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል ። ፕሮጀክቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉና እርስ በእርሳቸው የተሰናሰሉ 11 ሕንፃዎች ተካተውበታል ።

የአዲስ አበባ ከተማ የታላላቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ደቦ ቱንካ እንደሚሉት፤ የፕሮጀክቱ ግንባታ በ2012 ዓ.ም ነው የተጀመረው ። በሦስት ነጥብ ሦስት ሄክታር መሬት ላይ ያረፈና በአራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በጀት እየተገነባ ያለው ነው።

ፕሮጀክቱ ‹‹ዓድዋ ዜሮ ዜሮ ሙዚየም ፕሮጀክት›› የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፤ ሥራ አስኪያጁ ስለስያሜው ሲያብራሩም፡- ፕሮጀክቱ በእዚህ ስያሜ እንዲጠራ የተደረገው ፕሮጀክቱ እየተገነባ ያለበት የመሃል ፒያሳ ስፍራ ወደ ሁሉም ቦታ ለመሄድ መነሻ ነው ። የኢትዮጵያ እምብርት እንደመሆኑ ወደተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚደረጉ ጉዞዎች ከዚህ ቦታ ይጀምራሉ ። የዓድዋ ጉዞም ከዚሁ ቦታ ነው የተጀመረው ። ኢትዮጵያውያን ከየአቅጣጫው በመትመም አሁን ፕሮጀክቱ እየተገነባ ባለበት ቦታ ላይ ተሰባስበው፣ ነጋሪት ተጎስሞ ወደ ጦር ግንባር የዘመቱበት የመነሻ ቦታ በመሆኑም ነው ስያሜው የተሰጠው» ብለዋል ።

ኢንጂነር ደቦ እንዳሉት፤ ግንባታው የተለያዩ ክፍሎችን አካቷል፤ የዓድዋ ተራሮችን የሚያሳዩ ቅርጾች ይኖሩታል፤ በጦርነቱ ወቅት ወደ ዓድዋ የተደረገውን አስቸጋሪ ጉዞ ለማሳየት በፕሮጀክቱ ላይ ረጅም ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፤ መግቢያ በሩ ላይ የኢትዮጵያውያን ጀግንነት ማሳያ የሆኑት የጋሻና ጦር ምልክቶች እንዲኖሩት ተደርጓል ።

በውስጡ በርካታ ጋላሪዎች፣ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ ቅርስ ማሳያዎች እና የቱሪስት መስህብ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችም ተካተዋል ። በፕሮጀክቱ ውስጥ ነጋሪት ቅርጽ ያለው ክፍል ያለ ሲሆን፣ ነጋሪቱ ላይ ደግሞ በጦርነት የተሰዉ ሰማዕታት ምስል ይደረግበታል ።

በሌላ በኩል የውሃ ገንዳዎች የሚመስሉ ግንባታዎች ያሉት ሲሆን፤ በዚህም ላይ ጠላትን እንዴት ውሃ በመከላከል ማሸነፍ እንደሚቻል የሚያሳዩ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ይቀመጣሉ ። ይህም በተለይ በጦርነቱ ላይ ለጣሊያኖች ውሃ እንዳይደርስ ውሃውን በማቋረጥ ትልቅ ሚና የተጫወቱትን እቴጌ ጣይቱን የሚያስታውስ ይሆናል ሲሉ ኢንጂነር ደቦ ጠቁመዋል፡፡

‹‹የዓድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ነው፤ በየትኛውም ዓለም ያለ ጥቁር የሚኮራበት ። ጥቁር ማሸነፍ ይችላል፤ የማሸነፍ አቅም አለው ። ጥቁር ብልህ እንደሆነ ያሳየ ድል ነው የሚሉት ኢንጂነር ደቦ፤ የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ይበልጥ እንዲቀጣጠልም ሆነ የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑ የአፍሪካ ህብረትን የመመስረት እንቅስቃሴዎች እንዲጀመሩ መሠረት የሆነው የዓድዋ ድል መሆኑን ጠቅሰዋል ። ይህንን ትልቅ ታሪክ የሰሩ የጦር መሪዎችን የሚያሳዩ ምስሎች በሙዚየሙ እንደሚካተቱ ጠቁመዋል፡፡

የጽሕፈት ቤቱ የኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክተር ኢንጂነር ዳዊት ጥበቡ እንደሚሉት፤ ፕሮጀክቱ በዋናነት የዓድዋ ሙዚየም ሆኖ የሚያገለግል ነው ። በወቅቱ የነበረውን ታሪክ የሚገልጽ፣ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለውን ታሪክ ሊገልጽ እንዲሁም የወደፊት ተስፋን ሊያሳይ በሚችል መልኩ እየተገነባ ይገኛል፡፡

ፕሮጀክቱ የዓድዋ ድል ታሪክ በሚገባ እንዲዳሰስ እና እንዲታይ አድርጎ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው የገለጹት ኢንጂነር ዳዊት፣ በውስጡ የዓድዋ ታሪክን የሚዘክሩ የተለያዩ እውነቶች እንዲኖሩት መደረጉንም ነው ያመለከቱት። ኢትዮጵያውያን ስለ ታሪካቸው የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማስቻሉ ባሻገር፣ ሌሎች አፍሪካውያን ወንድሞች ኢትዮጵያ ለጥቁሮች ነፃነት ያበረከተችውን አስተዋጽኦ የበለጠ እንዲገነዘቡ ለማድረግ ይጠቅማል ብለዋል ።

ኢንጂነሩ ፕሮጀክቱ የሚገነባበት ቦታ ፒያሳ መሆኑን በመጥቀስም፣ የዓድዋን ድል ከመዘከር ባሻገር የፒያሳን መልክ የሚያሳይ እንዲሆን ብዙ ጥረት መደረጉንም ጠቁመዋል ። የፒያሳ መገለጫ የሆኑ የኪነ ሕንፃ ሥራዎች በውስጡ መካተታቸውን፣ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የአዲስ አበባን በተለይም የፒያሳን ውበት በእጅጉ ይጨምራል ተብሎ እንደሚታሰብም ነው ያብራሩት፡፡

በጦርነት ሴቶች ያደረጉትን ተሳትፎ የሚየሳዩ የኪነ ጥበብ ሥራዎች እንደሚኖሩትም ገልጸው፣ ከክተት አዋጁ፣ ከነጋሪት ጉሰማው አንስቶ ጦርነቱ እስኪያበቃ ድረስ የነበረውን ሁኔታ የሚያመላክት እንደሚሆንም ተናግረዋል ። ስንቅ ከማቀበል ጀምሮ እስከ ጦር መምራት ደረጃ ያሉትን የሴቶች ተሳትፎዎች፣ ጀግኖችን፣ ሰማዕታትን የሚዘክር፣ በዓድዋ ድል ወቅት የተከናወኑ የተለያዩ ኩነቶችን የሚገልጽ ፕሮጀክት መሆኑንም አስታውቀዋል ።

ኢንጂነር ዳዊት እንዳብራሩት፤ የተለያየ ሙያ ያላቸው ሰዎች በፕሮጀክቱ እየተሳተፉ ይገኛሉ፤ ሁሉም በእውቀታቸውና በሙያቸው አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ ። የታሪክና የኪነ ሕንፃ ባለሙያዎች፣ የአርክቴክቶች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር በፕሮጀክቱ በመሳተፍ ላይ ናቸው ።

ፕሮጀክቱ በዓድዋ ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያውያን ለነፃነታቸው እና ለሉዓላዊነታቸው ያሳዩትን ትብብር በሚያመለክት መልኩ እየተገነባ ይገኛል። ዛሬም ኢትዮጵያ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ናት ። ከችግሮቿ ለመሻገር የሁሉንም ዜጋ ትብብር ትሻለች ። ሁሉም በሙያው፣ በእውቀቱ፣ በገንዘቡ፣ በጉልበቱ ለአገሩ መሥራት አለበት። ሙዚየሙ በዓድዋ ወቅት የነበረውን ዓይነት ትብብር እና ህብረት የሚፈልጉ በርካታ ችግሮችን ለማሸነፍ መልእክት የሚተላለፍበት መሆኑም ተጠቁሟል።

ኢንጂነር ዳዊት እንዳስታወቁት፤ ፕሮጀክቱ አንድ ሺ መኪና ማቆም የሚችል ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያ እንዲኖረው ተደርጓል፤ ይህም በአካባቢው የሚስተዋለውን የመኪና ማቆሚያ ችግር ለመቅረፍ ሁነኛ መፍትሄ ይሆናል ። የመኪና ባለቤቶች መኪናቸውን በመንገድ ዳር በማቆም ለትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት እንዳይሆኑ መፍትሄ በመሆን ያገለግላል ። በከተማው ያለውን የትራፊክ ፍሰት ከማሳለጥ ባሻገር ለደንበኞች ንብረት ደህንነት መጠበቅ፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ጉልህ ሚና ይጫወታል ። ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉትና በአጠቃላይ ለከተማዋ ገጽታ ትልቅ ፋይዳ ያለው ፕሮጀክት ነው ።

የፕሮጀክቱ ግንባታ ጃንግ ሱ በተባለ የቻይና ተቋራጭ እየተካሄደ ይገኛል ። የኢትዮጵያ ግንባታ ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ደግሞ የማማከር ሥራውን ያካሂዳል ።

በፕሮጀክቱ ላይ ዘመኑ የደረሰባቸው አዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎች እና ሀሳቦች ተግባራዊ የተደረጉበት ሲሆን፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እየተሳተፉ ያሉበት እንደመሆኑ የእውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር እንደሚያፋጥን ተስፋ የተጣለበት ሲሉ ኢንጂነር ዳዊት ተናግረዋል ።

የፕሮጀክቱ ግንባታ በአሁኑ ወቅት 78 ነጥብ 2 በመቶ ላይ ደርሷል፤ ይጠናቃቃል ተብሎ ከተቀመጠለት ጊዜ በላይ መፍጀቱም ተጠቁሟል ። የፕሮጀክቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ደቦ ቱንካ ፕሮጀክቱ ሊጓተት የቻለበትንም ምክንያት ሲያብራሩ፤ «የፕሮጀክቱ ዲዛይን እና ግንባታ ሥራ አንድ ላይ የሚሄድ ነው ። ዲዛይን እና ግንባታው አንድ ላይ በሚሆንበት ጊዜ የዲዛይኑ ሥራ በየጊዜው ተጠንቶና ተቀምሮ አንድ ላይ መቀመጥ አለበት ። በፊት አንድ ፕሮጀክት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ጥናቱና ዲዛይኑ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው ወደ ሥራ የሚገባው፤ አሁን ግን ዲዛይኑ የኮንትራቱ አካል ነው ። የፕሮጀክቱ ግንባታ እንዲጓተት አንዱ ምክንያት ይሄ ነው» ብለዋል ፡፡

እንደ ኢንጂነር ደቦ ማብራሪያ፤ ፕሮጀክቱ እንደ ሌሎች የግንባታ ፕሮጀክቶች የሚገነባ አይደለም። መጀመሪያ ዲዛይኑ ላይ መግባባት፣ ዲዛይኖቹ በሚሠሩበት ወቅት የተዛባ ታሪክን እንዳያመጡ ጥንቃቄ ማድረግን ይፈልጋል ። የብዙ ባለድርሻ አካላት ይሁንታን ማግኘት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ ። ከባለድርሻ አካላቱ ይሁንታ ሲያገኝ ነው ዲዛይኑ መሬት ላይ እንዲሠራ የሚደረገው ። በመሆኑም ጥናትና ዲዛይን ብዙ ጊዜ ሊፈጅ ችሏል ።

በጥናትና ዲዛይን ጊዜ ደግሞ ኮቪድ 19 ተጨማሪ ተግዳሮት ሆኖ እንደነበር አስታውሰው፣ በወቅቱ በአብዛኛው እንቅስቃሴ እንዳልነበረም ተናግረዋል። ያ ወቅት ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶችን ለማስገባት አስቸጋሪ እንደነበረ፣ ባለፉት ዓመታት በአገሪቱ ውስጥ የነበረው አጠቃላይ ሁኔታም ግንባታው ላይ የራሱን ጫና ማሳደሩን ጠቅሰው፣ ይህ ሁሉ የፕሮጀክቱ ግንባታ እንዲጓተት ምክንያቶች መሆናቸውን አስታውቀዋል ።

ፕሮጀክቱ የተወሰነ መዘግየት ቢገጥመውም፣ ከባባድ የሚባሉ የኤሌክትሮ መካኒካል፣ የሳኒተሪ፣ እንዲሁም ኤሌክትሪካል ኢንስታሌሽን ሥራዎች ተጠናቀዋል ያሉት ኢንጂነር ደቦ፤ በተለያዩ ምክንያቶች የባከነውን ጊዜ በማካካስ በሚቀጥለው ዓመት ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ እና ለአገልግሎት ክፍት ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ የሚያስችለው አብዛኛው ዝግጅት ተጠናቋል ። ፕሮጀክትን በጊዜ ለማጠናቀቅ ዋናው ግብዓት ነው፤ ግብዓቶች ተመርተው፣ ተጓጉዘው፤ ለመገጠም ዝግጁ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ከ100 በላይ ኮንቴይነሮች ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ይዘው ከውጭ ገብተዋል። ከ50ሺ ካሬ በላይ የሚሸፍን ሴራሚክ ገብቷል። ሙሉ በሙሉ መሥራት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ። ፕሮጀክቱን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ ከተማ አስተዳደሩ እና ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በየጊዜው ጉብኝት እያደረጉ ናቸው ።

# ርዕሰ አንቀፅ



## በድርቅ አደጋ ውስጥ ያሉ ወገኖቻችንን እንታደግ!

ሀገራችን በድርቅና ከዚህ በሚመነጭ የረሀብ አደጋ ከሚጠቁ ሀገሮች መካከል አንዷ ናት። በዚህም በየዘመኑ በሰውና በንብረት ላይ የደረሱ ጉዳቶች ከፍተኛ እንደሆኑ የታሪክ ማህደራት ያመለክታሉ። ስሟ በዓለም አቀፍ ደረጃ የረሀብ መገለጫ እስኪመስል ድረስ ሲታይ መኖሩም የአደባባይ እውነታ ነው።

ከቅርቡ ጊዜያት ካለው እውነታ ብንነሳ በአፄ ምኒልክ (1880 - 1883)፤ በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ (1965/66 ዓ.ም) ፣ በደርግ (1977 ዓ.ም) በኢህአዴግ /1990/ ወቅት ከፍተኛ የድርቅና የርሃብ አደጋዎች ተከስተዋል፡፡ በዚህም ሀገር እንደ ሀገር የከፈለችው ዋጋ የየዘመኑ ሀገራዊ ጥቁር ታሪክ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በእነዚህ የታሪክ ምዕራፎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎቻችን ለከፋ የረሀብ አደጋ ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ለሞት ተዳርገዋል፤በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የጋማና የቀንድ ከብቶች አልቀዋል። በዚህም ሀገር በየዘመኑ አንገት ለሚያስደፉ የልብ ስብራቶች ተዳርጋለች፤ የልብ ስብራቱ ትውልድ ተሻግሮም የታሪካችን ጥቁር ጠባሳ ሆኗል።

ይህን ሀገራዊ ታሪካዊ እውነታ ለመለወጥና ይህን የታሪክ ጥቁር ጠባሳ ለመፋቅ እንደ ሀገር ሁለንተናዊ በሆነ የብልጽግና ንቅናቄ ውስጥ ባለንበት በዚህም ወቅት የድርቅ አደጋ በተለያዩ የሀገራቱ አካባቢዎች ተከስቷል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በኦሮሚያ ክልል፤ በቦረና ዞኑ የሚገኙ 13 ወረዳዎች በድርቅ ተጠቅተዋል። በሶማሌ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች ችግሩ እንደተከሰተ ተነግሯል።

በቦረና ዞን በድርቁ ምክንያት ከሁለት ሚሊዮን በላይ እንስሳት ሞተዋል፤ 60 በመቶ የሚሆነው የወረዳዎቹ ነዋሪዎችም /807 ሺህ ሰው/ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ከነዚህም ውስጥ 167 ሺህ የሚሆኑ ደግሞ አስቸኳይና ተከታታይ ድጋፍ የሚፈልጉ ናቸው።

መንግሥት በአንድ ዙር ከ600 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ከ90 ሺህ ስድስት መቶ ኩንታል በላይ ስንዴ፣ ሁለት ሺህ 66 ሊትር ዘይት እና 22 የውሃ ቦቴዎች እርዳታ አቅርቧል። ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና አጋር አካላት ወደ 750 ሚሊዮን የሚጠጋ የገንዘብ ድጋፍ ተገኝቷል።

የችግሩ ሰለባ የሆኑ ዜጎቻችንን ለመታደግ እየተደረገ ያለው ጥረት በመንግስትና በሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ቀጥሏል። በግለሰብ ሆነ በቡድን ደረጃ ድጋፎችን ለማሰባሰብ የሚደረጉ ጥረቶችም በስፋት እየተከናወኑ ነው። ይህ ይበል የሚያሰኝና ለወገን ቀድሞ ደራሽ ወገን መሆኑን በተጨባጭ ያመላከተ በጎ ተግባር ነው።

በችግሩ ውስጥ ካሉትም ሆነ ስጋት ውስጥ ከሚገኙ ተጨማሪ ዜጎቻችን አንጻር እየተካሄደ ያለው ድጋፉ ግን በቂ ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም። ችግሩን በስኬት አሸንፎ ለመውጣት በቀጣይም የእያንዳንዱን ዜጋ የነቃ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው።

በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል በተለያዩ ዘርፎች /የስንዴን ምርት ጀምሮ ውጤታማ መሆን በጀመርንበት ታሪካዊ ምዕራፍ የተከሰተው ይህ የድርቅ አደጋ የብልጽግና ጉዟችንን የሚፈታተን ቢሆንም ፤ በጀመርንበት መንገድ በቁርጠኝነት እንድንጓዝ የበለጠ እልሽኝነትን የሚፈጥር ነው።

የተከሰተው የድርቅ አደጋ የቱንም ያህል ቢፈታተነን፤ ቀደም ሲል ከፈተኑንና በአሸናፊነት ከተሻገርናቸው ችግሮቻችን የበለጠ አይሆኑም። ፈተናን ሳይጋፈጥ ለብልጽግና የበቃ አንድም ሀገር የለምና ችግሩ ከማንም በላይ እኔን ይመለከተኛል በሚል የዜግነትና የኃላፊነት መንፈስ በአንድነት መንቀሳቀስ ከቻልን ብዙ ዋጋ ሳያስከፍለን ልንቆጣጠረው እንችላለን። ለዚህ ደግሞ እጅ ለእጅ ተያይዘን ለመንቀሳቀስ ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዓድዋና ሌዎንቴብ

ሰላማዊት ውቤ

«ታሪክ ራሱን አይደግምም፤ የእገሌ ዘመን፣ የምንትሴ ዘመን ከሚለው መመሳሰል ውጪ» ይላል አሜሪካዊው ፀሐፊ ማርክ ትዌይን፤ እርግጥ ነው ፀረ ቅኝ አገዛዝ ጦርነት በብዙ ሀገሮች ተደርጓል፤ በእስያ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በአፍሪካ ለነፃነታቸው ለረጅም ዘመናት የታገሉና ድልም የተቀዳጁ አሉ፤ የአድዋው ጦርነት ግን በተደረገበት የታሪክ የዘመን ነቁጥና ሥፍራ አኳያ ሲታይ እጅግ አንፀባራቂና ቀዳሚ ቦታ ያለው ነው፤ ብዙ ተብሎለታል፤ ለዛሬው መልዕክታችን ከዚሁ የአድዋ ገድል ጋር በቅርብ የተገናኘ አንድ ሩሲያዊን ማስታወስ ፈልጌ ነው፡፡

ኒኮላይ እስቴፓኖቪች ሊዎንቴቭ ይሰኛል፤ ይህ ሰው የአድዋ ጦርነት ከመጀመሩ ጥቂት ጊዜያት በፊት ከአፄ ምኒልክ ጋር በቅርብ የተዋወቀ ነበር፤ ሰውየው የሩሲያ የሚሊታሪ መኮንን የነበረ ሲሆን በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የተጓዘ አገር አሳሽና የጂኦግራፊ ሚሲዮን አባልም ሆኖ ሀገሩን ሩሲያን አገልግሏል።

በ1887 ዓ.ም ነው ከጥቂት ረዳቶቹና ከበጎ ፈቃድ ተጓዦች ጋር ኢትዮጵያ ገብቷል፤ አመጣጡም በኦፊሴላዊ መንገድ ሲሆን የሩሲያ መንግስትን ተልእኮ በመያዝ በጊዜው ለነበሩት ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ለማድረስ ነበር፡፡

አፄ ምኒልክ ከዚህ ሰው ጋር ጥሩ ወዳጅነትና መቀራረብ እንደፈጠሩና አንዳንድ ሀገራዊ ጠቄሜታ ያላቸውን ጉዳዮች እንደፈፀሙ በታሪክ ተፅፎ ይገኛል፤ ወቅቱ ቅኝ ገዢዎች በኢትዮጵያ ዙሪያና ባጠቃላይም አፍሪካውያንን በተገዥነትና በባርነት በመግዛትና በመቆጣጠር የያዙበት ጊዜ ነበር።

ዛሬ የኢትዮጵያ ጎረቤት የነበሩት ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ሱዳን ሀገራት በቅኝ ገዥዎች የተያዙበት ነበር። በአውሮፓውያኑ የቅኝ ግዛት እሽቅድድም ወደኋላ የዘገየችው ኢጣሊያም ኢትዮጵያን ለመያዝ ዝግጅቷን ሁሉ ጨርሳ ትንኮሳዎችን እምታደርግበት ሰዓት ነበር፡፡

ሊዎንቴቭ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የነበረውን ቆይታ ጨርሶ ወደ ሃገሩ ሲመለስ ምኒልክ 30,000 ጠመንጃ፣ ከ5 ሚሊዮን በላይ አረርና ጥይት፣ 42 ያህል የተራራ ላይ መድፎች እንዲያመጣላቸው ከአደራ ጋር ልከውታል፤ ይህን የችግር ቀን ወዳጃቸውን አፄ ምኒልክ ተልዕኮውን ከፈፀመ በኋላ የማዕረግ ሽልማትም እንደሰጡት በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል።

የሩሲያ የኢትዮጵያ እርዳታ ለቀጠለው ለኢትዮ -ሩስያ ግንኙነት መነሻ ነበር፣ ሩሲያ የቀይ መስቀል ተልዕኮ አደራጅታ ልካ ነበር፣ ይህ ተልዕኮ የወታደራዊ እንደምታም ነበረው፤ ለዐድዋ ዘመቻ ለተንቀሳቀሰው ጦር የሕክምና ዕርዳታም ማድረግን ዓላማ ይዞ ነበር የመጣው፤ ይሁንና ይህ ቡድን አዲስ አበባ የደረሰው የአድዋ ውጊያ ከተፈፀመ ከሦስት ወራት በኋላ ነበር፡፡

እርግጥ ነው ዐድዋ የመላው አፍሪቃ (ፓን-አፍሪካዊነት) ምልክት ሆኗል፤ የአይበገሬነትና የአንድነት ትግል ተምሳሌት በመሆንም ይቀጥላል፤ በተጨማሪም ከአድዋ የኢትዮጵያ ድል ማድረግን ተከትሎ አገራችን የታፈረችና የተከበረች ሆና እንድትቆይ ምክንያት ሆኗል፤ ይህንን ጦርነት በማሸነፏም የተነሳ ዙሪያዋን ከከበቧት ኢምፔሪያሊስቶችና ቅኝ ገዢዎች ተከላክላ ድንበሯንም አስከብራለች፡፡ በበርሊኑ ኮንፈረንስ አፍሪቃን ለመቀራመት ያሴሩት መንግስታት እንኳን ከአድዋ ጦርነት በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማድረግ ተሽቀዳድመዋል፡፡

የኢትዮጵያና የሩሲያ ግንኙነት ብዙ ታሪካዊ አጋጣሚዎችን የሚጠቅስና መልከ ብዙ ቢሆንም በሊዎንቴቭ የተጀመረው ወዳጅነት ግን ዘመን ተሻጋሪ ሆኗል፤ የኋላ ኋላ ተጠናክሮ በርከት ላሉ የሁለቱ ሀገራት በተግባር ለተተረጎሙ ክንዋኔዎች ምክንያት ሆኗል፤ከጊዜ በኋላ ተጠናክሮ ለተከፈተው የደጃች ባልቻ ሆስፒታል እርሾ ሆኖ አገልግሏል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጥቅምት 16 ቀን 1950 ዓ.ም የደጃች ባልቻ ሆስፒታል ምሥረታ 10ኛ ዓመት በዓል ላይ ሲናገሩ ፤የሩሲያ መንግስት

**ዛሬ ስለ ዓድዋና ሊዎንቴቭን ስናስታውስ ኢትዮጵያውያን አንድ እውነት እንዳለን መናገር እንሻለን፤ ጠላት የፈለገውን ያህል መሣሪያ ታጥቆና ተደራጅቶ ቢመጣም ያ የዓድዋ ጦርነት ለሀገራችን የሞራል የበላይነት እንደነበረውና ብዙዎችም ምስክርነት እንደሰጡ ማስታወስ እንፈልጋለን፤ ኮሎኒያሊዝምን ያሸነፍነው በዚህ የበላይነት ነው፡፡ነበልባሉን የዓድዋ እሳት ወደ ከሰመ ፍም ሳለመቀየር በአዲስ የፓንአፍሪካዊነት መንፈስ ችቦ ይዘን በመነሳት እናስቀጥል**

ለዜጎቻቸው ጤንነትና ደህንነት የሚየግዙ ተግባራትን በመፈፀሙ እጅጉን መደሰታቸውን ጠቅሰው ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ከዚያም በኋላ የሩሲያና የኢትዮጵያ ግንኙነት እጅግ መልካም በሆነ መንገድ ቀጥሏል፤ ሩሲያም በየዓለም አቀፉ መድረክ ለኢትዮጵያ አጋርነቷን አሳይታለች፤ የታሪክ ምፀት ሆነና ኢትዮጵያ ድል ቀንቷት ራሷን ስታስከብር እንደቀደመው ዘመን ፊት የነሷት አገሮች ግንኙነት ለመቀጠል ሲሽቀዳደሙ ደግሞ ታዝበናል፡፡

ይህ በኒሎላይ እስቴፓኖቪች ሊዎንቴቭ የተጀመረው ምንም ዓይነት ቅኝ ግዛታዊና ኢምፔሪያሊስታዊ ፍላጎትና ዓላማ ያልነበረው የኢትዮጵያና የሩሲያ ግንኙነት በሌሎችም መስኮች በተደረጉ ትብብሮች ተደግመዋል፤ ሩሲያኖች (ሞስኮቦች) በባሕርዳር የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ በአሰብ የነዳጅ ማጣሪያ፣ ኢትዮጵያ በሶማሊያ በተወረረችበት ጊዜ በወታደራዊ መስክ ከኢትዮጵያ ጋር መቆም፤ በኦጋዴንም በምሥራቅና ምዕራብ ጋሻም፣ በካሉብና ጎዴ የነዳጅና ጋዝ ፍለጋና ቁፋሮ ሥራዎች፤ በባሕልና በትምህርት መስክ በተደረጉ ስምምነቶች ብዙ ኢትዮጵያዊያኖች ወደ ሩሲያ ተልከው ተምረው መመለሳቸው ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

በመሠረቱ እነዚህ በሩሲያ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ብቻ ሳይሆን ለዓለምም ተርፈዋል፡፡ ይህ በንጉሳዊው ሥርዓትም ሆነ በሪፑብሊካዊው አስተዳደር ዘመን የቀጠለ ግንኙነት በመርህ ላይ የተመሠረተ ለመሆኑ እምብዛም ማስረጃ የሚጠይቅ አይደለም፡፡በታላቅ ሀገርና በትንሽ ሀገር፣ በሀብታምና በድሃ መካከል የሚታይ ሳይሆን ሀገራት በዓለም አቀፍ መድረክ በእኩልነትና በፍትህ አደባባይ በእኩልነት ይታያሉ በሚለው መርህ መሠረት መሆኑ ነው፡፡

ዛሬ ስለ አድዋና ሊዎንቴቭን ስናስታውስ ኢትዮጵያውያን አንድ እውነት እንዳለን መናገር እንሻለን፤ ጠላት የፈለገውን ያህል መሣሪያ ታጥቆና ተደራጅቶ ቢመጣም ያ የአድዋ ጦርነት ለሀገራችን የሞራል የበላይነት እንደነበረውና ብዙዎችም ምስክርነት እንደሰጡ ማስታወስ እንፈልጋለን፤ ኮሎኒያሊዝምን ያሸነፍነው በዚህ የበላይነት ነው፡፡ ነበልባሉን የአድዋ እሳት ወደ ከሰመ ፍም ላለመቀየር በአዲስ የፓንአፍሪካዊነት መንፈስ ችቦ ይዘን በመነሳት እናስቀጥል፡፡

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# የሁለት አባቶች - አንድ ብሶት

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አንዳንዴ የሆነበትን ሁሉ ሲያስብ ከልብ ይከፋል ። ትናንት ሕይወትና ኑሮው እንዲህ አልነበረም ። ደስተኛና ብርቱ ነበር ። እንዳዛሬው በርካቶች ሳያገሉት፣ ሳያርቁት በፊት ቤተሰቦቹ፣ ወላጆቹ ሲኮሩበት ቆይተዋል ። እሱም ቢሆን ለእነሱ ፈጥኖ ደራሽ ነው ። እጁን አያጥፍም፤ ኪሱን አይሰስትም ። ቀድሞ የሚለው የሚናገረው ሁሉ ይሰማል ። ሀሳቡን የሚያከብሩ፣ ቃሉን የሚፈጽሙ ጥቂት አልነበሩም ።

ዛሬ ላይ ግን የነበረው እንደ ትናንቱ አልሆነም ። ተሰሚነቱ ጠፍቷል፣ ክብሩ ከእሱ ሄዷል ። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱን አሳምሮ ያውቀዋል ። ወላጆቹን ጨምሮ ብዘዎች ፊት ያዞሩበት ጉዳይ በአንድ ልጁ ምክንያት ነው ። ይህን ሲያስብ ይበልጥ ይከፋል ። ለሆነበት፣ ለተደረገበት ሁሉ ራሱን ደጋግሞ ይጠይቃል፣ ውስጡን ያስጨንቃል ። መልስ ሲያጣ ምላሹ የተለመደ ነው ። ኀዘን ብስጭት አያጣውም ። ብቸኝነት፣ ባይተዋርነት ይከበዋል ።

ደጀን ደምስ ትውልድና ዕድገቱ ምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋዳሞት ላይ ነው ። ዕድሜው ከፍ ሲል ከአካባቢው ርቆ የራሱን ሕይወት ጀመረ ። እንዲያም ሆኖ ወላጆቹን አልረሳም ። ጠንካራ ገበሬ ነውና በላቡ ወዝ ካገኘው በረከት «እነሆኝ» ማለትን ለምዷል ።

ደጀን ትውልድ መንደሩን ትቶ ዓመታትን የዘለቀው «መተከል» ከሚባል ቦታ ነበር ። አካባቢው ከእሱ ቢስማማ ጉልበቱን ከፍሎ ሌት ተቀን መትጋት ያዘ። የልፋቱን አላጣም ። የራሱ ጥሪት ኖረው፣ የአቅሙን ገንዘብ ቋጠረ ። በየጊዜው ወላጆቹን እየረዳ የሚቸረው ምርቃት በረከት ሆነለት ።

ጥቂት ቆይቶ ለፍቶ ያገኘበት፣ ሠርቶ የከበረበት፣ አካባቢ የሰላም እጦት ገጠመው ። ስፍራው የጦርነት አየር ነገሰበት ። በርካቶች ክቡር ሕይወታቸውን አጡ። ብዘዎች ቤት ንብረታቸው ወደመ ። እሱን ጨምሮ ሌሎች ደግሞ አካባቢውን ጥለው ሊሸሹ ግድ ሆነ ።

ደጀን ተመልሶ ትውልድ አገሩ ገባ ። ብቻውን አልነበረም ። ሚስቱና ከተወለደ ቀናት ያስቆጠረ ጨቅላ ልጁ አብረውት ናቸው ። አሁን እንደቀድሞው ከእጁ የሚያልፍ፣ ለሌሎች የሚተርፍ ኀበዝ አይደለም ። ጥሪት ሀብቱ የነጠፈበት፣ ቤት ንብረቱን ያጣ ተፈናቃይ ነው። ደጀንን ያገኙት ሁሉ እንደቀድሞው አልሆኑለትም። አቀባበላቸው ቀንሷል ። ፈገግታቸው ደብዝዟል። እንዲህ መሆኑ አባወራውን አስከፍቷል ። በተለይ ወላጆቹ ፊት አልሰጡትም ። የትናንት መልካምነቱን ዘንግተው በየምክንያቱ ያስቀይሙት ይዘዋል ።

ለዚህ ሰበቡ የአንድ ልጁ መታመም ነውና ደጀን ከልቡ አዝኗል ።

ልጁ ከተወለደ ጀምሮ ጤና ኖሮት አያውቅም። አንድ ዓመት ቢሞላውም እናት አባቱን አይለይም፣ እንደ ዕድሜው በወጉ አያይም፣ እንቅስቃሴው የዘገየ ፣ ችግሩ የሰፋ ሆኗል ። ያለበት ዕድሜ «ዳዴ» የሚልበት፣ መውደቅ መነሳትን የሚያውቅበት ነው ። እሱ ግን ከአልጋና ከእናቱ ትከሻ አልወረደም ።

አባት የልጁ ሁኔታ ቢያሳስበው ከቀናት በአንዱ ከሆስፒታል ይዞት ሄደ ። ሀኪሞች የሕፃኑ ችግር በእርግዝና ጊዜ በጭንቅላት ውስጥ የሚከሰት ችግር መሆኑን አስረዱት ።

አባት ስለጉዳዩ ማብራሪያ ጠየቀ ። ህመሙ ጽንሱ በእናት ሆድ ሳለ በጭንላት ላይ የሚከሰትና በሕክምና ስያሜው «ሀይድሮ ሴፋለስ» ተብሎ እንደሚጠራ ተነገረው ። ይህ ችግር ነፍሰጡር ሴት የፎሊክ አሲድን በአግባቡ ባለመውሰዷ ጋር የሚከሰት መሆኑን ተረዳ ።

ደጀን የልጁን ዕጣ ፈንታ እያሰበ ስለመፍትሄው ተጨነቀ ። ባለው ጊዜና አቅም ተጠቅሞ ልጁን ለማሳካም ሮጠ ። ሕክምናው የትኛውም ጤና ተቋም አይገኝም ። ቀዶ ሕክምና የሚያሻው፣ ክትትል የሚያስፈልገው ነው ። ምርጫ አልነበረውም ። ራሱን አበርትቶ ያለውን ቋጥሮ አዲስአበባ ከአንድ ሆስፒታል ደረሰ ። ሆስፒታሉ ለልጁ አልጋ ሰጥቶ ሕክምናው ተጀመረ ። ሕፃኑ አፋጣኝ ቀዶ ሕክምና ተደረገለት ። በጭንቅላቱ «ሸንት» የተባለው መሣሪያ ገብቶም ወደቤቱ ተመለሰ ።



ጉዳዩ በቤተሰቡና በአካባቢው እንደታወቀ አባት ደጀን ሌላ ፈተና ገጠመው ። የልጁ ሕመም ወደሌሎች እንደሚተላለፍ ታስቦ መገለል ይደረግበት ያዘ ። ቤተሰቦቹ ልጃቸውን ከመርዳት ይልቅ ሊቀበሉት ከበዳቸው ። ትናንት ስለእሱ የነበራቸውን አክብሮት ሲያስታውስ በድርጊታቸው አዘነ ። አሁን ለራሱ ቤተሰብ እንኳን የሚተርፍ አቅም የለውም ። እንደቀድሞው የእጁን ሊሰጥ ያለውን ሁሉ ሊያበረክት አይችልም ። ዛሬ የእርዳታ ስንዴ የሚሰፈርለት፣ የእርዳታ እጆችን የሚያይ ተፈናቃይ ነው ።

ደጀን ቤተሰቦቹን ጨምሮ ለአካባቢው ነዋሪ ስለ ልጁ ችግር ሊያስረዳ ሞከረ ። ሕመሙ ለሌሎች ጤና እንደማያሰጋ ዘርዝሮ ሊያሳምን ጣረ ። ቀላል አልሆነለትም ። የሰሙት ሁሉ ፊት አዞሩበት ። ዝም አላለም ። በአካባቢው እንደሱ ልጅ ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው ሕፃናት መኖራቸውን አውቋል ። ወላጆቻቸው ከእይታ ደብቀው ቤት ዘግተውባቸዋል ። እሱ ሕመማቸው ሕክምና እንደሚያግዘው ያውቃልና ሊረዳቸው ይፈልጋል ።

ሁሉም ይህን ሊያደርጉ አይፈቅዱም ። አብዛኞቹ የፍላጎትና የአቅም ማጣት ችግር አለባቸው ። ደጀን የአንድ ዓመት ልጁን አዲስ አበባ ወስዶ ለማሳከም ብዙ ዋጋ ከፍሏል ። በሥራ ማጣትና በችግር እየተፈተነ ለልጁ መኖር ብዙ ታግሏል ። እንደእሱ ይህን ሊያደርጉ የሞከሩ አለመኖራቸውን ሲያስብ ግን ልቡ ያዝናል ።

እናቶች በእርግዝና ጊዜ ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄ ከእሱ በላይ አስረጂና እማኝ የለም ። አባወራው በልጁ የደረሰው ችግር በሌሎች ወላጆች እንዲደርስ አይሻም። የሚሰማው ቢያገኝ የራሱንና የባለቤቱን ተሞክሮ ለሁሉም ማጋራት ይፈልጋል። ብዙዎቹ ግን እውነታውን መቀበል ይከብዳቸዋል። ችግሩን ከእርግማን አያይዘው «የእግዜር ቁጣ» መሆኑን ያምናሉ ።

ደጀን በጤናው ዘርፍ ስለፎሊክ አሲድ አስፈላጊነት ብዙ እንዳልተሠራ ይሰማዋል ። በተለይ ለገጠሯ ሴት በወጉ ግንዛቤው ሊደርስ ይገባል ባይ ነው ። በተቻለ አቅም ይህ ንጥረ ነገር በምግብ፣ በጤፍና በጨው ውስጥ መጨመር ቢችል በርካቶችን መታደግ እንደሚቻል ግንዛቤ ወስዷል ።

በተሳሳተና ባልተገባ ግንዛቤ ደጀንና ባለቤቱን የመሰሉ ወላጆች እንግልትና የበዛ መገለል እያጋጠማቸው ነው ። እንዲህ መሆኑ ሕይወትን በወጉ መርቶ፣ ቤተሰብን በነፃነት ለማሳደር እንቅፋት ይሆናል ።

ከአባት ደጀን ጋር የነበረኝን ቆይታ ጨርሼ ከሌላው አባወራ ወግ ይዣለሁ ። አቶ ጌቱ ዘሪሁን ይባላል ። የወልቂጤ ነዋሪ ነው ። ጌቱ ከአራት ዓመት በፊት የመጀመሪያ ወንድ ልጁን አግኝቷል ። የዛኔ እጅግ ደስተኛ ወላጅ ነበር ። በወቅቱ እንደአባት ለልጁ የሚፈልገውን አሟልቶ ለማሳደግ ሲጥር ቆይቷል ።

በቅርቡ ሁለተኛውን ልጁን ሲታቀፍም ደስታው ከቀድሞ የተለየ አልነበረም ። ሕፃኑ ሁለተኛ ወሩን እንደያዘ ግን የነበረው ስሜት ተቀየረ ። የልጁ ጤና ማጣት ሳቅ ፈገግታውን ነጠቀው ። ሐሳብ ዓላማውን አደበዘዘው ። ጌቱ ልጁን ለማሳየት ጤና ጣቢያ ደረሰ። ከምርመራ በኋላ የሕክምና ባለሙያዎቹ ውጤቱን ነግረው ለከፍተኛ ሕክምና ወደ አዲስ አበባ ጻፉለት የሕፃኑ ችግር በጭንቅላቱ ውስጥ የተፈጠረ የነርቭ ዘንግ ክፍተት መሆኑን ከሄደበት ሆስፒታል አረጋገጠ ።

ከአካባቢው ርቆ ለመጣው አባወራ ይህን መስማት በእጅጉ ይከብዳል ። አሁን የሕመሙን ስሜት ለይቶ የማይነግረው ጨቅላ ሁኔታ እያሳሰበው ነው ። የሰው አገር ሰው ቢሆንም ልጁን ማትረፍ ግድ ይለዋል ። ጌቱ ባለቤቱ በሆስፒታል ክትትል መውለዷን ያውቃል ። ልጁ በተወለደ የመጀመሪያዎቹ ጊዜያትም ምንም የተለየ ምልክት እንዳልነበረው እርግጠኛ ነው ። አሁን ግን ለትንሹ ልጅ ተከታታይ ሕክምና እንደሚያስፈልግ እየተነገረው ነው ።

አባት ጌቱ ልጁን ይዞ በሆስፒታሉ ሕክምናውን ጀመረ ። የሁለት ወሩ ጨቅላ የመጀመሪያው ቀዶ ሕክምና ተደረገለት ። አባወራው ከቤቱ ርቆ ከሆስፒታል አልጋ ይዞ ልጁን እያስታመመ ነው ። በዚህ ስፍራ የሰው ዓይን ይርባል፣ ጠያቂ ዘመድ ይናፍቃል ። እንዳሰበው አልሆነም።

ጌቱ በልጁ ሕመም የቤተሰቦቹን ድርጊት ታዝቧል። በወቅቱ ወላጆቹን ጨምሮ የቅርብ የሚላቸው ሰዎች ያደረባቸው ስሜት የተለየ ነው ። ለሕክምናው አዲስ አበባ በቆየባቸው ጊዜያት የት ወደቅህ? ምን ደረስክ? ያለው የለም ። ቢጨንቀው ራሱ እየደወለ ያለበትን ሁኔታ ይናገር ጀመር ። የተለየ ነገር አላገኘም። ማንም ስለእሱና ስለሚስቱ ፣ ስለሕፃኑ ደህንነት ግድ አልሰጠውም ። በእሱ ግምት እንዲህ መሆኑ ሁሉም በሕፃኑ ላይ ያደረባቸው ተስፋ መቁረጥ ነው ።

ጌቱ እንደሚለው የእሱ ልጅ ማለት ለቤተሰቦቹ እንደተለየ ፍጡር ሆኗል ። ነገ እንደሌሎች ለራሱ የሚበጅ፣ ለአገርም የሚጠቅም አይደለም ። ይህ ዓይነቱ እውነት ለአባት ጌቱ በእጅጉ ይከብዳል ። ገና ከአሁኑ በልጁ እየደረሰበት ያለው መገለል አሳዝኖታል ። እሱ ለሕፃኑ ሕይወት መሮጡ ነገውን በማሰብና ተስፋ በማድረግ ነው ።

የመጀመሪያ ልጁ አሁን አራት ዓመት ሆኖታል። ሲወለድ ጀምሮ አንዳች የጤና ችግር የለውም ። አባት ትንሹ ልጅ የገጠመውን ሕመም በሕክምና እስኪያውቀው የውስጡን ጥያቄ ለመመለስ ቸግሮት ነበር ። ይህ እውነት ከኅብረተሰቡ አመለካከት ተዳምሮም ሲያስጨንቀው፣ ሲያስተክዘው ቆይቷል። አሁን ግን ሕመሙን አውቆ በቂ ግንዛቤ ወስዷል ። የሕፃኑ ችግር በሕክምና አጠራሩ «ሀይድሮሴፋለስ» በሚል ይታወቃል ። ሕመሙ በጭንቅላት ውስጥ ያለ የፈሳሽ መጠን መጨመር ሲሆን በአብዛኛው በእርግዝና የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት በጽንሱ ላይ የሚከሰት ችግር ነው ።

ጌቱ ይህን እውነት ያወቀው እንደሌሎች ወላጆች አስቀድሞ ሳይሆን ከልጁ መወለድ ሁለት ወራት በኋላ ነበር። አባት የመጀመሪያ ልጁ ፍጹም ጤነኛ ነውና ስለምን ብሎ መጨነቅ፣ መጠየቁ አልቀረም ። ለልጁ ሕክምናውን ለመጀመርም ከቦታው ርቆ አዲስ አበባ መምጣት ግድ ይለዋል ። ይህ ሁሉ ለእሱና ለባለቤቱ ቀላል አልሆነም ።

አባወራው ያለዘመድ እገዛ፣ ያለቤተሰብ «አይዞህ» ባይነትግራ በገባው ጊዜ ከጎኑ የቆመለትን አጋር አይረሳም። «ሆፕ ኢሲቢኤች» የተሰኘ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ከጭንቅላት ፈሳሽ መጨመርና ከአከርካሪ ህብለሰርሰር ችግሮች ጋር በሚወለዱ ሕፃናት ላይ የሚሠራ ብቸኛ ተቋም ነው ።

ይህ ተቋም እንደ አባት ደጀን እንደ ጌቱና መሰል ወላጆችን ችግር በማቃለል ይታወቃል ። ድርጅቱ የተመሠረተው በሕመሙ ተጠቂ በሆኑ ሕፃናት ወላጆችና ቤተሰቦቻቸው ነው ። ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለቀዶ ሕክምና የሚመጡ ሕፃናትና ቤተሰቦቻቸውን ተቀብሎ በማቆያዎች በማስተናገድ ችግሮቻቸውን ይቀርፋል ።

ድርጅቱ ከሕመሙ ጋር የተወለዱ ሕፃናትን ለመንከባከብ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን በመስጠት በችግሩ ዙሪያ ግንዛቤዎችን ያስጨብጣል ። ተቋሙ በቀዶ ጥገና ወቅት የሚያስፈልገውን «ሸንት» የተባለ የጭንቅላት ውስጥ አቅርቦት በማሟላትም የበርካታ ሕፃናትን ሕይወት በመታደግ ላይ ይገኛል ።

ዛሬ ጌቱ ቀድሞ በአዕምሮው ሲመላለስ ለቆየው ጥያቄ ምላሹን አግኝቷል ። አሁን እናቶች ከእርግዝና በፊትና በኋላ «ፎሊክ አሲድ»ን በመጠቀም ችግሩን ማምለጥ እንደሚችሉ ያውቃል ። ይህ እውነት በባለቤቱና መሰል እናቶች ዳግም እንዳይከሰት ይጠነቀቃል ። ሌሎችም ከዚህ አጋጣሚ መማር እንዳለባቸው አይጠፋውም ። ችግሩ «በእኛ ይብቃ» ለማለት ግን ግንዛቤው በስፋት ሊኖር ይገባል ባይ ነው ።

አባት ጌቱ አሁን የሕፃናቱ ችግር በሕክምና ከታገዘ መፍትሄ እንዳለው ተገንዝቧል ። ዛሬ ስለ ልጁ ያልተገባ ስሜት ላላቸው ሰዎች ሁሉ የሚሰጠውን ምላሽ ያውቃል። በአካባቢው እንደ እሱ ልጅ ተመሳሳይ ሕመም ያለባቸውን ሕፃናት ወደ ሕክምና በማምጣት የግንዛቤ ለውጥ መፍጠር እንደሚያሻም እየገባው ነው።

ከተለያዩ ቦታዎች በአንድ የተገናኙት ሁለቱ አባቶች ውስጣዊ ብሶት ተመሳሳይ ነው ። ሁለቱም በቤተሰቦቻቸውና በማህበረሰቡ መገለል አግኝቷቸዋል ። ልጆቻቸውን ከሕክምናው እስኪያደርሱም መንገዳቸው ገደል ነበር ።

አሁን የሁለቱም አባቶች አስተሳሰብ በአንድ ተጋምዷል ። ችግርን በመጋፈጥ እንጂ የችግሩን ሰለባዎችና ቤተሰቦቻቸውን በማግለል መፍትሄ እንደማይኖር አውቀዋል ። ይህ እውነት በራሳቸው ሆኖ አይተውታልና ችግሩን ተጋፍጦ ችግር ለመፍታት ግንባር ቀደም ሊሆኑ ዝግጁ ናቸው ። የቆሙት ዛሬ ላይ ነውና ብሶታቸውን የሚቀርፍ፣ ለድካማቸው የሚደርስ ጠንካራ ክንድ፣ አጋር መከታ ይሻሉ ። አሁን! ዛሬ ላይ ።

# ስፖርት



# የሠራተኛው የበጋ ወራት ውድድሮች በጠንካራ ፉክክር ቀጥለዋል

ቦጋስ አበበ

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ለሶስት አመታት ተቋርጠው የነበሩት የሰራተኛው ስፖርት ውድድሮች ባለፈው ጥር 07/2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ በተካሄደው የበጋ ወራት ውድድሮች የመክፈቻ መርሃግብር መቀጠላቸው ይታወሳል። ከስድስት ወራት ላላነሰ ጊዜ በአስር የስፖርት አይነቶች በርካታ ፉክክሮችን የሚያስተናግዱት የሰራተኛው የበጋ ወራት የስፖርት ውድድሮች ባለፉት ሳምንታትም ቀጥለው በጥሩ መነቃቃት እየተካሄዱ ይገኛሉ።

ከፍተኛ ፉክክር በሚያስተናግደው የወንዶች እግር ኳስ ውድድር ባለፈው ሳምንት ስድስት ጨዋታዎች በተለያዩ ሜዳዎች የተካሄዱ ሲሆን፤ ሁሉም ጨዋታዎች በመሸናነፍ ተጠናቀዋል። ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ንፋስ ስልክ ፔፕሲ ኮላ ፋብሪካን 4ለ0 የረታበት ጨዋታ የመጀመሪያው ነው። ኢትዮ ቴሌኮም ረጲ ሳሙና ፋብሪካን 2ለ1 በሆነ ውጤት የረታበት ጨዋታ ጥሩ ፉክክር ከታየባቸው መርሃግብሮች አንዱ ሲሆን፣ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ቃሊቲ ብረታብረት ፋብሪካን በተመሳሳይ 2ለ1 ውጤት ማሸነፍ ችሏል። ኢስት አፍሪካን ቦትሊንግ ካምፓኒ ፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅትን 5ለ2 ያሸነፈበት ጨዋታም በሳምንቱ መርሃግብር በርካታ ግቦች የተቆጠሩበት ሆኗል። ኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስን 2ለ0 ሲረታ፣ ሆራይዘን አዲስ ጎማ ሞኤንኮ ኩባንያን 1ለ0 ያሸነፈበት ጨዋታ በጠባብ ውጤት የተጠናቀቀ መርሃግብር ነው።



በሁለት ዲቪዚዮን ተከፍሎ እየተካሄደ የሚገኘው የእግር ኳስ ውድድር በሰራተኛው ስፖርት ጠንካራ ፉክክር እያስተናገደ ነው፣

በሰራተኛው ስፖርት ሌላው ጠንካራ ፉክክር የሚደረግበት የቮሊቦል ውድድር በወንዶች ሁለት ጨዋታዎችን ያስተናገደ ሲሆን፣ ሙገር ሲሚንቶ ኢትዮ ቴሌኮምን 3ለ0፣ መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ግብርና ስራዎችን 3ለ1 በሆነ ውጤት መርታት እንደቻሉ ከውድድሩ አዘጋጅ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን(ኢሰማኮ) ስፖርት ክፍል የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በወንዶች ጠረጴዛ ቴኒስ በተካሄዱ ሶስት ጨዋታዎች ደግሞ ኢትዮ ቴሌኮም ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካን 3ለ0 ሲረታ፣ ኢትዮ ኤሌክትሪክ አንበሳ የከተማ አውቶቡስን 3ለ1እንዲሁም ፋፋ የምግብ ፋብሪካ ሞኤንኮን 3ለ0 ማሸነፍ ችለዋል። በተመሳሳይ በሴቶች ጠረጴዛ ቴኒስ በተካሄደ ብቸኛ ውድድርም በወንዶች ሽንፈት የገጠመው አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት በሴቶች ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግን 3ለ0 መርታት ችሏል። በዳርትና ቼስ ውድድሮች በሳምንቱ የተካሄዱ በርካታ ፉክክሮችም በመሸናነፍ መጠናቀቃቸው ታውቋል።

የሰራተኛው የበጋ ወራት ውድድሮች ዛሬና ነገ ቀጥለው ሲውሉም በተለያዩ ሜዳዎች የሚካሄዱ ፉክክሮች ይጠበቃሉ። በተለይም በአንደኛና ሁለተኛ ዲቪዚዮን በሚካሄዱ ውድድሮች ጠንካራ ፉክክር ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በርካታ ጨዋታዎችም በተለያዩ ሜዳዎች እንደሚከናወኑ ታውቋል። ከነዚህ መካከል ነገ በጎፋ ካምፕ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ከዮሐንስ ቢፍ ኢንጂነሪንግ በአንደኛ ዲቪዚዮን የሚያደርጉት ፉክክር ተጠባቂ ነው። በተመሳሳይ ዲቪዚዮንና ሜዳ ነገ አንበሳ የከተማ አውቶቡስ ከ ኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ይገናኛሉ። በዚሁ ዲቪዚዮን ነገ ኢትዮ ቴሌኮም ከኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች በስብስቴ ነጋሲ ትምህርት ቤት ሜዳ የሚያደርጉት ጨዋታም ይጠበቃል። በዚሁ ሜዳ ላይ ነገ በሁለተኛ ዲቪዚዮን እግር ኳስ ውድድር መከላከያ ኮንስትራክሽን ከይርጋለም አዲስ ጨርቃጨርቅ የሚያካሂዱት ጨዋታም የዚህ ሳምንት መርሃግብር ይሆናል። በዚሁ ዲቪዚዮን በዳግማዊ ምኒልክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነገ ሁለት ጨዋታዎች ሲካሄዱ ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ሆራይዘን አዲስ ጎማን፣ፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት ኢትዮጵያ ልማት ባንክን ይገጥማሉ።

ዛሬ በሴቶች ቮሊቦል አንደኛ ዲቪዚዮን የሚካሄደው አንድ ጨዋታ አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎትን ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ያገናኛል። በተመሳሳይ ውድድር የወንዶች ሁለተኛ ዲቪዚዮን ደግሞ ሆራይዘን አዲስ ጎማ ከመከላከያ ኮንስትራክሽን፣ ቃሊቲ ብረታብረት ከአዲስ አበባ ቀላል ባቡር የሚጫወቱ ይሆናል። በጠረጴዛ ቴኒስ፣ዳማ፣ዳርትና ቼስ በሁለቱም ፆታ ዛሬ የሚካሄዱ የቤት ውስጥ ውድድሮችም ተጠባቂ ናቸው።

በአገር አቀፍ ደረጃ ትልቅ እንቅስቃሴ ከሚደረግባቸው የስፖርት መድረኮች አንዱ በሰራተኛው መካከል የሚካሄደው ስፖርታዊ ውድድር ነው። በኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን(ኢሰማኮ) አማካኝነት በየአመቱ በሶስት የተለያዩ መድረኮች የሚካሄዱ ስፖርታዊ ውድድሮች በርካታ ቁጥር ያለው ተሳታፊ የሚያስተናግዱ ናቸው። የበጋ ወራት ውድድሮች፣አገር አቀፍ የሰራተኞች ውድድርና አለም አቀፉን የሰራተኞች ቀን ሜይዴይን አስመልክቶ የሚካሄዱት ሶስት የውድድር መድረኮች በኢትዮጵያ ረጅም አመት ያስቆጠሩ መሆናቸው ይታወቃል። እነዚህ የውድድር መድረኮች የተለያዩ ተቋማትና ድርጅቶች በሺዎች የሚቆጠሩ ሰራተኞቻቸውን የሚያሳትፉባቸውም ናቸው።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል ለ2015 በጀት ዓመት ለህሙማን አገልግሎት የሚውል

ሎት 1 የተለያዩ የህሙማን ቀለብ ወተት፣ የታሸጉ ጭማቂዎች፣ የተዘጋጀ በሶ እና ሌሎች ምግቦች በድጋሚ የወጣ

ሎት 2 የተለያዩ አላቂ የፅዳት ዕቃዎች በጨረታ ቁጥር 03/2015 በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሠረት በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች፡ -**

1. በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ ሕጋዊ የአቅራቢዎች ምዝገባ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ፡፡

2 ከአቅራቢዎች ስም ዝርዝር ውስጥ በተለያዩ ጥፋቶች ያልተሰረዙ ወይም የቅጣት ጊዜአቸው ያልተጠናቀቀ በዚህ ጨረታ ላይ መሳተፍ አይችሉም።

3. በገንዘብ ሚ/ር በዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገቡ እንዲሁም 2015 ዓ/ም በጨረታ መሳተፍ የሚችሉ መሆናቸው ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ አካል የተሰጣቸውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ

**እያንዳንዱ ተጫራች፡-**

1. ሎት 1 እና ሎት 2ለሁለቱም ሎቶች ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር/ የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ/የባንክ ጋራንቲ በሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል ስም በማሰራት ማቅረብ ይኖርበታል የባንክ ጋራንቲው ከ90/ዘጠና/ ቀን በላይ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም ተጫራች ሰነድ በሚሞላበት ወቅት ስርዝ ድልዝ ወይንም ፍሉድ መጠቀም የለበትም ይህን ያደረገ ተጫራች ሰነዱ ከውድድር ውጭ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም ተጫራች ናሙና ማቅረብ አለባቸው ተብለው የተገለፁትን ዕቃዎች ናሙና ማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም መጋቢት 11 እና መጋቢት 12/2015 ዓ/ም ብቻ ናሙናውን እስከ ሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል ቢሮ /ጥይት ቤት/ ቅጥር ገጊቢ ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. እያንዳንዱ ተጫራች የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት እስከ መጋቢት 13/2015 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት ድረስ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በጥይት ቤት ቅጥር ግቢ ፋይናንስ ቢሮ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት መጋቢት 13/2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ተዘግቶ ከቀኑ 8፡30 ሰዓት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በጥይት ቤት ቅጥር ግቢ ግዥ ቢሮ ይከፈታል፡፡
6. ጨረታውን ያሸነፉ ተጫራቾች ዕቃውን እስከ መ/ቤታችን መረከቢያ ግምጃ ቤት ድረስ አቅርበው የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፡
7. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ስልክ ቁጥር

011-855-00-24/011-124-12-42... ፋይናንስ ቡድን

011-140-07-96/011-872-13-19. ግዥ ቡድን

## የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል



## Invitation to Bid

The Jigjiga University Sheik Hassen Yabare Referral Hospital Needs to Procure Administration Building Constriction Material Through Open Bidding Method

Procurement Reference number: JJU/SHYRH/NCB/106/2014 E.C

1.The Jigjiga University Sheik Hassen Yabare Referral Hospital (JJUSHYRH) has fund for the procurement of

Lot1: Administration Building Constriction Material

Lot2: Finishing & Decoration Material

2. The Jigjiga University Sheik Hassen Yabare Referral Hospital invites sealed bids from eligible bidders for the supply and delivery of

Lot1: Administration Building Constriction Material

Lot2: Finishing & Decoration Material

3. Bidding will be conducted in accordance with the open tendering procedures contained in the Public Procurement Proclamation of the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and is open to all bidders Who Fulfil The Following Documents 1. Renewed Business License 2 Tin number Certificate and other mandatory documents.

4. Interested eligible bidders may obtain further information from office of the procurement. Tell: 025278-67-87/0915006938 and inspect the bidding documents at the address given below at 8(a) from 2:0011:30 hour in the morning& afternoon every working day in Bid Floating Period.

5. A complete set of Bidding Documents in English may be purchased by interested bidders at the address below at 8(b) and upon payment of a non-refundable fee of Ethiopian Birr 400[four hundred]. The method of payment will be in cash. The document will be sent by [in person or by their representative starting from the day ITB posted]. No liability will be accepted for loss or late delivery.

6. Bids must be delivered to the address below at 8(c) at or before, at 10:00 am in the Morning. All bids must be accompanied by a bid security of Ethiopian Birr, 0.5 up to 2% of total contract price. Late bids shall be rejected. Bids will be opened in the presence of the bidders' representatives who choose to attend at the address below at 8(d) at, at 10:30 am or in the morning.

7. Jigjiga University Sheik Hassen Yabare Referral Hospital reserves the right to reject any bid or all bids at any time prior to contract award without thereby incurring any liability to bidders.

8 (a) Address documents may be inspected at: Office of the procurement,
Tell: 025-278-6787

(b) Address documents will be issued from: JJU SHYRH office of procurement,
Tell: 025278-6787

(c) Address Bids must be delivered to: Office of Procurement, on 22nd Day, after the bid issued on Ethiopian herardat 10:00 am or in the morning

(d) Address of Bid Opening: JJUSHYRH, on 22nd Day,after the bid issued on Ethiopian her aldat 10:30 am or in the Morning

## Jigjiga University